# ኦሪት ዘሌዋውያን

## የሚቃጠል መሥዋዕት

1 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን ጠራው፤ ከመገ
ናኛውም ድንኳን እንዲህ ሲል ተናገረው፤
2“እስራኤላውያንን ተናገራቸው፤ እንዲህም
በላቸው፤ ከእናንተ ማንም ሰው ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) ከእንስሳ ወገን መባ በሚያቀርብበት
ጊዜ ከላሙ፣ ከበጉ፣ ወይም ከፍየሉ መንጋ
መካከል ያቅርብ።
3“ ‘መባው በሚቃጠል መሥዋዕትነት ከላ
ሞች መንጋ መካከል የሚቀርብ ከሆነ፣ እን
ከን የሌለበትን ተባዕቱን መሥዋዕት በእግ
ዚአብሔር (ያህዌ) ዘንድ ተቀባይነት እንዲ
ያገኝ በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ላይ ያቅ
ርበው። 4የሚቃጠል መሥዋዕት ሆኖ በሚ
ቀርበው እንስሳ ራስ ላይም እጁን ይጫን፤
ይህም ያስተሰርይለት ዘንድ በምትኩ ተቀ
ባይነት ያገኛል። 5ወይፈኑን በእግዚአብ
ሔር (ያህዌ) ፊት ይረደው፤ ካህናቱ የአሮን
ልጆችም ደሙን አምጥተው በመገናኛው
ድንኳን ደጃፍ ባለው በመሠዊያው ዙሪያ
ሁሉ ይርጩት። 6እርሱም የሚቃጠለውን
መሥዋዕት ቈዳ ይግፈፍ፤ ብልቱንም ያው
ጣው። 7የካህኑ የአሮን ልጆች በመሠዋ
ያው ላይ ዕንጨት ረብርበው እሳት ያንድ
ዱበት። 8ካህናቱ የአሮን ልጆች ጭንቅላ
ቱንና ሥቡን ጨምረው ብልቶቹን በመሠ
ዊያው ላይ በሚነደው ዕንጨት ላይ ይደር
ድሩት፤ 9አቅራቢው የሆድ ዕቃውንና እግሮ
ቹን በውሃ ይጠብ፤ ካህኑም መባውን ሁሉ
በመሠዊያው ላይ ያቃጥል፤ ይህም በእሳት
የሚቀርብ፣ ሽታውም እግዚአብሔርን (ያህዌ)
ደስ የሚያሰኝ የሚቃጠል መሥዋዕት ይሆ
ናል።
10“ ‘መባው በሚቃጠል መሥዋዕትነት
ከበግ ወይም ከፍየል መንጋ መካከል የሚቀ
ርብ ከሆነ፣ እንከን የሌለበትን ተባዕቱን
ያቅርብ። 11የሚቀርበውን መሥዋዕት ከመሠ
ዊያው በስተ ሰሜን በኩል በእግዚአብሔር
(ያህዌ)ፊት ይረደው፤ ካህናቱ የአሮን ልጆ
ችም ደሙን በመሠዊያው ላይ ዙሪያውን
ሁሉ ይርጩት። 12አቅራቢው ብልቶቹን
ያውጣ፤ ካህኑም ጭንቅላቱንና ሥቡን
ጨምሮ በመሠዊያው ላይ በሚነደው ዕን
ጨት ላይ ይደርድረው፤ 13አቅራቢው የሆድ
ዕቃውንና እግሮቹን በውሃ ይጠብ፤ ካህኑ
መባውን ሁሉ አምጥቶ በመሠዊያው ያቃ
ጥል፤ ይህም በእሳት የሚቀርብ፣ ሽታውም
እግዚአብሔርን (ያህዌ) ደስ የሚያሰኝ የሚቃ
ጠል መሥዋዕት ይሆናል።
14“ ‘ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በሚቃጠል መሥ
ዋዕትነት የሚቀርበው መባ ከወፎች ወገን
ከሆነ፣ ዋኖስ ወይም የርግብ ጫጩት ያቅ
ርብ። 15ካህኑም ወደ መሠዊያው ያምጣው፤
ራሱን ቈልምሞ ይቀንጥሰው፤ የተቈረጠ
ውንም ራስ በመሠዊያው ላይ ያቃጥል፤
ደሙም በመሠዊያው አጠገብ ይንጠፍጠፍ፤
16ከሆድ ዕቃውም ጥሬ ቤቱን[ሀ] ለይቶ ከላባ
ዎቹ ጋር ከመሠዊያው በስተ ምሥራቅ
በኩል፣ ዐመድ በሚፈስበት ስፍራ ይጣ
ለው። 17በክንፎቹ በኩል ለሁለት ይሰንጥ
ቀው፤ ነገር ግን ጨርሶ አያለያየው፤ ካህ
ኑም በመሠዊያው ላይ በሚነደው ዕንጨት
ላይ ያቃጥለው፤ ይህም በእሳት የሚቀርብ፣
ሽታውም እግዚአብሔርን (ያህዌ) ደስ የሚያሰኝ
የሚቃጠል መሥዋዕት ይሆናል።”

## የእህል ቍርባን

2 “ ‘ማንኛውም ሰው የእህል ቍርባን
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በሚያቀርብበት
ጊዜ፣ ዱቄቱ የላመ ይሁን፤ ዘይት ያፍስበት፤
ዕጣንም ይጨምርበት፤ 2ወደ ካህናቱም ወደ
አሮን ልጆች ያምጣው። ካህኑ ከላመው
ዱቄትና ከዘይቱ አንድ እፍኝ ሙሉ ያንሣ
ለት፤ ዕጣኑንም ሁሉ ይውሰደው፤ ይህንም
በእሳት የሚቀርብ፣ ሽታውም እግዚአብሔርን
(ያህዌ) ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት አድርጎ
ለመታሰቢያ በመሠዊያው ላይ ያቃጥለው።
3የተረፈውም የእህሉ ቍርባን ለአሮንና ለል
ጆቹ ይሰጥ፤ ይህም ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
በእሳት ከሚቀርበው ቍርባን እጅግ የተቀ
ደሰ ክፍል ነው።
4“ ‘በማብሰያ ምድጃ የተጋገረ የእህል
ቍርባን በምታቀርብበት ጊዜ፣ ከላመ
ዱቄት ተዘጋጅቶ እርሾ ሳይገባበት በዘይት
ተለውሶ የተጋገረ ኅብስት ይሁን፤ አለዚ
ያም[ለ] ያለ እርሾ በስሱ ተጋግሮ ዘይት
የተቀባ ቂጣ ይሁን። 5የእህል ቍርባንህ
በምጣድ የሚጋገር ከሆነ፣ እርሾ ሳይገባበት
በዘይት ከተለወሰ ከላመ ዱቄት ይዘጋጅ።
6ቈራርሰህ ዘይት አፍስበት፤ ይህ የእህል

1፥1 ዘፀ3፥4፤ 25፥22፤27፥21፤40፥2
1፥2 ዘሌ7፥16:38፤ 22፥21፤23፥38፤ 27፥9፤22፥18-19፤ ዘኍ15፥3
1፥3 ቍ5:10፤ ዘፍ8፥20፤ዘፀ12፥5፤ ዘሌ6፥25፤17፥9፤ 22፥19:20:27፤ ዘኍ6፥16፤ዘዳ12፥5-6:11፤ዕዝ8፥35፤ ኢሳ58፥5፤ሚል1፥8፤ ዕብ9፥14፤ 1ጴጥ1፥19
1፥4 ቍ3፤ ዘፍ32፥20፤ዘፀ29፥10: 15:36፤32፥30፤ ዘሌ4፥29፤6፥25፤ ሕዝ45፥15፤
1፥5 ቍ3፤ ዘፀ29፥1:11:20፤ ዘሌ3፥2:8፤8፥2፤10፥6፤ 21፥1፤ዘኍ15፥8፤ ዘዳ18፥3፤መዝ50፥9፤ 69፥31፤ዕብ12፥24፤ 1ጴጥ1፥2
1፥6 ዘፀ29፥17፤ ዘሌ7፥8፤
1፥7 ቍ17፤ ዘፍ22፥9፤ ዘሌ3፥5፤6፥12
1፥8 ቍ12፤ ዘፀ29፥13፤ ዘሌ8፥20፤ 9፥13
1፥9 ቍ3:13፤ ዘፍ8፥21፤ ዘፀ29፥17: 18፤ዘሌ2፥2፤3፥5:16፤ 6፥22፤9፥14፤17፥6፤ 23፥8:25:36፤ ዘኍ18፥17፤ 8፥6:11-13:19፤ ኤፌ5፥2
1፥10 ቍ3፤ ዘፍ22፥7፤ ዘፀ12፥5፤ዘሌ3፥12፤ 4፥23:28፤5፥6፤ ዘኍ15፥11
1፥11 ዘፀ29፥11:20
1፥12 ቍ8
1፥13 ቍ9፤ ዘፀ29፥17፤ ዘሌ6፥22፤ዘዳ12፥27
1፥14 ዘፍ15፥9፤ ሉቃ2፥24
1፥15 ዘሌ5፥8:9
1፥16 ዘሌ4፥12፤ 6፥10፤ዘኍ4፥13
1፥17 ቍ7፤ ዘፍ15፥10
2፥1 ቍ2:15:16፤ ዘፀ29፥2:40:41፤ ዘሌ5፥11፤6፥14-18፤ 7፥12፤24፥7፤ ዘኍ15፥4፤28፥5፤ ነህ13፥9፤ኢሳ43፥23
2፥2 ቍ9:16፤ ዘሌ1፥9፤5፥11:12፤6፥15፤24፥7፤ዘኍ5፥26፤18፥8፤መዝ16፥5፤ 73፥26፤ኢሳ1፥13፤53፥12፤ 5፥6፤66፥3 2፥3 ቍ10፤ ዘፀ30፥36፤ ዘሌ6፥16፤10፥2:13 2፥4 ዘፀ29፥2፤ዘሌ7፥9:12፤ 8፥26፤ 26፥26 2፥5 ዘሌ6፥21፤ 7፥9፤ሕዝ4፥3

[ሀ] 16 ለዚህ ቃል የዕብራይስጡ ትርጓሜ በርግጠኝነት አይታ ወቅም።
[ለ] 4 ወይም እንዲሁም

ቍርባን ነው። 7የእህል ቍርባንህ በመጥ
በሻ የሚበስል ከሆነ፣ ከላመ ዱቄትና ከዘይት
ይዘጋጅ። 8በዚህ ሁኔታ የተዘጋጀውን የእህል
ቍርባን ወደ እግዚአብሔር (ያህዌ) አምጥተህ
ለካህኑ አስረክብ፤ ካህኑም ወደ መሠዊያው
ይወስደዋል፤ 9ከእህሉም ቍርባን ላይ ለመ
ታሰቢያ የሚሆነውን ክፍል ያነሣና በእሳት
የሚቃጠል፣ ሽታውም እግዚአብሔርን (ያህዌ)
ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት አድርጎ በመሠ
ዊያው ላይ ያቃጥለዋል። 10የተረፈውም ቍር
ባን ለአሮንና ለልጆቹ ይሰጥ፤ ይህም ለእግ
ዚአብሔር (ያህዌ) በእሳት ከሚቀርበው ቍር
ባን እጅግ የተቀደሰ ክፍል ነው።
11“ ‘ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በእሳት በም
ታቀርቡት ቍርባን ውስጥ እርሾ ወይም
ማር ጨምራችሁ ማቃጠል ስለማይገባችሁ፣
በምታቀርቡት በማንኛውም የእህል ቍርባን
እርሾ አይኑርበት። 12እነዚህን የበኵራት
ቍርባን አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
ማቅረብ ትችላላችሁ፤ ነገር ግን ሽታው
ደስ የሚያሰኝ ቍርባን ሆነው በመሠዊያ
ላይ ለመቃጠል አይቀርቡም። 13የምታቀር
በውን የእህል ቍርባን ሁሉ በጨው ቀም
መው፤ የአምላክህ (ኤሎሂም) የቃል ኪዳን ጨው
ከእህል ቍርባንህ አይታጣ፤ በቍርባንህም
ላይ ጨው ጨምርበት።
14“ ‘የእህል በኵራት ቍርባን ለእግዚአ
ብሔር (ያህዌ) በምታመጣበት ጊዜ፣ የተፈ
ተገና በእሳት የተጠበሰ እሸት አቅርብ።
15ዘይት ጨምርበት፤ ዕጣንም በላዩ አስቀ
ምጥ፤ ይህ የእህል ቍርባን ነው። 16ካህኑም
ከተፈተገው እህልና ከዘይቱ ወስዶ፣ ከዕ
ጣኑ ሁሉ ጋር ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በእሳት
የሚቀርብ መታሰቢያ አድርጎ ያቃጥል።

## የኅብረት መሥዋዕት

3 “ ‘ማንኛውም ሰው የሚያቀርበው ቍር
ባን ከላሞች መንጋ የሚቀርብ የኅብረት
መሥዋዕት[ሐ] ከሆነ፣ እንከን የሌለበትን
ተባዕት ወይም እንስት በእግዚአብሔር
(ያህዌ) ፊት ያቅርብ። 2በሚያቀርበው እንስሳ
ራስ ላይ እጁን ይጫን፤ በመገናኛው ድንኳን
ደጃፍ ላይ ይረደው፤ ካህናቱም የአሮን ልጆች
ደሙን በመሠዊያው ላይ ዙሪያውን ይር
ጩት። 3ከኅብረት መሥዋዕቱ ለእግዚአ
ብሔር (ያህዌ) በእሳት የሚቀርብ ቍርባን
አድርጎ ያምጣ፤ የሆድ ዕቃውን የሚሸፍ
ነውን ሥብ፣ በሆድ ዕቃው ላይ ያለውን
ሥብ ሁሉ፣ 4ሁለቱን ኵላሊቶች፣ በኵላሊ
ቶቹ ላይና በጎድኑ አጠገብ ያለውን ሥብ
እንዲሁም የጉበቱን መሸፈኛ ከኵላሊቶቹ
ጋር አንድ ላይ አውጥቶ ያቅርብ። 5የአሮንም
ልጆች በመሠዊያው በሚነደው ዕንጨት
ላይ ባለው በሚቃጠለው መሥዋዕት ላይ
አድርገው ያቃጥሉት፤ ይህም በእሳት የሚ
ቀርብ፣ ሽታውም እግዚአብሔርን (ያህዌ) ደስ
የሚያሰኝ መሥዋዕት ይሆናል።
6“ ‘ከበግ ወይም ከፍየሉ መንጋ ለእግ
ዚአብሔር (ያህዌ) የኅብረት መሥዋዕት የሚያቀ
ርብ ከሆነ፣ እንከን የሌለበትን ተባዕት
ወይም እንስት ያቅርብ። 7መሥዋዕቱ
የበግ ጠቦት ከሆነም፣ በእግዚአብሔር (ያህዌ)
ፊት ያምጣው፤ 8በጠቦቱ ራስ ላይ እጁን
ይጫን፤ በመገናኛው ድንኳን ፊት ለፊት
ይረደው፤ የአሮንም ልጆች ደሙን በመሠ
ዊያው ላይ ዙሪያውን ይርጩት። 9ከኅብረት
መሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በእሳት የሚ
ቀርብ ቍርባን አድርጎ ያምጣ፤ ሥቡን፣
እስከ ጀርባ ዐጥንቱ ድረስ የተቈረጠ ላቱን
በሙሉ፣ የሆድ ዕቃውን የሸፈነውን ሥብ፣
ከሆድ ዕቃው ጋር የተያያዘውን ሥብ
ሁሉ፣ 10ሁለቱን ኵላሊቶች፣ ኵላሊቶቹ
ላይና በጎድኑ አጠገብ ያለውን ሥብ እን
ዲሁም የጉበቱን መሸፈኛ ከኵላሊቶቹ
ጋር አብሮ አውጥቶ ያቅርብ። 11ካህኑም
ይህን ሁሉ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በእሳት
የሚቀርብ የመብል ቍርባን አድርጎ በመ
ሠዊያው ላይ ያቃጥል።
12“ ‘መሥዋዕቱ ፍየል ከሆነ፣ በእግዚ
አብሔር (ያህዌ) ፊት ያቅርብ፤ 13በራሱም ላይ
እጁን ይጫንበት፤ በመገናኛው ድንኳን ፊት
ለፊት ይረደው፤ የአሮንም ልጆች ደሙን
በመሠዊያው ላይ ዙሪያውን ይርጩት።
14ከሚያቀርበውም መሥዋዕት ላይ ለእግዚ
አብሔር (ያህዌ) በእሳት የሚቀርብ ቍርባን
አድርጎ ያቅርብ፤ የሆድ ዕቃውን የሚሸፍ
ነውን ሥብ፣ ከሆድ ዕቃው ጋር የተያያ
ዘውን ሥብ ሁሉ፣ 15ሁለቱን ኵላሊቶች፣
በኵላሊቶቹ ላይና በጎድኑ አጠገብ ያለውን
ሥብ፣ እንዲሁም የጉበቱን መሸፈኛ ከኵላ
ሊቶቹ ጋር አብሮ አውጥቶ ያቅርብ።
16ካህኑም ይህን ሁሉ በእሳት የሚቀርብና
ሽታውም ደስ የሚያሰኝ የመብል ቍርባን
አድርጎ በመሠዊያው ላይ ያቃጥል፤ ሥብ
ሁሉ የእግዚአብሔር (ያህዌ) ነው።
17“ ‘በምትኖሩበት ስፍራ ሁሉ፣ ሥብ
ወይም ደም ከቶ አትብሉ፤ ይህ ለመጪው
ትውልድ ሁሉ የተሰጠ የዘላለም ሥርዐት
ነው።’ ”

## የኀጢአት መሥዋዕት

4 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ ሲል
ተናገረው፤ 2“ለእስራኤል ሕዝብ እን
ዲህ በላቸው፤ ‘ማንም ሰው ባለማወቅ ኀጢ

[ሐ]1 በትውፊት የሰላም መሥዋዕት ይባላል፤ እንዲሁም ቍ 3:6:9 ይመ።

2፥7 ዘሌ7፥9
2፥9 ቍ2፤ዘፍ8፥21
2፥10 ቍ3፤ ዕዝ2፥63
2፥11 ዘፀ23፥18፤ ዘሌ6፥16
2፥12 ዘፀ34፥22
2፥13 ዘኍ18፥19፤ 2ዜና13፥5፤ ሕዝ43፥24፤ማር9፥49
2፥14 ዘፀ34፥22፤ ዘኍ15፥20፤ዘዳ16፥1 3፤26፥2፤ሩት3፥2
2፥15 ቍ1
2፥16 ቍ1:2፤ ዘኍ4፥16፤ ኤር14፥12
3፥1 ቍ6፤ዘፀ12፥5፤ 32፥6፤ዘሌ7፥11-34፤ 17፥5
3፥2 ዘፀ24፥6፤ 29፥15:20፤40፥2፤ ዘሌ1፥5፤17፥6፤ ዘኍ8፥10፤18፥17
3፥3 ዘፀ29፥13፤ 12፥9
3፥4 ቍ10፤ ዘፀ29፥13፤ዘሌ4፥9
3፥5 ቍ11:16፤ ዘፀ29፥13:38-42፤ ዘሌ1፥7:9፤7፥29-34፤ ዘኍ28፥3-10
3፥6 ቍ1፤ ዘሌ22፥21፤ ዘኍ15፥3:8
3፥7 ዘሌ17፥3:8-9፤ ዘኍ15፥5፤28፥5:7:8፤ 1ነገ8፥62
3፥8 ዘሌ1፥5
3፥9 ኢሳ34፥6፤ ኤር46፥10፤ ሕዝ39፥19፤ ሶፎ1፥7
3፥11 ቍ5:16፤ ዘሌ9፥18፤21፥6:17፤ ዘኍ28፥2
3፥12 ዘሌ1፥10፤ 4፥3
3፥13 ዘፀ24፥6፤ ዘሌ1፥5
3፥15 ዘሌ7፥4
3፥16 ቍ5:11፤ ዘፍ4፥4፤ዘሌ1፥9፤ 7፥31፤1ሳሙ2፥16
3፥17 ዘፍ9፥4:12፤ ዘፀ12፥14:20፤ 27፥21፤ዘሌ7፥25-26 17፥10-16፤ ዘዳ12፥16፤ ሐሥ15፥20
4፥2 ቍ13:22:27፤ ዘሌ5፥15-18፤ 22፥14፤ዘኍ15፥22: 24-29፤35፥11-15፤ ኢሱ20፥3:9፤ዕብ9፥7

አት ቢሠራ፣ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) አታድርጉ
ብሎ ካዘዛቸውም አንዱን ተላልፎ ቢገኝ፣
3“ ‘የተቀባውም ካህን በሕዝቡ ላይ በደል
የሚያስከትል ኀጢአት ቢሠራ፣ ስለ ሠራው
ኀጢአት እንከን የሌለበት አንድ ወይፈን
*ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) የኀጢአት መሥዋዕት
አድርጎ ያቅርብ። 4ወይፈኑን በመገናኛው
ድንኳን ደጃፍ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት
ያቅርብ፤ እጁንም በወይፈኑ ራስ ላይ ይጫን፤
*በእግዚአብሔርም* (ያህዌ) ፊት ይረደው። 5የተ
ቀባው ካህን ከወይፈኑ ደም ጥቂት ወስዶ
ወደ መገናኛው ድንኳን ይግባ፤ 6ጣቱንም
በደሙ ውስጥ ነክሮ ከመቅደሱ መጋረጃ
ትይዩ፣ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ሰባት
ጊዜ ይርጨው። 7ካህኑ ከደሙ ጥቂት ወስዶ
በመገናኛው ድንኳን ውስጥ *በእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ፊት ያለውንና ሽታው ጣፋጭ የሆነ
ዕጣን የሚታጠንበትን መሠዊያ ቀን
ዶች ይቀባ። የተረፈውን የወይፈኑን ደም
ሁሉ በመገናኛው ድንኳን መግቢያ ላይ
ባለው በሚቃጠል መሥዋዕት መሠዊያ
ግርጌ ያፍሰው፤ 8ለኀጢአት መሥዋዕት ከሚ
ቀርበው ወይፈን ሥቡን ሁሉ ያውጣ፤
ይኸውም፦ የሆድ ዕቃውን የሚሸፍነውን
ሥብና ከሆድ ዕቃው ጋር የተያያዘውን
ሥብ፣ 9ሁለቱንም ኵላሊቶች፣ በኵላሊ
ቶቹ ላይና በጎድኑ አጠገብ ያለውን ሥብ
እንዲሁም የጒበቱን መሸፈኛ ከኵላሊ
ቶቹ ጋር አብሮ አውጥቶ ያቅርብ፤ 10ለኅ
ብረት መሥዋዕትም[መ] ከሚቀርበው ወይፈን[ሠ]
እንዳወጣ ሁሉ ሥቡን ያውጣ፤ ካህኑም
የሚቃጠል መሥዋዕት በሚቀርብበት መሠ
ዊያ ላይ ያቃጥለው። 11ነገር ግን የወይ
ፈኑን ቈዳና ሥጋውን ሁሉ፣ ጭንቅላቱንና
እግሮቹን፣ ሆድ ዕቃውንና ፈርሱን፣ 12የወ
ይፈኑን ብልት ሁሉ ከሰፈር ውጭ ዐመድ
ወደሚፈስበት በአምልኮው ሥርዐት መሠረት
ንጹሕ ወደ ሆነው ስፍራ ይውሰደው፤ በተቈ
ለለው ዐመድ ላይ ዕንጨት አንድዶ ያቃ
ጥለው።
13“ ‘መላው የእስራኤል ሕዝብ ባለ
ማወቅ ኀጢአት ቢሠራ፣ አታድርጉ ብሎ
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ካዘዘውም አንዱን
ተላልፎ ቢገኝ፣ ይህ ሕዝብ ጥፋቱ ባይታ
ወቀውም በደለኛ ነው። 14የሕዝቡ ጉባኤ
ኀጢአት መሥራቱን በተረዳ ጊዜ፣ ለኀጢ
አት መሥዋዕት የሚሆን አንድ ወይፈን
በመገናኛው ድንኳን ፊት ያቅርብ። 15የሕ
ዝቡም ሽማግሌዎች *በእግዚአብሔር* (ያህዌ)
ፊት እጆቻቸውን በወይፈኑ ራስ ላይ ይጫኑ፤
ወይፈኑም *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ይታ
ረድ። 16የተቀባውም ካህን ከወይፈኑ ደም
ጥቂት ወስዶ ወደ መገናኛው ድንኳን
ይግባ። 17ጣቱን በደሙ ውስጥ ነክሮ፣
በመጋረጃው ትይዩ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ ፊት
ሰባት ጊዜ ይርጨው። 18ከደሙ ጥቂት
ወስዶ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ *በእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ፊት ያለውን የመሠዊያ ቀን
ዶች ይቀባ፤ የተረፈውን ደም ሁሉ በመ
ገናኛው ድንኳን መግቢያ ላይ ባለው
በሚቃጠል መሥዋዕት መሠዊያ ግርጌ ያፍ
ሰው። 19ከወይፈኑም ሥቡን ሁሉ ወስዶ
በመሠዊያው ላይ ያቃጥል፤ 20ለኀጢአት መሥ
ዋዕት ባቀረበው ወይፈን ላይ እንዳደረገው
ሁሉ፣ በዚህኛውም ወይፈን ያድርግ፤ በዚ
ህም መሠረት ካህኑ ስለ ሕዝቡ ያስተሰ
ረያል፤ እነርሱም ይቅር ይባላሉ። 21ወይ
ፈኑንም ከሰፈር ውጭ ያውጣው፤ የመ
ጀመሪያውን ወይፈን እንዳቃጠለው
ሁሉ ይህኛውንም ያቃጥል፤ ይህም ስለ
ሕዝቡ የሚቀርብ የኀጢአት መሥዋዕት
ነው።
22“ ‘አንድ የሕዝብ መሪ ባለማወቅ ኀጢ
አት ቢሠራ፣ አምላኩም *እግዚአብሔር*
(ኤሎሂም ያህዌ) አታድርጉ ብሎ ከከለከላቸው
ትእዛዛት አንዱን ተላልፎ ቢገኝ እርሱ
በደለኛ ነው። 23ኀጢአት መሥራቱን በተ
ረዳ ጊዜ እንከን የሌለበትን ተባዕት ፍየል
የግሉ መሥዋዕት አድርጎ ያቅርብ። 24እጁ
ንም በፍየሉ ራስ ላይ ይጫን፤ የሚቃጠል
መሥዋዕት በሚታረድበትም ስፍራ *በእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ፊት ይረደው፤ ይህም የኀጢ
አት መሥዋዕት ነው። 25ካህኑም ከመሥዋዕቱ
ደም በጣቱ ጥቂት ወስዶ የሚቃጠል መሥ
ዋዕት የሚቀርብበትን መሠዊያ ቀንዶች
ይቀባ፤ የተረፈውንም ደም ሁሉ በመሠዊያው
ግርጌ ያፍሰው። 26የኅብረት መሥዋዕቱን
እንዳቃጠለ ሁሉ ሥቡንም በሙሉ በመ
ሠዊያው ላይ ያቃጥል፤ በዚህም መሠረት
ካህኑ የሰውየውን ኀጢአት ያስተሰረይለ
ታል፤ ሰውየውም ይቅር ይባላል።
27“ ‘ከሕዝቡ መካከል አንዱ ሰው ባለ
ማወቅ ኀጢአት ቢሠራ፣ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
አታድርጉ ብሎ ከከለከላቸው ትእዛዛት
አንዱን ተላልፎ ቢገኝ እርሱ በደለኛ
ነው። 28ኀጢአት መሥራቱን በተረዳ ጊዜ፣
እንከን የሌለባትን እንስት ፍየል ስለ
ፈጸመው ኀጢአት የግሉ መሥዋዕት አድርጎ
ያቅርብ። 29እጁን ለኀጢአት መሥዋዕት
በቀረበችው ፍየል ራስ ላይ ይጫን፤ የሚ
ቃጠል መሥዋዕት በሚታረድበት ስፍራም

4፥3 ቍ14፡24፡32፤ ዘፍ18፥23፤ዘፀ12፥5፤ 28፥41፤30፥10፤ ዘሌ3፥12፤5፥6-13፤ 8፥14፤9፥2-22፤ 10፥16፤16፥3፡5፤ 19፥16፤ዘኍ15፥27፤ መዝ66፥15፤ ሕዝ 43፥19፡23፤ ዕብ9፥13-14
4፥4 ቍ15፡24፤ ዘሌ1፥3፤ዘኍ8፥12
4፥5 ቍ16፤ ዘሌ16፥14
4፥6 ቍ7፤ዘፀ25፥8፤ 24፥8፤ዘሌ16፥14፡19
4፥7 ቍ18፡30፡34፤ ዘፀ27፥2፤29፥12፤ ዘሌ5፥9፤8፥15፤9፥9፤ 16፥18
4፥8 ቍ 19፤
4፥9 3፥4
4፥10 ዘፀ29፥13፤ 32፥6፤ዘሌ9፥4
4፥11 ዘፀ29፥14፤ ዘሌ8፥17፤9፥11፤ ዘኍ19፥5
4፥12 ዘፀ29፥14፤ ዘሌ1፥16፤6፥11፡30፤ 8፥17፤9፥11፤10፥14፤ 16፥3፤ዘኍ19፥9፤ ዕብ13፥11
4፥13 ቍ2
4፥14 ቍ3፤ ዘኍ15፥24
4፥15 ቍ4፤ ዘፀ3፥16፤19፥7፤ 29፥10፤ዘሌ8፥14፡22፤ ዘኍ8፥10፤2ዜና29፥23
4፥16 ቍ5
4፥17 ቍ6፤ ዘኍ19፥4፡18
4፥18 ቍ7፤ ዘሌ5፥9፤6፥30፤8፥15፤ 10፥18፤17፥6፤ 2ዜና29፥22
4፥19 ቍ8፡26
4፥20 ቍ26፡31፡ 35፤ዘፀ29፥36፤ 32፥30፤ዘኍ15፥25፤ ሮሜ3፥25፤ ዕብ10፥10-12
4፥21 ቍ12፤ ዘሌ16፥5፡15፤ 2ዜና29፥21
4፥22 ቍ2፤ ዘኍ31፥13
4፥23 ቍ3፤ ዘሌ1፥10
4፥24 ቍ3፡4፤ ዘሌ6፥25
4፥25 ዘሌ9፥9፤ 16፥18፤ ሕዝ43፥20፡22
4፥26 ዘፀ32፥30፤ ዘሌ5፥10፤12፥8
4፥27 ቍ2
4፥28 ቍ3፤ ዘሌ1፥10፤5፥6፤ ሕዝ40፥39፤44፥27
4፥29 ቍ4፡24፤ ዘፍ8፥20፤ዘሌ1፥4

[መ]10 በትውፊት ***የሰላም መሥዋዕት*** ይባላል፤ እንዲሁም ቍ 26፡31፡35 ይመ።
[ሠ]10 የዕብራይስጡ ቃል ተባዕትንና እንስትን ሊያጠቃልል ይችላል።

ይረዳት:: [30]ካህኑ በጣቱ ከደሟ ጥቂት
ወስዶ የሚቃጠል መሥዋዕት የሚቀርብበትን
መሠዊያ ቀንዶች ይቅባ፤ የተረፈውንም
ደም ሁሉ በመሠዊያው ግርጌ ያፍሰው::
[31]ሥቡን ከኅብረት መሥዋዕት በወጣበት
አኳኋን ሥቡን ሁሉ ያውጣ፤ ካህኑም ሽታው
እግዚአብሔርን (ያህዌ) ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት
አድርጎ በመሠዊያው ላይ ያቃጥለው፤ በዚ
ህም መሠረት ካህኑ የሰውየውን ኀጢአት
ያስተሰርይለታል፤ ሰውየውም ይቅር ይባ
ላል::
[32]“ ‘ስለ ኀጢአት መሥዋዕት የበግ ጠቦት
የሚያቀርብ ከሆነ፣ እንከን የሌለባትን እን
ስት ያቅርብ:: [33]እጁን በጠቦቷ ራስ ላይ
ይጫን፤ የሚቃጠል መሥዋዕት በሚታረ
ድበት ስፍራም የኀጢአት መሥዋዕት አድርጎ
ይረዳት:: [34]ካህኑም ከኀጢአት መሥዋዕቱ
ደም በጣቱ ጥቂት ወስዶ የሚቃጠል
መሥዋዕት የሚቀርብበትን መሠዊያ ቀንዶች
ይቅባ፤ የተረፈውንም ደም ሁሉ በመ
ሠዊያ ግርጌ ያፍሰው:: [35]ሥቡ ከኅብረት
መሥዋዕት ጠቦት በወጣበት አኳኋን
ሥቡን ሁሉ ያውጣ፤ ካህኑም በመሠዊያው
ላይ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በእሳት በሚቀር
በው መሥዋዕት ላይ ያቃጥለው:: በዚህ
መሠረት ሰውየው የሠራውን ኀጢአት
ካህኑ ያስተሰረይለታል፤ ሰውየውም ይቅር
ይባላል::

5 “ ‘አንድ ሰው ስላየውና ስለሚያውቀው
ነገር ሕጋዊ ምስክርነቱን እንዲሰጥ
ተጠይቆ ቃሉን ለመስጠት ፈቃደኛ ባይ
ሆን፣ ይህ ሰው ኀጢአት ሠርቶአልና ይጠ
የቅበታል::
[2]“ ‘ማንኛውም ሰው ሳያውቅ በሥርዐቱ
መሠረት የተከለከለውን ርኩስ ነገር
ቢነካ፣ ይኸውም:- የረከሰ የአውሬ በድን
ወይም የረከሰ የቤት እንስሳ በድን ወይም
በደረቱ እየተሳበ የሚንቀሳቀሰውን የረከሰ
ፍጥረት በድን ቢነካ ይህ ሰው ረክሶአል፤
በደለኛም ነው::
[3]“ ‘ወይም የሰውን ርኵሰት ይኸውም
ርኵስ የሚያደርገውን ማናቸውንም ነገር
ሳያውቅ ቢነካ፣ ነገሩን ባወቀ ጊዜ በደለኛ
ይሆናል::
[4]“ ‘ሰዎች በሚምሉበት በማናቸውም
ነገር፣ በጎ ወይም ክፉ ለማድረግ ሳያስብ
በግዴለሽነት ቢምል በኋላ ግን ነገሩን ባወቀ
ጊዜ በደለኛ ይሆናል::
[5]“ ‘ማንኛውም ሰው ከእነዚህ በአንዱ
በደለኛ ሆኖ ቢገኝ፣ የትኛውን ኀጢአት
እንደሠራ ገልጾ መናዘዝ አለበት፤ [6]ስለ
ኀጢአቱም ቅጣት የኀጢአት መሥዋዕት
እንድትሆነው ከመንጋው አንዲት የበግ
ወይም የፍየል እንስት ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) ያቅርብ፤ ካህኑም ስለ ኀጢአቱ ያስተ
ሰረይለታል::
[7]“ ‘ሰውየው ስለ ሠራው ኀጢአት በግ
ለማቅረብ ዐቅሙ ካልፈቀደ ሁለት ዋኖሶች
ወይም ሁለት የዋኖስ ጫጩቶች የመጀ
መሪያውን ለኀጢአት መሥዋዕት፣ ሁለተ
ኛውን ለሚቃጠል መሥዋዕት ለእግዚአ
ብሔር (ያህዌ) ያቅርብ:: [8]ወደ ካህኑም ያም
ጣቸው፤ እርሱም ለኀጢአት መሥዋዕት
የምትሆነውን አስቀድሞ ያቅርብ፤ ራሷን
ዐንገቷ ላይ ይቈልምም፤ ነገር ግን ቈርጦ
አይጣል፤ [9]ከኀጢአት መሥዋዕቱም ጥቂት
ደም ወስዶ በመሠዊያው ዙሪያ ላይ ይር
ጨው፤ የተረፈውም ደም ሁሉ በመሠዊ
ያው ግርጌ ይፍሰስ፤ ይህም የኀጢአት
መሥዋዕት ነው:: [10]ካህኑም ቀደም ሲል
በታዘዘው መሠረት ሁለተኛዋን የሚቃጠል
መሥዋዕት አድርጎ ያቅርብ፤ ካህኑም የሰው
የውን ኀጢአት ያስተሰረይለታል፤ ሰውየውም
ይቅር ይባላል::
[11]“ ‘ሰውየው ሁለት ርግቦች ወይም
ሁለት የዋኖስ ጫጩቶች ለማቅረብ ዐቅሙ
ካልፈቀደ፣ ስለ ሠራው ኀጢአት የኢፍ
መስፈሪያ[ሌ] አንድ ዐሥረኛ የላመ ዱቄት
ለኀጢአት መሥዋዕት ያቅርብ፤ ነገር ግን
የኀጢአት መሥዋዕት ስለሆነ ዘይት አያፍ
ስበት፤ ዕጣንም አይጨምርበት፤ [12]ከዚያም
ለካህኑ ያቅርብ፤ ካህኑም ለመታሰቢያ እን
ዲሆን ዕፍኝ ሙሉ ይዝገንለት፤ በእሳት
ከሚቀርበውም ቍርባን በላይ አድርጎ
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በመሠዊያው ላይ በእ
ሳት ያቃጥለው፤ ይህም የኀጢአት መሥዋዕት
ነው:: [13]ሰውየው ከእነዚህ በአንዱ ኀጢ
አት ቢሠራ፣ ካህኑ በዚህ ሁኔታ ያስተሰር
ይለታል፤ ሰውየውም ይቅር ይባላል:: ከመ
ሥዋዕቱ የተረፈውም እንደ እህል ቍር
ባን ሁሉ ለካህኑ ይሆናል::’ ”

## የበደል መሥዋዕት

[14]እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ [15]“ማንኛውም ሰው በደል ቢፈጽም
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) ከተቀደሰ ከማናቸውም
ነገር በማጕደል ኀጢአት ቢሠራ፣ ከመንጋው
እንከን የሌለበትን አውራ በግ የበደል
መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
ያቅርብ:: የዋጋውም ግምት በቤተ መቅ
ደሱ ሰቅል[ሰ] መሠረት ተመዝኖ በጥሬ ብር
ይሁን፤ ይህም የበደል መሥዋዕት ነው::
[16]ከተቀደሱ ነገሮች ያጐደለውንም ይተካ፤

4፥30 ቍ7
4፥31 ቍ20:35፤ ዘፍ8፥21፤ዘሌ1፥4
4፥32 ዘፀ29፥38፤ ዘሌ1፥3፤9፥3፤ 14፥10
4፥33 ቍ29፤ ዘሌ1፥4:5
4፥34 ቍ7
4፥35 ቍ31
5፥1 ቍ17፤ ዘፀ28፥38፤ዘሌ7፥18፤ 17፥16፤19፥8፤ 20፥17፤24፥15፤ ዘኍ5፥31፤9፥13፤ 15፥31፤19፥20፤ 30፥15፤ምሳ29፥24፤ ማቴ26፥63፤
5፥2 ቍ3፤ ዘሌ7፥21፤11፥8:11: 24-40፤13፥45፤ ዘዳ14፥8፤ዘኍ19፥22 ኢዮ15፥16፤ መዝ51፥5፤ኢሳ6፥5፤ 52፥11፤ 64፥6፤ ሕዝ36፥17፤ሐጌ2፥13
5፥3 ዘሌ7፥20፤ 11፥25፤14፥19፤ 21፥1፤ዘኍ5፥2፤9፥6፤ 19፥7:11-16፤ ሕዝ44፥25
5፥4 ዘኍ30፥6:8፤ ኢሳ41፥23
5፥5 ዘሌ16፥21፤ 26፥40፤ዘኍ5፥7፤ ኢሱ7፥19፤ 1ነገ8፥47፤ምሳ28፥13
5፥6 ዘፀ32፥30፤ ዘሌ1፥10፤4፥3:28
5፥7 ቍ11፤ ዘፍ15፥9፤ዘሌ12፥8፤1 4፥21፤14፥22:30፤ 27፥8፤ዘኍ6፥10
5፥8 ዘሌ1፥15:17
5፥9 ዘፀ24፥6፤ ዘሌ1፥15፤4፥7
5፥10 ዘፀ32፥30፤ ዘሌ1፥14-17፤4፥26፤ 1ዜና15፥13
5፥11 ቍ7፤ ዘፍ15፥9፤ዘፀ16፥36፤ ዘሌ2፥1
5፥12 ዘፀ2፥2፤ ዘሌ2፥9
5፥13 ዘፀ29፥41፤ 32፥30፤ዘሌ2፥3
5፥15 ቍ16:18፤ ዘፀ29፥3፤30፥13፤ ዘሌ4፥2፤6፥5:6፤7፥1: 7፤14፥12- 17፤19፥21:22፤22፥1 4፤ዘኍ5፥8፤ 6፥12:14፤ 15፥6፤18፥9፤28፥11፤ 1ሳሙ6፥3፤ ዕዝ10፥19፤ ኢሳ53፥10
5፥16 ቍ15፤ ዘሌ6፥4፤27፥13፤ ዘኍ5፥7
5፥17 ቍ1:15

[ሌ]11 ሁለት ሊትር ገደማ ይሆናል
[ሰ]15 11.5 ግራም ይሆናል::

የዚህንም ተመን አንድ አምስተኛ በላዩ
ጨምሮ ለካህኑ ይስጥ፤ ካህኑም ከበጉ ጋር
የበደል *መሥዋዕት* አድርጎ በማቅረብ ያስ
ተሰርይለታል፤ ሰውየውም ይቅር ይባላል።
17“ ‘ማንኛውም ሰው ኀጢአት ቢሠራ፣
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) አታድርጉ ብሎ ከከለ
ከላቸው ትእዛዛት ሳያውቅ አንዱን ተላልፎ
ቢገኝ በደለኛ ነው፤ በኀጢአቱም ይጠየቅ
በታል። 18እርሱም ከመንጋው ለበደል *መሥ
ዋዕት* የሚሆን እንከን የሌለበት አውራ በግ
ወደ ካህኑ ያምጣ፤ ዋጋውም ተመጣጣኝ
ይሁን። ካህኑም በዚህ ሁኔታ ሰውየው
ሳያውቅ ስለ ፈጸመው ስሕተት ያስተሰር
ይለታል፤ ሰውየውም ይቅር ይባላል። 19ይህ
የበደል *መሥዋዕት* ነው። ሰውየውም *በእግ
ዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ጥፋት በመፈጸሙ
በደለኛ[ሸ] ነው።”

6 *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2“ማንኛውም ሰው በዐደራ የተ
ሰጠውን ወይም በመያዣነት የተቀበለውን
በመካድና ባልንጀራውን በማጭበርበር ኀጢ
አት ቢሠራ፣ *እግዚአብሔርንም* (ያህዌ) ቢበድል
ወይም ባልንጀራውን ቢቀማው ወይም
ቢያታልለው፣ 3ወይም የጠፋ ነገር አግኝቶ
አላየሁም ቢል ወይም በሐሰት ቢምል
ወይም ሰዎች የሚያደርጉትን እንዲህ ያለውን
ማናቸውንም ኀጢአት ቢሠራ፣ 4በዚህ ሁኔታ
ኀጢአት ቢሠራና በደለኛ ቢሆን፣ የሰረቀ
ውን ወይም የቀማውን ወይም በዐደራ
የተሰጠውን ወይም ጠፍቶ ያገኘውን ይመል
ሳል፤ 5በሐሰት የማለበትንም ሁሉ ይመልስ፤
የበደል *መሥዋዕቱን* በሚያቀርብበት ጊዜ
የወሰደውን በሙሉ የዋናውን አንድ አምስ
ተኛ በመጨመር ለባለ ንብረቱ ይመልስ።
6ከመንጋውም እንከን የሌለበትን ዋጋው
ተመጣጣኝ የሆነ አውራ በግ ስለ በደሉ
*መሥዋዕት* አድርጎ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ)
ለማቅረብ ወደ ካህኑ ያምጣ፤ 7በዚህም ሁኔታ
ካህኑ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ያስተሰረ
ይለታል፤ ሰውየውም ስለ ፈጸመው ስለ ማን
ኛውም በደል ይቅር ይባላል።

### የሚቃጠል *መሥዋዕት*

8*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 9“አሮንና ልጆቹን እንዲህ ብለህ
እዘዛቸው፤ ‘ስለሚቃጠለው *መሥዋዕት* አቀ
ራረብ የምትከተለው *ሥርዐት* ይህ ነው:-
የሚቃጠለው *መሥዋዕት* ሌሊቱን ሁሉ
እስኪነጋ ድረስ በመሠዊያው ላይ ባለው
ማንደጃ ላይ ይቀመጥ፤ እሳቱም በመሠዊ
ያው ላይ ዘወትር ሲነድ ይደር። 10ካህኑም
ከበፍታ የተሠራ የውስጥ ሱሪውን ካጠለቀ

5፥18 ቍ15፤ ዘሌ6፥6፤14፥12፤
5፥19 2ነገ12፥16
6፥2 ዘፍ31፥7፤ ዘፀ22፥7፤ዘሌ19፥11፤ ዘኍ5፥6፤መዝ73፥27 ኤር9፥4፡5፤ ሐሥ5፥4፤ቈላ3፥9
6፥3 ዘፀ23፥4፤ 22፥11
6፥4 ዘሌ5፥16፤ ሕዝ33፥15፤ ሉቃ19፥8
6፥5 ዘሌ5፥15፤ ዘኍ5፥7
6፥6 ዘሌ5፥15፤ ዘኍ5፥8
6፥7 ዘፀ32፥30
6፥9 ቍ12፤ ዘሌ7፥37
6፥10 ዘፀ28፥39-42፡ 43፤39፥27፤28፤ ዘሌ1፥16
6፥11 ዘሌ4፥12
6፥12 ዘፀ29፥13፤ 32፥6፤ዘሌ1፥7
6፥14 ዘሌ2፥1፤ ዘኍ6፥15፤15፡4፤ 28፥13
6፥15 ዘሌ2፥1፡2፡9
6፥16 ቍ26፤ ዘፀ27፥9፤29፥11፡31፤ ዘሌ2፥3፡11፤8፥31፤ 10፥13፤16፥24፤24፥9 ዘኍ18፥10፤ ሕዝ44፥29
6፥17 ቍ29፤ ዘፀ29፥28፤40፥10፤ ዘሌ7፥7፤10፥12፡16፡18፤21፥22፤24፥9፤ ዘኍ5፥9፤18፥9፡10
6፥18 ቍ29፤ ዘፍ9፥12፤ዘፀ30፥29፤ ዘሌ2፥3፤7፥6፤ ዘኍ5፥9፤18፥9-10
6፥20 ዘፀ16፥36፤ 28፥41፤29፥2፤ ዘሌ23፥13፤ ዘኍ4፥16፤5፥15፤ 28፥5
6፥21 ዘሌ2፥5
6፥22 ዘፀ28፥41፤ 29፥30፤ዘሌ1፥9

በኋላ፣ የበፍታ ቀሚሱን ይልበስ፤ እሳቱ
በመሠዊያው ላይ *መሥዋዕቱን* ከበላው በኋላ
የሚቀረውን ዐመድ አንሥቶ፣ በመሠዊ
ያው አጠገብ ያፍስስ። 11ከዚያም ልብሱን
አውልቆ ሌላ ልብስ ይቀይር፤ ዐመዱንም
ተሸክሞ ከሰፈር ውጭ በአምልኮው *ሥርዐት*
*መሠረት* ንጹሕ ወደ ሆነ ስፍራ ይውሰድ።
12በመሠዊያው ላይ ያለው እሳት ዘወትር
ይንደድ፤ ምን ጊዜም አይጥፋ። ካህኑ ጧት
ጧት እሳቱ ላይ ማገዶ ይጨምር፤ በእሳቱ
ላይ የሚቃጠለውን *መሥዋዕት* ያዘጋጅ፤
በዚህም ላይ የኅብረት *መሥዋዕቱን*[ቀ] *ሥብ*
ያቃጥል። 13በመሠዊያው ላይ ያለው እሳት
ዘወትር ይንደድ፤ ምን ጊዜም አይጥፋ።

### የእህል ቍርባን

14“ ‘የእህል ቍርባን *ሥርዐት* ይህ ነው:-
የአሮን ልጆች ቍርባኑን በመሠዊያው ትይዩ
*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ያቅርቡት። 15ካህኑ
ከላመው ዱቄትና ከዘይቱ አንድ ዕፍኝ
ያንሣለት፤ በእህሉ ቍርባን ላይ ያለውንም
ዕጣን በሙሉ ይውሰድ፤ ይህንም፣ ሽታው
*እግዚአብሔርን* (ያህዌ) ደስ የሚያሰኝ *መሥዋ
ዕት* አድርጎ፣ ለመታሰቢያ በመሠዊያው
ላይ ያቃጥለው። 16የተረፈውንም አሮንና
ልጆቹ ይብሉት፤ እርሾ ሳይገባበት በተቀደ
ሰው ስፍራ፣ በመገናኛው ድንኳን ቅጥር
ግቢ ውስጥ አደባባዩ ላይ ይብሉት። 17ያለ
እርሾ *መጋገር* አለበት፤ በእሳት ከሚቀርብ
ልኝ ቍርባን ይህን የእነርሱ ድርሻ አድ
ርጌ ሰጥቻቸዋለሁ። ይህም፣ እንደ ኀጢ
አት *መሥዋዕትና* እንደ በደል *መሥዋዕት*
ሁሉ እጅግ የተቀደሰ ነው። 18ማንኛውም
ከአሮን ዘር የተወለደ ወንድ ሊበላው ይች
ላል፤ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) ከሚቀርበው የእ
ሳት ቍርባን ለእርሱ የተመደበ የዘላለም
ድርሻው ነው፤ የሚነካውም ሁሉ[በ] ቅዱስ
ይሆናል።’ ”
19*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 20“አሮን ወይም ልጆቹ በተቀቡበት
ዕለት[ተ] *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) የሚያቀርቡት
ቍርባን ይህ ነው:- የኢፍ[ቸ] አንድ ዐሥረኛው
የላመ ዱቄት ግማሹን ለጧት፣ ግማሹን
ለማታ የዘወትር የእህል ቍርባን አድርገው
ያቅርቡት። 21በሚገባ በዘይት ተለውሶ በም
ጣድ ላይ ይጋገር፤ ከዚያም የእህሉን ቍርባን
ቈራርሰህ[ኀ] ሽታው *እግዚአብሔርን* (ያህዌ) ደስ
የሚያሰኝ ይሆን ዘንድ አቅርብ። 22በእርሱ

[ሸ]19 ወይም *ለፈጸመው በደል ሙሉ የኀጢአቱ ማስተስረያ ነው።*
[ቀ]12 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል።
[በ]18 ወይም *የሚነካው ሰው ሁሉ፤* እንዲሁም ቍ 27 ይመ
[ተ]20 ወይም *በተቀባበት ዕለት አሮን እና ልጆቹ*
[ቸ]20 ሁለት ሊትር ገደማ ይሆናል
[ኀ]21 የዚህ ቃል የዕብራይስጡ ትርጓሜ በእርግጠኝነት አይታወቅም

ቦታ ተቀብቶ ካህን የሚሆነው ልጁ ይህን
ያዘጋጅ፤ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የተመደበ ድርሻ
ነውና ፈጽሞ ይቃጠል። 23ካህኑ የሚያቀር
በው የእህል ቍርባን ሁሉ ፈጽሞ ይቃጠል
እንጂ አይበላ።”

## የኀጢአት መሥዋዕት

24እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤
25“አሮንንና ልጆቹን እንዲህ በላቸው፤ ስለ
ኀጢአት መሥዋዕት አቀራረብ የምትከተለው
ሥርዐት ይህ ነው፤ የሚቃጠል መሥዋዕት
በሚታረድበት ስፍራ የኀጢአቱም መሥዋዕት
እዚያው በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት ይታረድ፤
ይህም እጅግ ቅዱስ ነው። 26መሥዋዕቱንም
የሚያቀርበው ካህን ይብላው፤ ይህም በተቀ
ደሰው ስፍራ በመገናኛው ድንኳን ቅጥር
ግቢ ውስጥ፣ በአደባባዩ ላይ ይበላ። 27ሥጋ
ውን የሚነካ ሁሉ የተቀደሰ ይሆናል፤ ደሙ
በልብስ ላይ ቢረጭ፣ ያን ልብስ በተቀደሰ
ስፍራ እጠብ። 28ሥጋው የተቀቀለበት የሸ
ክላ ዕቃ ይሰበር፤ የናስ ዕቃ ከሆነ ግን ተፈ
ግፍጎ በውሃ ይታጠብ። 29ከካህናት ወገን
የሆነ ወንድ ሁሉ ከዚህ መብላት ይችላል፤
ይህም እጅግ ቅዱስ ነው። 30ነገር ግን ደሙ
ለማስተሰረያ እንዲሆን ወደ መገናኛው
ድንኳን ወደ ቅድስት የቀረበው የኀጢአት
መሥዋዕት ሁሉ በእሳት ይቃጠል እንጂ
አይበላ።

## የበደል መሥዋዕት

7 “ ‘እጅግ ቅዱስ የሆነው የበደል መሥ
ዋዕት የአቀራረብ ሥርዐት ይህ ነው፦
2የሚቃጠል መሥዋዕት በሚታረድበት ስፍራ
የበደሉም መሥዋዕት እዚያው ይታረድ፤
ደሙም በመሠዊያው ላይ ዙሪያውን ይረጭ።
3ሥቡን በሙሉ ያቅርብ፤ ይኸውም፦ ላቱን፣
የሆድ ዕቃውን የሚሸፍነውን ሥብ፣ 4ሁለቱ
ኵላሊቶች፣ በኵላሊቶቹ ላይና በጐድኑ
አጠገብ ያለውን ሥብ እንዲሁም ከኵላሊ
ቶቹ ጋር የሚወጣውን የጕበቱን ሽፋን
አብሮ ያቅርብ። 5ካህኑም ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) በእሳት የሚቀርብ አድርጎ በመሠዊያው
ላይ ያቃጥል፤ ይህም የበደል መሥዋዕት
ነው። 6ከካህን ወገን የሆነ ወንድ ሁሉ ከዚህ
መብላት ይችላል፤ ነገር ግን በተቀደሰ ስፍራ
ይበላ፤ ይህም እጅግ ቅዱስ ነው።
7“ ‘የኀጢአት መሥዋዕትና የበደል መሥ
ዋዕት አቀራረብ ሥርዐት አንድ ነው፤
መሥዋዕቶቹ የስርየቱን ሥርዐት ለሚያስ
ፈጽመው ካህን ይሰጣሉ። 8ስለ ማንኛውም
ሰው የሚቃጠል መሥዋዕት የሚያቀርበው
ካህን ቈዳውን ለራሱ ይውሰድ። 9በማብሰያ
ምድጃ የተጋገረ፣ በመቀቀያ ወይም በም

6፥25 ዘፀ29፥11፤ 30፥10፤ዘሌ1፥3፤ 4፥24
6፥26 ቊ16፤ ዘፀ27፥9፡21፤40፥2
6፥27 ዘፀ29፥37፤ ዘሌ10፥10፤ ሕዝ44፥19፤46፥20፤ ሐጌ2፥12
6፥28 ዘሌ11፥33፤ 15፥12፤ዘኍ19፥15
6፥29 ቊ17፡18፤ ሕዝ42፥13
6፥30 ዘሌ4፥12፡18፤ ሕዝ45፥15
7፥1 ዘሌ5፥15፤ ሕዝ40፥39
7፥3 ዘፀ29፥13
7፥4 ዘሌ3፥15
7፥5 ዘፀ29፥13
7፥6 ዘሌ6፥18፤ ሕዝ42፥13
7፥7 ቊ6፤ ዘፀ30፥10፤ ዘሌ2፥3፤5፥15፤6፥17፡26፤14፥13፤ዘኍ5፥8፤ 2ነገ12፥16፤ 1ቆሮ9፥13፤10፥18
7፥8 ዘሌ1፥6
7፥9 ዘሌ2፥4፡5፡7
7፥12 ቊ13፡15፤ ዘሌ2፥1፡4፤22፥29፤ ዘኍ6፥19፤መዝ50፥14፤54፥6፤107፥22፤116፥17፤ኤር33፥11፤ 44፥19
7፥13 ቊ12፤ ዘፀ34፥22፤ ዘሌ23፥17፤ አሞ4፥5
7፥15 ዘፀ12፥10
7፥16 ዘፍ28፥20፤ ዘፀ35፥29፤ ዘሌ1፥2፤19፥5-8፤ 22፥18፡21፤23፥38፤ ዘኍ15፥3፤29፥39፤ ዘዳ12፥6፤23፥21-23፤መዝ54፥6፤ ሕዝ46፥12
7፥17 ዘፀ12፥10፤ ዘሌ19፥6
7፥18 ዘሌ5፥1፤ 19፥7፤ዘኍ18፥27፤ 2ዜና33፥16
7፥20 ዘፍ17፥14፤ ዘሌ5፥3፤22፥3-7
7፥21 ዘሌ5፥2
7፥23 ዘሌ17፥3፤ ዘዳ14፥4
7፥24 ዘፀ22፥31

ጣድ የበሰለ ማንኛውም የእህል ቍርባን
ለሚያቀርበው ካህን ይሰጥ። 10ማናቸውም
በዘይት የተለወሰ ወይም ደረቅ የእህል
ቍርባን ለአሮን ልጆች ሁሉ እኩል ይሰጥ።

## የኅብረት መሥዋዕት

11“ ‘አንድ ሰው ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
የኅብረት መሥዋዕት' በሚያቀርብበት ጊዜ፣
ሊከተለው የሚገባው ሥርዐት ይህ ነው፦
12“ ‘መሥዋዕቱን የሚያቀርበው ለምስጋና
መግለጫ ከሆነ፣ ከምስጋና መሥዋዕቱ ጋር
ያለ እርሾ የተጋገረና በዘይት የተለወሰ
ኅብስት እርሾ ሳይገባበት በሥቡ ተጋግሮ
ዘይት የተቀባ ቂጣ በሚገባ ታሽቶ በዘይት
የተለወሰም የላመ ዱቄት ኅብስት አብሮ
ያቅርብ። 13ለምስጋና ከሚሆነው የኅብረት
መሥዋዕት ጋር በእርሾ የተጋገረ ኅብስት
ያቅርብ። 14ከእያንዳንዱም ዐይነት አንዳንድ
አንሥቶ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የተለየ ቍር
ባን በማድረግ ያቅርብ፤ ይህም የኅብረት
መሥዋዕቱን ደም ለሚረጨው ካህን ይሰጥ።
15ለምስጋና የሚሆነው የኅብረት መሥዋዕት
ሥጋ፣ በቀረበበት ዕለት ይበላ እንጂ አን
ዳች አይደር።
16“ ‘መሥዋዕቱ ስእለት በመፈጸሙ ወይም
በበጎ ፈቃድ የሚቀርብ ከሆነ፣ በቀረበበት
ዕለት ይበላ፤ የተረፈውም ሁሉ በማግስቱ
ይበላ። 17እስከ ሦስት ቀን የቆየ ማንኛ
ውም የመሥዋዕቱ ሥጋ ይቃጠል። 18ማንኛ
ውም የኅብረት መሥዋዕት ሥጋ በሦስተኛው
ቀን ከተበላ ተቀባይነት የለውም፤ ርኵስ
በመሆኑ ላቀረበው ሰው ዋጋ አይኖረውም፤
ከዚያም የበላ ሰው የበደል ዕዳ ይሆንበታል።
19“ ‘ርኩስ ከሆነ ነገር ጋር የተነካካ ሥጋ
ይቃጠል እንጂ አይበላ። ሌላውን ሥጋ ግን
በሥርዐቱ መሠረት ንጹሕ የሆነ ማንኛውም
ሰው ይብላ፤ 20ነገር ግን ንጹሕ ያልሆነ ማን
ኛውም ሰው ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የቀረበውን
የትኛውንም የኅብረት መሥዋዕት ሥጋ
ቢበላ፣ ከሕዝቡ ፈጽሞ ይወገድ። 21ማንኛውም
ሰው የሰውን ርኵሰት ወይም ርኩስ እንስ
ሳን ወይም ማንኛውንም ርኩስ ነገር ቢነካና
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) ከቀረበው የኅብረት
መሥዋዕት ሥጋ ቢበላ፣ ያ ሰው ፈጽሞ ከሕ
ዝቡ ይወገድ።

## ሥብና ደም መብላት መከልከሉ

22እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 23“ለእስራኤላውያን እንዲህ በላቸው፤
‘የበሬ ወይም የላም፣ የበግ ወይም የፍየል
ሥብ አትብሉ። 24ሞቶ የተገኘው ወይም

'11 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል፤ እንዲሁም
ቊ 13-37 ይመ

አውሬ የገደለው ከብት ሥብ ለሌላ ተግ
ባር ይዋል እንጂ አይበላ። 25ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) በእሳት ከሚቀርብ[ኘ] እንስሳ ሥብ
የሚበላ ማንኛውም ሰው ከሕዝቡ ይወገድ።
26በየትኛውም ቦታ ብትኖሩ የማንኛውንም
የወፍ ዘር ወይም የእንስሳ ደም አትብሉ።
27ማንኛውም ሰው ደም ቢበላ፣ ያ ሰው
ከሕዝቡ ይወገድ።’ ”

### የካህኑ ድርሻ

28እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 29“ለእስራኤላውያን እንዲህ በላቸው፤
‘የኅብረት መሥዋዕት ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ስለ ራሱ
መሥዋዕት አድርጎ ከዚሁ ላይ ለእግዚአ
ብሔር (ያህዌ) ያቅርብ። 30በእሳት ለእግዚአ
ብሔር (ያህዌ) የሚቀርበውን መሥዋዕት በራሱ
እጅ ያቅርበው፤ ሥቡን ከፍርምባው ጋር
ያቅርብ፤ ፍርምባውን መሥዋዕት አድርጎ
በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት ይወዝውዘው።
31ካህኑ ሥቡን በመሠዊያው ላይ ያቃጥል፤
ፍርምባው ግን ለአሮንና ለልጆቹ ይሰጥ።
32የኅብረት መሥዋዕታችሁን የቀኝ ወርች
ለካህኑ የተለየ አድርጋችሁ ስጡት። 33የኅብ
ረት መሥዋዕቱን ደምና ሥብ የሚያቀር
በው የአሮን ልጅ ቀኝ ወርቹን የራሱ
ድርሻ አድርጎ ይውሰድ። 34ከእስራኤላውያን
የኅብረት መሥዋዕት ላይ የተወዘወዘውን
ፍርምባና የቀረበውን ወርች ወስጃለሁ፤
ለካህኑ ለአሮንና ለልጆቹም ከእስራኤላው
ያን የሚያገኙት መደበኛ ድርሻቸው እን
ዲሆን ሰጥቻቸዋለሁ።’ ”

35ካህናት ሆነው እግዚአብሔርን (ያህዌ)
እንዲያገለግሉ በቀረቡ ቀን፣ በእሳት ለእግዚ
አብሔር (ያህዌ) ከቀረበው መሥዋዕት ላይ
ለአሮንና ለልጆቹ የተመደበላቸው ድርሻ
ይህ ነው። 36ካህናቱ በተቀቡበት ቀን፣ እስ
ራኤላውያን መደበኛ ድርሻ አድርገው ከት
ውልድ እስከ ትውልድ ይህን እንዲሰጧ
ቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) አዘዘ።

37እንግዲህ የሚቃጠል መሥዋዕት፣ የእ
ህል ቍርባን፣ የኀጢአት መሥዋዕት፣ የበደል
መሥዋዕት፣ የክህነት ሹመት መሥዋዕትና
የኅብረት መሥዋዕት ሥርዐት ይህ ነው፤
38ይህም፣ በሲና ምድረ በዳ እስራኤላው
ያን መሥዋዕታቸውን ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
እንዲያቀርቡ ባዘዛቸው ቀን በሲና ተራራ
ላይ ለሙሴ የሰጠው ሥርዐት ነው።

### አሮንና ልጆቹ ካህናት ሆነው መሾማቸው

8፥1-36 ተጓ ምብ ዘፀ 29፥1-37

8 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤
2“አሮንንና ልጆቹን፣ ልብሰ ተክህኖውን፣

7፥26 ዘፍ9፥4
7፥27 ዘፍ9፥4
7፥30 ዘፀ29፥4
7፥31 ዘፀ29፥13፡27
7፥32 ዘፀ29፥27፤ ዘሌ10፥14፡15፤ ዘኍ5፥9፤6፥20፤ 18፥18
7፥34 ዘፀ29፥22፡ 27፤ ዘሌ10፥15፤ ዘኍ6፥20፤1ሳሙ 9፥24፤
7፥36 ዘሌ8፥12፡30
7፥37 ዘፀ29፥31፤ ዘሌ6፥9፡14
7፥38 ዘፀ19፥11፤ ዘሌ1፥2፤26፥46፤ ዘኍ36፥13፤ዘዳ4፥5፤ 29፥1
8፥2 ቊ18፡22፤ ዘፀ28፥1፡2፡4፡43፤ 29፥2-3፤30፥10፡ 23-25፡30፤39፥27፤ ዘሌ1፥5
8፥3 ዘኍ8፥9
8፥5 ዘፀ29፥1
8፥6 ዘፀ29፥4፤ 30፥19፤ሐሥ22፥16
8፥7 ዘፀ28፥4
8፥8 ዘፀ25፥7፤ 28፥30
8፥9 ዘፀ28፥2፡36፤ 39፥28፤ዘሌ21፥10
8፥10 ቊ2፤ ዘፀ26፥1፤30፥26
8፥11 ዘፀ30፥29
8፥12 ዘፀ30፥30፤ ዘሌ7፥36
8፥13 ዘፀ28፥4፡ 39፡40፤39፥27፤ ዘሌ21፥10
8፥14 ዘፀ30፥10፤ ዘሌ4፥3፡15
8፥15 ዘሌ4፥7፡ 18፤ሕዝ43፥20፤ ዕብ9፥22
8፥17 ዘሌ4፥11፡12
8፥18 ቊ2

የመቅቢያ ዘይቱን፣ ለኀጢአት መሥዋዕት
የሚሆነውን ወይፈን፣ ሁለቱን አውራ በጎ
ችና እርሾ ሳይገባበት የተጋገረው ቂጣ ያለ
በትን መሶብ አምጣ፤ 3ማኅበሩን በሙሉ
በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ሰብስብ።” 4ሙሴም
እግዚአብሔር (ያህዌ) እንዳዘዘው አደረገ፤ ማኅ
በሩም በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ተሰበሰበ።

5ሙሴም ማኅበሩን፣ “እግዚአብሔር (ያህዌ)
እንዲደረግ ያዘዘው ይህ ነው” አላቸው።
6ሙሴም አሮንንና ልጆቹን ወደ ፊት አወ
ጣቸው፤ በውሃም አጠባቸው። 7አሮንን
እጀ ጠባብ አለበሰው፤ መቀነት አስታጠ
ቀው፤ ቀሚስ አጠለቀለት፤ ኤፉድ ደረበለት፤
በልዩ ጥበብ በተጠለፈው መታጠቂያ ኤፉ
ዱን አስታጠቀው፤ በላዩም አሰረው፤ 8የደረት
ኪሱን በላዩ አደረገለት፤ በደረት ኪሱም
ውስጥ ኡሪምንና ቱሚምን አኖረ። 9እግዚ
አብሔር (ያህዌ) ባዘዘውም መሠረት፣ ሙሴ
ጥምጥሙን በአሮን ራስ ላይ አደረገ፤ በጥ
ምጥሙም ላይ በፊት ለፊቱ በኩል የተቀ
ደሰውን አክሊል አደረገለት።

10ሙሴም መቅቢያ ዘይቱን ወሰደ፤
ማደሪያ ድንኳኑንና በውስጡ የሚገኘውን
ሁሉ ቀብቶ ቀደሰ። 11ከዘይቱም ጥቂት
ወስዶ በመሠዊያው ላይ ሰባት ጊዜ ረጨ፤
ይቀድሳቸውም ዘንድ መሠዊያውን ከነመገ
ልገያ ዕቃው ሁሉ እንዲሁም የመታጠቢያ
ሳሕኑን ከነማስቀመጫው በዘይት ቀባ። 12ከመ
ቅቢያ ዘይቱም በአሮን ራስ ላይ አፈሰሰ፤
የተቀደሰ እንዲሆንም ቀባው። 13እግዚአ
ብሔርም (ያህዌ) ባዘዘው መሠረት ሙሴ፣ የአ
ሮንን ልጆች ወደፊት አቅርቦ እጀ ጠባብ
አለበሳቸው፤ መታጠቂያ አስታጠቃቸው፤
ቆብም ደፋላቸው።

14ሙሴም የኀጢአት መሥዋዕት የሆነ
ውን ወይፈን አመጣ፤ አሮንና ልጆቹም
በወይፈኑ ራስ ላይ እጃቸውን ጫኑ። 15ሙሴም
ወይፈኑን ዐረደ፤ ደሙንም ወስዶ መሠዊ
ያውን ያነጻ ዘንድ በጣቱ የመሠዊያውን
ቀንዶች ሁሉ ቀባ፤ የቀረውንም ደም በመ
ሠዊያው ሥር አፈሰሰው። ለመሠዊያውም
እንዲህ አድርጎ ያስተሰርይለት ዘንድ ቀደ
ሰው። 16ሙሴም የሆድ ዕቃውን የሚሸፍ
ነውን ሁሉ፣ የጕበቱን ሽፋን፣ ኵላሊቶ
ችንና ሥባቸውን ወስዶ በመሠዊያው ላይ
አቃጠለ። 17ሙሴም እግዚአብሔር (ያህዌ)
ባዘዘው መሠረት ወይፈኑን፣ ቈዳውን፣
ሥጋውንና ፈርሱን ከሰፈር ውጭ አቃ
ጠለ።

18ሙሴ ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚሆ
ነውን አውራ በግ አቀረበ፤ አሮንና ልጆቹም

[ኘ]25 ወይም በእሳት ከቀረበው

እጃቸውን በበጉ ላይ ጫኑ፡፡ [19]ሙሴም
በጉን ዐርዶ ደሙን በመሠዊያው ላይ ዙሪ
ያውን ረጨ፡፡ [20]በጉንም በየብልቱ ቈራረጠ፤
ጭንቅላቱን፣ ብልቶቹንና ሥቡን አቃ
ጠለ፡፡ [21]ሆድ ዕቃውንና እግሮቹን በውሃ
አጠበ፤ ሙሴም እግዚአብሔር (ያህዌ) ባዘዘው
መሠረት፣ በጉን በሙሉ ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) በእሳት የሚቀርብ፣ ሽታውም ደስ የሚ
ያሰኝ የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ በመ
ሠዊያው ላይ አቃጠለው፡፡

[22]ሙሴ ለቅድስና የሚሆነውን ሌላ
አውራ በግ አቀረበ፤ አሮንና ልጆቹም እጆ
ቻቸውን በበጉ ራስ ላይ ጫኑ፡፡ [23]ሙሴ
አውራ በጉን ዐረደ፤ ከደሙም ጥቂት
ወስዶ የአሮንን ቀኝ ጆሮ ጫፍ፣ የቀኝ
እጁን አውራ ጣትና የቀኝ እግሩን አውራ
ጣት አስነካ፤ [24]የአሮንንም ልጆች ወደ
ፊት ጠራ፤ ከደሙም ጥቂት ወስዶ የቀኝ
ጆሮአቸውን ጫፍ፣ የቀኝ እጃቸውን አውራ
ጣትና የቀኝ እግራቸውን አውራ ጣት አስ
ነካ፤ የቀረውንም ደም በመሠዊያው ላይ
ዙሪያውን ረጨ፡፡ [25]ሥቡን፣ ላቱን፣ ሆድ
ዕቃውን የሚሸፍነውን ሥብ ሁሉ፣ የጕበቱን
ሽፋን፣ ሁለቱን ኵላሊቶችና ሥባቸውን
እንዲሁም ቀኝ ወርቹን ወሰደ፤ [26]በእግዚ
አብሔርም (ያህዌ) ፊት ካለው፣ ያለ እርሾ
የተጋገረ ዳቦ ካለበት መሶብ ላይ አንድ
ኅብስት፣ አንድ በዘይት የተጋገረ ዳቦ እን
ዲሁም ስስ ቂጣ ወስዶ በሥቦቹና በቀኝ
ወርቹ ላይ አኖረ፡፡ [27]እነዚህንም ሁሉ ለአሮ
ንና ለልጆቹ በእጃቸው ሰጣቸው፤ እነርሱም
የሚወዘወዝ መሥዋዕት አድርገው በእግዚ
አብሔር (ያህዌ) ፊት ወዘወዙት፡፡ [28]ሙሴም
ከእጃቸው ተቀብሎ፣ ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
በእሳት የሚቀርብ፣ ሽታውም ደስ የሚያ
ሰኝ መሥዋዕት አድርጎ በመሠዊያው ላይ
በሚቃጠለው መሥዋዕት ላይ አቃጠለው፡፡
[29]ሙሴም እግዚአብሔር (ያህዌ) ባዘዘው መሠ
ረት፣ ድርሻው የሆነውን ክህነት የመስጫ
ውን አውራ በግ ፍርምባ ወስዶ የሚወዘ
ወዝ መሥዋዕት በማድረግ በእግዚአብሔር
(ያህዌ) ፊት ወዘወዘው፡፡

[30]ቀጥሎም ሙሴ በመቅቢያው ዘይትና
በመሠዊያው ላይ ካለው ደም ጥቂት ወስዶ፣
በአሮንና በልብሱ እንዲሁም በአሮን ልጆ
ችና በልብሳቸው ላይ ረጨ፤ በዚህም ሁኔታ
አሮንንና ልብሱን፣ ልጆቹንና ልብሳቸውን
ቀደሰ፡፡

[31]ሙሴም አሮንና ልጆቹን እንዲህ አላ
ቸው፤ "ሥጋውን በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ
ቀቅሉት፤ በዚያም፣ 'አሮንና ልጆቹ ይብሉት'
ተብዬ በታዘዝሁት[ሀ] መሠረት፣ በክህነት
መስጫው መሥዋዕት መሶብ ውስጥ ካለው

8፥20 ዘሌ1፥8
8፥22 ቍ2፤ ዘሌ4፥15
8፥23 ዘሌ14፥14፡25
8፥24 ዕብ9፥18-22
8፥25 ዘሌ3፥3-5
8፥26 ዘሌ2፥4
8፥27 ዘኍ5፥25
8፥29 ዘሌ7፥31-34
8፥30 ዘፀ28፥1፡2፤ ዘሌ7፥36
8፥31 ዘሌ6፥16
8፥33 ዘሌ14፥8፤ 15፥13፡28፤ ዘኍ19፥11፤ ሕዝ43፥25
8፥34 ዕብ7፥16
8፥35 ዘሌ18፥30፤ 22፥9፤ዘኍ3፥7፤9፥19 ዘዳ11፥1፤1ነገ2፥3፤ ሕዝ48፥11፤ዘካ3፥7
9፥1 ዘሌ4፥15፤ ሕዝ43፥27
9፥3 ቍ8፡15፤ ዘሌ4፥3፡32፤10፥16
9፥4 ዘፀ29፥43፤ 32፥6፤ዘሌ4፥10፤
9፥6 ዘፀ16፥7
9፥7 ዘፀ30፥10፤ ዘሌ16፥6፤ ዕብ5፥1፡3፤7፥27
9፥8 ዘሌ4፥1-12፤ 10፥19

ኅብስት ጋር ብሉት፤ [32]የተረፈውንም ሥጋና
ኅብስት በእሳት አቃጥሉ፡፡ [33]የክህነት መቀ
በያችሁ ሥርዐት እስከሚፈጸምበት እስከ
ሰባት ቀን ድረስ በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ
ቆዩ፤ ሥርዐቱንም ለመፈጸም ሰባት ቀን
ይወስዳልና፡፡ [34]ዛሬ የተፈጸመው ይህ ሥርዐት
ለእናንተ ማስተሰረያ እግዚአብሔር (ያህዌ) ያዘ
ዘው ነው፡፡ [35]እንዳትሞቱ ሰባቱን ቀንና
ሌሊት ከመገናኛው ድንኳን ደጃፍ አትለዩ፤
የእግዚአብሔርንም (ያህዌ) ሥርዐት ጠብቁ፤
የታዘዝሁት እንዲህ ነውና፡፡" [36]አሮንና
ልጆቹም እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ አማ
ካይነት ያዘዘውን ሁሉ አደረጉ፡፡

## ካህናቱ አገልግሎታቸውን ጀመሩ

9 በስምንተኛውም ቀን ሙሴ አሮንንና
ልጆቹን እንዲሁም የእስራኤልን ሽማ
ግሌዎች ጠራቸው፤ [2]አሮንንም እንዲህ አለው፤
"የኀጢአት መሥዋዕት እንዲሆንልህ አንድ
እንቦሳ እንዲሁም የሚቃጠል መሥዋዕት
እንዲሆንልህ አንድ አውራ በግ፣ ወስደህ፣
በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት አቅርባቸው፤ ሁለ
ቱም እንከን የሌለባቸው ይሁኑ፡፡ [3]እስራ
ኤላውያንንም እንዲህ በላቸው፤ 'ለኀጢአት
መሥዋዕት አንድ አውራ ፍየል፣ ለሚቃጠል
መሥዋዕት እንከን የሌለባቸውን የአንድ
ዓመት እምቦሳና የአንድ ዓመት ጠቦት፣
[4]ለኅብረት መሥዋዕት[ለ] አንድ በሬና[ሐ] አንድ
አውራ በግ በዘይት ከተለወሰ የእህል ቍር
ባን ጋር በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት ለመሠ
ዋት አቅርቡ፤ እግዚአብሔር (ያህዌ) ዛሬ ይገ
ለጥላችኋልና፡፡' "

[5]እነርሱም ሙሴ ያዘዛቸውን ሁሉ ወደ
መገናኛው ድንኳን ደጃፍ አመጡ፤ ሕዝቡም
በሙሉ ቀርበው በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት
ቆሙ፡፡ [6]ሙሴም፣ "የእግዚአብሔር (ያህዌ)
ክብር ይገለጥላችሁ ዘንድ፣ እንድታደርጉት
እግዚአብሔር (ያህዌ) ያዘዛችሁ ይህ ነው"
አለ፡፡

[7]ሙሴ አሮንን፣ ወደ መሠዊያው ቀር
በህ የኀጢአት መሥዋዕትህንና የሚቃጠ
ለውን መሥዋዕትህን ሠዋ፤ ለራስህና ለሕ
ዝቡም አስተሰርይ፤ እግዚአብሔርም (ያህዌ)
ባዘዘው መሠረት የሕዝቡን መሥዋዕት
አቅርብ፤ አስተሰርይላቸውም" አለው፡፡

[8]አሮንም ወደ መሠዊያው መጥቶ ስለ
ራሱ የኀጢአት መሥዋዕት የቀረበውን

[ሀ]31 ወይም ብዬ ባዘዝሁት
[ለ]4 በትውፊት የሰላም መሥዋዕት ይባላል፤ እንዲሁም ቍ 18፥22 ይመ፡፡
[ሐ]4 የዕብራይስጥ ቃል ተባዕትና እንስትን ሊያጠቃልል ይችላል፤ እንዲሁም ቍ 18፡19 ይመ

እምቦሳ ዐረደው። 9ልጆቹም ደሙን አመጡ
ለት፤ እርሱም ጣቱን በደሙ ውስጥ ነክሮ
የመሠዊያውን ቀንዶች ቀባ፤ የተረፈውንም
ደም በመሠዊያው ግርጌ አፈሰሰው። 10እግዚ
አብሔር (ያህዌ) ሙሴን ባዘዘው መሠረት የኀ
ጢአት መሥዋዕቱን ሥብ፣ ኵላሊቶቹንና
የጕበቱን ሽፋን በመሠዊያው ላይ አቃጠ
ለው፤ 11ሥጋውንና ቍርበቱንም ከሰፈሩ
ውጭ በእሳት አቃጠለው።

12ከዚህ በኋላ አሮን የሚቃጠለውን
መሥዋዕት ዐረደ፤ ልጆቹ ደሙን አቀበ
ሉት፤ እርሱም ደሙን በመሠዊያው ላይ
ዙሪያውን ረጨ። 13ልጆቹም የሚቃጠለ
ውን መሥዋዕት ብልት አንድ በአንድ፣
ጭንቅላቱን ሳይቀር አምጥተው ሰጡት፤
እርሱም በመሠዊያው ላይ አቃጠለው።
14የሆድ ዕቃውንና እግሮቹን አጥቦ በመ
ሠዊያው ላይ ካለው ከሚቃጠለው መሥዋ
ዕት በላይ አቃጠለ። 15አሮንም የሕዝቡን
መሥዋዕት አቀረበ፤ ስለ ሕዝቡ የኀጢአት
መሥዋዕት የሆነውን ፍየል ወስዶ ዐረደው፤
እንደ ፊተኛው ሁሉ ይህንም በኀጢአት
መሥዋዕትነት ሠዋው።

16የሚቃጠለውንም መሥዋዕት አምጥቶ
በሥርዐቱ መሠረት አቀረበው። 17የእህል
ቍርባኑን አመጣ፤ ከላዩም እፍኝ ሙሉ
ወስዶ ጧት ጧት ከሚቀርበው የሚቃጠል
መሥዋዕት በተጨማሪ በመሠዊያው ላይ
አቃጠለ።

18አሮንም ስለ ሕዝቡ የኅብረት መሥ
ዋዕት የቀረቡትን በሬውንና አውራ በጉን
ዐረደ፤ ልጆቹም ደሙን አመጡለት፤ እር
ሱም ደሙን በመሠዊያው ላይ ዙሪያውን
ረጨ። 19የበሬውንና የአውራ በጉን ሥብ:-
ላቱን፣ የሆድ ዕቃውን የሚሸፍነውን ሥብ፤
ኵላሊቶቹንና የጕበቱን ሽፋን፣ 20በፍር
ምባዎቹ ላይ አስቀመጡ፤ አሮንም ሥቡን
በመሠዊያው ላይ አቃጠለ፤ 21ፍርምባዎቹ
ንና የቀኝ ወርቹንም ሙሴ ባዘዘው መሠ
ረት፣ የመወዝወዝ መሥዋዕት አድርጎ በእ
ግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት ወዘወዘው።

22አሮንም እጆቹን ወደ ሕዝቡ ዘርግቶ
ባረካቸው፤ የኀጢአት መሥዋዕቱን፣ የሚ
ቃጠለውን መሥዋዕትና የኅብረቱን መሥ
ዋዕት ካቀረበ በኋላ ወረደ።

23ከዚህ በኋላ፣ ሙሴና አሮን ወደ መገ
ናኛው ድንኳን ገቡ፤ ከዚያ ሲወጡም ሕዝ
ቡን ባረኩ፤ የእግዚአብሔርም (ያህዌ) ክብር
ለሕዝቡ ሁሉ ተገለጠ። 24እሳት ከእግዚ
አብሔር (ያህዌ) ዘንድ ወጥቶ፣ በመሠዊያው
ላይ የነበረውን በላ፤ ሕዝቡም ሁሉ ይህን
ባዩ ጊዜ እልል አሉ፤ በግምባራቸውም
ተደፉ።

9፥9 ቈ12፡18፤
ዘፀ29፥12፤ሕዝ43፥20
9፥11 ዘሌ4፥11፡12
9፥12 ቍ9፤
ዘሌ10፥19
9፥13 ዘሌ1፥8
9፥14 ዘሌ1፥9
9፥15 ዘሌ4፥27-31
9፥16 ዘሌ1፥1-13
9፥17 ዘሌ3፥5
9፥18 ዘሌ3፥1-11
9፥21 ዘፀ29፥24፡26
9፥22 ዘፍ48፥20፤
ዘፀ39፥43፤
ሉቃ24፥50
9፥23 ዘፀ40፥2፤
24፥16
9፥24 ዘፀ19፥18፤
መሳ6፥21፤13፥20፤
1ነገ18፥39
10፥1 ቍ2፤
ዘፀ6፥23፤24፥1፤
28፥1፤30፥9፤
ዘሌ16፥1፡12፤
ዘኍ3፥2-4፤
ዘኍ11፥1፤16፥7፡18፡
35፡46፤26፥61፤
1ነገ7፥50፤2ነገ25፥15
1ዜና6፥3፤2ዜና4፥22
ኤር52፥19፤
ኢሳ6፥6፤ሕዝ8፥11
10፥2 ዘፍ19፥24፤
38፥7፤ዘኍ11፥1፤
16፥35፤1ዜና24፥2፤
ኢዮ1፥16፤
መዝ2፥12፤50፥3፤
106፤18፤ኢሳ29፥6
10፥3 ዘፀ14፥4፤
19፥22፤30፥29፤
ዘሌ21፥6፤22፥32፤
ዘኍ16፥5፤20፥13፤
ኢሳ5፥16፤44፥23፤
49፥3፤55፥5፤
60፥21፤ሕዝ28፥22፤
38፥16
10፥4 ዘፀ6፥18፡22፤
25፥8፤ሐሥ5፥6፡9፡10
10፥5 ዘሌ8፥13
10፥6 ዘፍ50፥3፡
10፤ዘፀ6፥23፤
ዘሌ13፥45፤21፥10፤
ዘኍ1፥53፤5፥18፤
16፥22፤20፥29፤
ኢሱ7፥1፤22፥18፤
1ሳሙ 25፥1፤
ኤር41፥5፤
ማር14፥63
10፥7 ዘፀ25፥8፤
28፥41
10፥9 ዘፍ9፥21፤
ዘፀ12፥14፤29፥40፤
ዘሌ23፥13፤ዘኍ6፥3፤
15፥5፤ 28፥7፤
ዘዳ14፥26፤28፥39፤
29፥6፤ መሳ13፥4፤
ምሳ23፥29-35፤
31፥4፡7፤ኢሳ5፥22፤
22፥13፤28፥1፡7፤
29፥9፤56፥12፤
ኤር35፥6፤ሕዝ44፥21፤
ሆሴ4፥11፤ሚክ2፥11፤
ዕን2፥15-16፤
ሉቃ1፥15፤ኤፌ5፥18፤

## የናዳብና የአብዩድ መሞት

10 የአሮን ልጆች ናዳብና አብዩድ
እያንዳንዳቸው ጥናዎቻቸውን ወስ
ደው ፍም አደረጉባቸው፤ ዕጣንም ጨመሩባ
ቸው፤ እርሱ ያላዘዛቸውን፣ ያልተፈቀደውን
እሳት በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት አቀረቡ።
2ከዚህም የተነሣ እሳት ከእግዚአብሔር (ያህዌ)
ዘንድ ወጥቶ በላቸው፤ በእግዚአብሔርም (ያህዌ)
ፊት ሞቱ።

3ሙሴም አሮንን እንዲህ አለው፤ “እግዚ
አብሔር (ያህዌ):-
‘ወደ እኔ በሚቀርቡት መካከል፣
ቅድስናዬን እገልጣለሁ፤
በሕዝቡም ሁሉ ፊት፣
እከበራለሁ’ ብሎ የተናገረው ይህን ነው።”
አሮንም ዝም አለ።

4ሙሴ የአሮንን አጎት የዑዝኤልን ልጆች
ሚሳኤልንና ኤልጻፋንን ጠርቶ፣ “ወደዚህ
ኑና ወንድሞቻችሁን አንሡ፤ ከመቅደሱም
ደጃፍ አርቃችሁ፣ ከሰፈር ወደ ውጭ
ውሰዷቸው” አላቸው። 5እነርሱም መጥተው
ሙሴ ባዘዛቸው መሠረት፣ ሟቾቹ የክህ
ነት ቀሚሳቸውን እንደ ለበሱ ተሸክመው
ከሰፈር ወደ ውጭ አወጧቸው።

6ሙሴም አሮንንና የአሮንን ልጆች፣
አልዓዛርንና ኢታምርን እንዲህ አላቸው፤
“እንዳትሞቱ፣ በሕዝቡም ላይ ቍጣ እንዳ
ይመጣ ጠጕራችሁን አትንጩ፤[ሠ] ልብሳች
ሁንም አትቅደዱ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር
(ያህዌ) በእሳት ስላጠፋቸው ሰዎች ወንድሞ
ቻችሁ እስራኤላውያን ሊያለቅሱላቸው ይች
ላሉ። 7የእግዚአብሔር (ያህዌ) የመቅቢያ ዘይት
በላያችሁ ነውና እንዳትሞቱ ከመገናኛው
ድንኳን አትውጡ።” እነርሱም ሙሴ እንዳ
ላቸው አደረጉ።

8እግዚአብሔርም (ያህዌ) አሮንን እንዲህ
አለው፤ 9“እንዳትሞቱ አንተና ልጆችህ ወደ
መገናኛው ድንኳን በምትገቡበት ጊዜ
የወይን ጠጅ ወይም ሌላ የሚያሰክር መጠጥ
አትጠጡ፤ ይህም በልጅ ልጃችሁ ዘንድ
የሚጠበቅ ዘላለማዊ ሥርዐት ነው። 10የተቀ
ደሰውንና ያልተቀደሰውን፣ ርኩሱንና
ንጹሑን ለዩ፤ 11እግዚአብሔርም (ያህዌ) በሙሴ
አማካይነት የሰጣቸውን ሥርዐት ሁሉ ለእ
ስራኤላውያን አስተምሩ።

12ሙሴም አሮንንና የተረፉትን ልጆቹን

1ጢሞ3፥3፤ቲቶ1፥17 10፥10 ዘፍ7፥2፤ ዘሌ6፥27፤14፥57፤
20፥25፤ሕዝ22፥26 10፥11 ዘዳ17፥10፡ 11፤24፥8፤25፥1፤
33፥10፤2ዜና15፥3፤ 17፥7፤ዕዝ7፥25፤ ነህ8፥7፤ምሳ4፥27፤
ሐጌ2፥11፤ሚል2፥7 10፥12 ዘፀ29፥41፤ ዘሌ6፥14-18

[ሠ]6 ወይም አትላጩ

አልዓዛርንና ኢታምርን እንዲህ አላቸው፤
“በእሳት *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) ከቀረበው
የእህል ቊርባን የቀረውን ወስዳችሁ ያለ
እርሾ ጋግሩት፤ እጅግ ቅዱስ ስለሆነ በመ
ሠዊያው አጠገብ ብሉት፤ 13*ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) በእሳት ከሚቀርበው *መሥዋዕት* ያን
ተና የልጆችህ ድርሻ ይህ ስለሆነ፣ በተቀደሰ
ስፍራ ብሉት፤ እንዲህ ታዝዣለሁና። 14ከእ
ስራኤላውያን የኅብረት *መሥዋዕት*[o] ላይ
የእናንተ ድርሻ ሆኖ ስለተሰጠ፣ የተወዘወዘ
ውን ፍርምባና የቀረበውን ወርች አንተ፣
ወንዶችና ሴቶች ልጆችህ በአምልኮው
*ሥርዐት መሠረት* ንጹሕ በሆነ ስፍራ ብሉት።
15የቀረበውን ወርችና የተወዘወዘውን ፍርምባ
*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) *ፊት የመወዝወዝ
መሥዋዕት* ሆኖ በእሳት ከቀረበው *ሥብ*
*ጋር* ይምጣ። ይህም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ባዘ
ዘው *መሠረት* ለአንተና ለልጆችህ ለዘላ
ለም የተመደበ ድርሻ ይሆናል።”

16ሙሴ ለኀጢአት *መሥዋዕት* የሚቀ
ርበውን ፍየል አጥብቆ ፈለገ፤ *መቃጠሉንም*
በተረዳ ጊዜ የተረፉትን የአሮንን ልጆች
አልዓዛርንና ኢታምርን ተቈጣቸው፤ እንዲ
ህም አላቸው፤ 17“የኀጢአት *መሥዋዕቱን*
ለምን በተቀደሰው ስፍራ አልበላችሁትም?
እጅግ የተቀደሰ ነው፤ *በእግዚአብሔር*
(ያህዌ) *ፊት* ስርየት በማስገኘት የሕዝቡን ኀጢ
አት እንድታስወግዱበት የተሰጣችሁ ነበር፤
18ደሙ ወደ ተቀደሰው ስፍራ ስላልገባ፣
በሰጠሁት ትእዛዝ *መሠረት* ፍየሉን በተቀ
ደሰው ስፍራ መብላት ይገባችሁ ነበር።”

19አሮንም ሙሴን፣ “እነሆ፤ በዛሬው ቀን
የኀጢአት *መሥዋዕታቸውንና* የሚቃጠል
*መሥዋዕታቸውን በእግዚአብሔር* (ያህዌ) *ፊት*
አቀረቡ፤ እኔም እንዲህ ያለ ነገር የደረሰብኝ
ሰው ነኝ፤ ታዲያ፣ ዛሬ የኀጢአት *መሥዋዕ
ቱን* ብበላ ኖሮ *እግዚአብሔርስ* (ያህዌ) ደስ
ይለው ኖሮአልን?” አለው። 20ሙሴም ይህን
በሰማ ጊዜ መልሱ አረካው።

### የተፈቀደና ያልተፈቀደ መብል
11፥1-23 ተጓ ምብ ዘዳ 14፥3-20

11 *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴንና አሮንን
እንዲህ አላቸው፤ 2“እስራኤላውያንን
እንዲህ በሏቸው፤ ‘በየብስ ከሚኖሩ እንስሳት
ሁሉ የምትበሏቸው እነዚህ ናቸው፦ 3ሰኰ
ናው የተሰነጠቀውን የሚያመሰኳውን ማንኛ
ውንም እንስሳ መብላት ትችላላችሁ።

4“ ‘የሚያመሰኩ ሆነው ሰኰናቸው ያልተ
ሰነጠቀ ወይም ሰኰናቸው የተሰነጠቀ ሆኖ
የማያመሰኩትን አትብሉ፤ ግመል ያመሰ
ኳል፤ ሰኰናው ስላልተሰነጠቀ ግን በእና
ንተ ዘንድ ርኩስ ይሁን። 5ሽኮኮ ያመስ
ኳል፤ ሰኰናው ስላልተሰነጠቀ ግን በእናንተ
ዘንድ ርኩስ ይሁን። 6ጥንቸል ያመሰኳል፤
ሰኰናው ስላልተሰነጠቀ ግን በእናንተ ዘንድ
ርኩስ ይሁን። 7ዐሳማ ሰኰናው የተሰነጠቀ
ቢሆንም ስለማያመሰኳ በእናንተ ዘንድ
ርኩስ ይሁን። 8የእነዚህን እንስሳት *ሥጋ*
አትብሉ፤ ጥንባቸውንም አትንኩ፤ በእና
ንተ ዘንድ ርኩሶች ይሁኑ።

9“ ‘በባሕሮችና በወንዞች ውሃ ውስጥ
ከሚኖሩት ፍጡሮች ክንፍና ቅርፊት ያላቸ
ውን መብላት ትችላላችሁ፤ 10ነገር ግን
በባሕሮችና በወንዞች ውስጥ ከሚኖሩት
ፍጡሮች ሁሉ፣ ከሚንፏቀቁት ወይም በውሃ
ውስጥ ከሚኖሩት ሕይወት ካላቸው ሌሎች
ፍጡሮች *መካከል* ክንፍና ቅርፊት የሌላቸው
በእናንተ ዘንድ አስጸያፊዎች ይሁኑ፤ 11በእና
ንተ ዘንድ አስጸያፊ ስለ ሆኑ *ሥጋቸውን*
አትብሉ፤ በድናቸውንም ተጸየፉላችሁ፤
12ክንፍና ቅርፊት የሌለው ማንኛውም በውሃ
ውስጥ የሚኖር ፍጡር በእናንተ ዘንድ
አስጸያፊ ይሁን።

13“ ‘ከአዕዋፍ ወገን እነዚህን ትጸየፉላ
ችሁ፤ ጸያፍ ስለሆኑም አትብሏቸው፦ ንስር፣
ጥንብ አንሣ፣ ግልገል አንሣ፣ 14ጭላት፣ ማን
ኛውም ዐይነት ጭልፊት፣ 15ማንኛውም
ዐይነት ቁራ፣ 16ሰጐን፣ ጠላቋ፣ ዝይ፣ ማንኛ
ውም ዐይነት በቋል፣ 17ጉጉት፣ ርኩም፣
ጋጋኖ፣ 18የውሃ ዶሮ፣ ይብራ፣ ስደተኛ
አሞራ፣ 19ሽመላ፣ ማንኛውም ዐይነት ሳቢሳ፣
ጅንጁላቴ ወፍና የሌሊት ወፍ።[ǁ]

20“ ‘ክንፍ ኖሮአቸው በአራት እግር የሚ
ንቀሳቀሱ ነፍሳት ሁሉ በእናንተ ዘንድ አስ
ጸያፊዎች ይሁኑ። 21ነገር ግን ክንፍ ኖሮ
አቸው በአራት እግር ከሚንቀሳቀሱ ነፍሳት
*መካከል* ከምድር በሚፈናጠሩበት እግራቸው
አንጓ ያለባቸውን መብላት ትችላላችሁ።
22ከእነዚህ ማንኛውንም ዐይነት አንበጣ፣
ፌንጣና ኵብኵባ መብላት ትችላላችሁ።
23ነገር ግን ክንፍ ኖሮአቸው በአራት እግር
የሚንቀሳቀሱትን ፍጥረታት ተጸየፏቸው።

24“ ‘ከእነዚህ የተነሣ ትረክሳላችሁ፤ የእነ
ዚህን በድን የሚነካ ሁሉ እስከ ማታ ድረስ
ርኵስ ይሆናል። 25የእነዚህንም በድን የሚ
ያነሣ ሰው ሁሉ ልብሱን ይጠብ፤ ሆኖም
እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ነው።

26“ ‘ሰኰና ያለው፣ ነገር ግን ሰኰናው
ያልተሰነጠቀና የማያመሰኳ ማንኛውም እንስሳ
በእናንተ ዘንድ ርኩስ ይሁን። የእነዚህንም
በድን የሚነካ ሰው ሁሉ ይረክሳል። 27አራት

10፥13 ዘሌ6፥16፤ ሕዝ42፥13
10፥14 ዘፀ29፥31፤ ዘሌ4፥12፤ዘኍ5፥9
10፥15 ዘፀ29፥28፤ ዘሌ7፥34፤
10፥16 ዘሌ9፥3
10፥17 ዘፀ28፥38፤ ዘሌ6፥24-30፤ ሕዝ42፥13
10፥18 ዘሌ4፥18፤ 6፥17፡26
10፥19 ዘሌ9፥12
11፥2 ሐሥ10፥12-14
11፥4 ሐሥ10፥14
11፥7 ኢሳ65፥4፤ 66፥3፡17
11፥8 ዘሌ5፥2፤ ዕብ9፥10
11፥10 ቍ12
11፥11 ዘሌ5፥2
11፥12 ቍ10
11፥14 ዘፍ1፥11
11፥15 ዘፍ8፥7
11፥18 ኢሳ13፥21፤ 14፥23፤34፥11፡13፤ ሰፎ2፥14
11፥19 ዘፍ1፥11፤ ኢሳ2፥20፤ዘካ5፥9
11፥20 ሐሥ10፥14
11፥22 ማቴ3፥4፤ ማር1፥6
1፥24 ቍ27-40፤ ዘሌ5፥2፤13፥3፤14፥4 6፤15፥5፤22፥6፤ ዘኍ19፥7፡19
11፥25 ቍ28፤ ዘፀ19፥10፤ዘሌ13፥6፡ 34፤14፥8፡47፤15፥5፤ 16፥26፤ዘኍ8፥7፤ 19፥7፡8፤31፥24

[o]14 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል
[ǁ]19 በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ያሉ የእያንዳንዱ አዕዋፍ፣ ነፍሳትና እንስሳት ትክክለኛ ማንነታቸው በትክክል አይታወቅም

እግር ካላቸው እንስሳት ሁሉ በመዳፋቸው
የሚሄዱት በእናንተ ዘንድ ርኩሳን ናቸው፤
በድናቸውንም የሚነካ ሁሉ እስከ ማታ
ድረስ ርኵስ ይሆናል። 28የእነዚህን በድን
የሚያነሣ ሰው ልብሱን ይጠብ፤ ሆኖም
እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ይሆናል፤ እንስሳ
ቱም በእናንተ ዘንድ ርኵሳን ናቸው።

29“ ‘ምድር ለምድር ከሚንቀሳቀሱ እን
ስሳት መካከል እነዚህ በእናንተ ዘንድ ርኩ
ሳን ናቸው፦ ሙጭልጭላ፣ ዐይጥ፣ እን
ሽላሊት በየወገኑ፣ 30ዔሊ፣ ዐዞ፣ ገበሎ፣
አርጃኖ፣ ዕሥሥት። 31ምድር ለምድር ከሚ
ንቀሳቀሱ እንስሳት ሁሉ መካከል እነዚህ
በእናንተ ዘንድ ርኩሳን ናቸው፤ ከእነዚህም
የሞተውን የሚነካ ሁሉ እስከ ማታ ድረስ
ርኩስ ይሆናል። 32በድኑ በማንኛውም ዕቃ
ላይ ቢወድቅ ያ ዕቃ ከዕንጨት፣ ከጨርቅ፣
ከቈዳ ወይም ከበርኖስ የተሠራ ቢሆን
ርኩስ ይሆናል፤ በውሃ ውስጥ ይደረግ፤
ሆኖም ርኩስ ነው፤ ከዚያም በኋላ ንጹሕ
ይሆናል። 33በድኑም በሸክላ ዕቃ ውስጥ
ቢወድቅ፣ በውስጡ ያለ ነገር ሁሉ ርኩስ
ስለሚሆን ዕቃውን ስበሩት። 34ማንኛውም
ምግብ እንዲህ ካለው ዕቃ ውሃ ቢፈስበት
ይረክሳል፤ ከዚህ ዕቃ የሚጠጣውም ነገር
ሁሉ ርኵስ ነው፤ 35ከበድናቸው አንዱ
የወደቀበት ነገር ሁሉ ይረክሳል፤ ምድጃም
ይሁን ማሰሮ ይሰበር፤ ርኩሳን ናቸው፤
እናንተም ተጸየፏቸው። 36ነገር ግን ምንጭ
ወይም የውሃ ማጠራቀሚያ ጕድጓድ ንጹሕ
እንደ ሆነ ይቈያል፤ ሆኖም በድኑን የነካ
ይረክሳል። 37በሚዘራ ዘር ላይ በድን ቢወ
ድቅ ዘሩ ንጹሕ እንደሆነ ይቆያል። 38ነገር
ግን በዘሩ ላይ ውሃ ከፈሰሰበት በኋላ በድን
ቢወድቅበት ዘሩ በእናንተ ዘንድ ርኩስ
ነው።

39“ ‘እንድትበሉ ከተፈቀደላችሁ እንስ
ሳት አንዱ ቢሞት፣ በድኑን የሚነካ ማንኛ
ውም ሰው እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ይሆ
ናል። 40ማንም ሰው ከበድኑ ቢበላ ልብሱን
ይጠብ፤ ሆኖም እስከ ማታ ድረስ ርኩስ
ነው፤ በድኑን የሚያነሣ ልብሱን ይጠብ፤
ሆኖም እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ይሆናል።

41“ ‘ምድር ለምድር የሚንቀሳቀስ ማንኛ
ውም ፍጡር ጸያፍ ነው፤ አይበላም። 42ምድር
ለምድር የሚንቀሳቀሰውን ፍጡር ሁሉ፣
ይኸውም በደረቱ የሚሳበውን ወይም በአራት
እግር የሚሄደውን ወይም ብዙ እግሮች
ያሉትን አትብሉ፤ ጸያፍ ነው። 43በእነዚህ
ፍጡራን ሁሉ ራሳችሁን አስጸያፊ አታድ
ርጉ፤ በእነርሱም ራሳችሁን በማጕደፍ አት
ርከሱ። 44እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ (ያህዌ

11፥28 ዕብ9፥10
11፥29 ቆላ41፤
ኢሳ66፥17
11፥32 ዘሌ15፥12፤
ዘኍ19፥18፤31፥20
11፥33 ዘሌ6፥28
11፥39 ቆላ40፤
ዘሌ17፥15፤22፥4፡8፤
ዘኍ19፥11፤ዘዳ14፥21፤
ሕዝ4፥14፤44፥31
11፥40 ቆላ25፡39፤
ዘሌ14፥8፤17፥15፤
22፥8፤ሕዝ44፥31፤
ዕብ9፥10
11፥43 ቆላ44፤
ዘሌ20፥25፤22፥5
11፥44 ቆላ43፤
ዘፀ6፥2፡7፤19፥10፤
20፥2፤22፥31፤31፥13
ዘሌ19፥2፤20፥7፤
ዘኍ15፥40፤ዘዳ14፥2
ኢሱ3፥5፤ 7፥13፤
24፥19፤ 1ሳሙ2፥2፤
1ዜና15፥12፤
2ዜና29፥5፤35፥6፤
ኢዮ6፥10፤
መዝ99፥3፤ኢሳ43፥3፤
51፥15፤ሕዝ20፥5፤
ኤፌ1፥4፤1ተሰ4፥7፤
1ጴጥ1፥15፡16
11፥45 ዘፍ17፥7፤
ዘፀ19፥6፤ዘሌ25፥38፡
55፤1ጴጥ1፥16
11፥47 ዘሌ10፥10
12፥2 ዘሌ15፥19፤
18፥19፤ኢሳ64፥6፤
ሕዝ18፥6፤22፥10፤
36፥17
12፥3 ዘፍ17፥10፤
ዘፀ22፥30፤ሉቃ1፥59
12፥6 ዘፀ29፥38፤
ዘሌ5፥7፤23፥12፤
ዘኍ6፥12፡14፤7፥15፤
ሉቃ2፥22
12፥8 ዘፍ15፥9፤
ዘሌ4፥26፤5፥7፤
14፥22፤ሉቃ2፥22-24
13፥2 ቆላ3፡4፡9፡
10፡15፡19፡28፡38፡
39፡43፤ዘፀ4፥6፤
ዘሌ14፥3፡32፡56፤
ዘኍ5፥2፤ዘዳ24፥8

ኤሎሂም) ቅዱስ ነኝና እናንተም ተለዩ፤ ቅዱሳንም
ሁኑ፤ ምድር ለምድር በሚንቀሳቀስ በማን
ኛውም ፍጡር ራሳችሁን አታርክሱ። 45አምላ
ካችሁ (ኤሎሂም) እሆን ዘንድ ከግብፅ ምድር
ያወጣኋችሁ እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ፤
ስለዚህ እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን
ሁኑ።

46“ ‘እንስሳትንና አዕዋፍን፣ በውሃ ውስጥ
የሚኖሩትንና ምድር ለምድር የሚንቀሳቀ
ሱትን ፍጥረታት ሁሉ በሚመለከት የተሰጠ
ሕግ ይህ ነው። 47በዚህም በርኩሱና በንጹሑ
መካከል፣ እንዲሁም ሕይወት ካላቸው ፍጡ
ራን የሚበሉትንና የማይበሉትን ትለያላ
ችሁ።’ ”

## ከወሊድ በኋላ የመንጻት ሥርዐት

12 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2“እስራኤላውያንን እንዲህ
በላቸው፤ ሴት አርግዛ ወንድ ልጅ በምትወ
ልድበት ጊዜ፣ ልክ እንደ ወር አበባዋ ጊዜ
እስከ ሰባት ቀን ትረክሳለች። 3ሕፃኑም
በስምንተኛው ቀን ይገረዝ። 4ሴትዮዋም
ከደሟ እስክትነጻ ድረስ ሠላሳ ሦስት ቀን
ትቆይ፤ የመንጻቷም ወራት እስኪፈጸም
ድረስ ማንኛውንም የተቀደሰ ነገር አትንካ፤
ወደ ቤተ መቅደስም አትግባ። 5ነገር ግን
የወለደችው ሴት ልጅ ከሆነ፣ እንደ ወር
አበባዋ ጊዜ ሁለት ሳምንት ትረክሳለች፤
ከዚያም ከደሟ እስክትነጻ ስድሳ ስድስት
ቀን ትቆይ።

6“ ‘ሴትዮዋ ወንድ ወይም ሴት ልጅ
ዋን ወልዳ የመንጻትዋ ጊዜ ሲፈጸም፣ ለሚ
ቃጠል መሥዋዕት የአንድ ዓመት ጠቦት፣
ለኀጢአት መሥዋዕት አንድ የዋኖስ ጫጩት
ወይም አንድ ርግብ ወደ መገናኛው ድንኳን
ደጃፍ ወስዳ ካህኑ ዘንድ ታቅርብ። 7ካህኑም
በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት ያቅርበው፤ ያስተ
ሰርይላትም፤ ሴትዮዋም ከደሟ ፈሳሽ ትነ
ጻለች።

“ ‘ሴትዮዋ ወንድ ወይም ሴት ብትወልድ
ሕጉ ይኸው ነው። 8ጠቦት ለማምጣት ዐቅ
ምዋ ካልፈቀደ፣ ሁለት ርግቦች ወይም
ሁለት የዋኖስ ጫጩቶች፣ አንዱ ለሚቃጠል
መሥዋዕት፣ ሌላው ደግሞ ለኀጢአት መሥ
ዋዕት ታቅርብ፤ በዚህም ካህኑ ያስተሰርር
ይላታል፤ እርሷም ትነጻለች።’ ”

## ተላላፊ የቈዳ በሽታ

13 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴንና አሮንን
እንዲህ አላቸው፤ 2“ማንኛውም ሰው
በሰውነቱ ቈዳ ላይ ዕብጠት ወይም ችፍታ
ቋቍቻ ቢወጣበትና ይህም ወደ ተላላፊ

የቈዳ በሽታ[ሠ] የሚለወጥበት ከሆነ፣ ወደ
ካህኑ አሮን ወይም ካህናት ከሆኑት ልጆቹ[የ]
ወደ አንዱ ያምጡት። [3]ካህኑም በሰውየው
ቈዳ ላይ ያለውን ቍስል ይመርምር፤
በቍስሉ በተበከለው አካባቢ ያለው ጠጕር
ወደ ነጭነት ተለውጦ ቢያገኘውና ቦታው
ጐድጕዶ[ደ] ወደ ውስጥ ቢገባ፣ ይህ ተላላፊ
የቈዳ በሽታ ነው። ካህኑም መርምሮ ይህን
ባወቀ ጊዜ፣ ሰውየው በአምልኮው ሥርዐት
መሠረት ርኩስ መሆኑ ይገለጽ። [4]በቈዳው
ላይ ያለው ቋቁቻ ነጭ ሆኖ ቢታይ ነገር
ግን ከቈዳው በታች ዘልቆ ባይገባና በቦ
ታው ላይ የሚገኘው ጠጕር ወደ ነጭነት
ባይለወጥ፣ ካህኑ በሽተኛውን ሰባት ቀን
ያግልለው። [5]በሰባተኛውም ቀን ካህኑ በሽ
ተኛውን ይመርምረው፤ ቍስሉ ለውጥ ካላ
መጣና በቈዳውም ላይ ካልተስፋፋ እንደገና
ሰባት ቀን ያግልለው። [6]በሰባተኛው ቀን
ካህኑ እንደገና ይመርምረው፤ ቍስሉ ከከሰ
መና በቈዳው ላይ ካልተስፋፋ፣ ካህኑ
ሰውየው ንጹሕ መሆኑን ያስታውቅ፤ ቍስሉ
ችፍታ እንጂ ሌላ አይደለም። ሰውየው ልብ
ሱን ይጠብ፤ ንጹሕም ይሆናል። [7]ራሱን ለካ
ህን አሳይቶ መንጻቱ ከታወቀ በኋላ፣ ችፍ
ታው በቈዳው ላይ እየተስፋፋ ከሆነ፣
እንደ ገና ካህኑ ፊት ይቅረብ፤ [8]ካህኑም
ይመርምረው፤ ችፍታው በቈዳው ላይ ተስፋ
ፍቶ ከተገኘ ካህኑ ሰውየው ርኩስ መሆ
ኑን ያስታውቅ፤ ተላላፊ የቈዳ በሽታ ነው።

[9]"ማንኛውም ሰው ተላላፊ የቈዳ በሽታ
ከያዘው፣ ወደ ካህኑ ያምጡት፤ [10]ካህኑም
ይመርምረው፤ በሰውነቱ ላይ ጠጕሩን ወደ
ነጭነት የለወጠ ነጭ ዕባጭ ካለና በዕብ
ጠቱም ውስጥ ቀይ ሥጋ ቢታይ፣ [11]ሥር
የሰደደ የቈዳ በሽታ ነውና ሰውየው ርኩስ
መሆኑን ካህኑ ያስታውቅ፤ ርኩስ መሆኑ
ግልጽ ስለ ሆነም ሰውየውን አያግልለው።

[12]"ደዌው በአካላቱ ሁሉ ላይ በመውጣት
በሽተኛውን ከራስ ጠጕር እስከ እግር ጥፍር
ያለበሰው መሆኑን ካህኑ እስካየ ድረስ፣
[13]ካህኑ ይመርምረው፤ ደዌው የሰውየውን
ሰውነት ሙሉ በሙሉ ሸፍኖት ከተገኘ፣ ያ
ሰው ንጹሕ መሆኑን ያስታውቅ፤ ሙሉ
በሙሉ ነጭ ስለ ሆነ ንጹሕ ነው። [14]ነገር
ግን ቍስሉ አመርቅዞ ቀይ ሥጋ ቢታይበት
ርኩስ ይሁን። [15]ካህኑም የተገለጠውን ቀይ
ሥጋ በሚያይበት ጊዜ ርኩስ መሆኑን ያስ
ታውቅ፤ ቀይ ሥጋ ርኩስ ስለ ሆነ፣ ተላ
ላፊ በሽታ ነው። [16]ቀይ ሥጋ ተለውጦ
ከነጣ ግን ወደ ካህኑ ይሂድ፤ [17]ካህኑም
ይመርምረው፤ ቍስሎች ወደ ነጭነት ተለ
ውጠው ከተገኙ፣ የታመመው ሰው ንጹሕ
መሆኑን ካህኑ ያስታውቅ፤ ንጹሕም ይሆናል።

13፥3 ቍ8:11: 20:30፤ዘሌ21፥1፤ ዘኍ9፥6
13፥4 ቍ2:5:21: 26:33:46፤ዘሌ14፥38 ዘኍ12፥14:15፤ ዘዳ24፥9
13፥5 ቍ27:32: 34:51፤ዘሌ14፥9
13፥6 ቍ13:17: 23:28:34፤ዘሌ11፥25 ፤14፥8:9:20፤ 48፤15፥8፤ዘኍ8፥7፤ ማቴ8፥3፤ ሉቃ5፥12-14
13፥7 ሉቃ5፥14
13፥11 ዘፀ4፥6፤ ዘሌ14፥8፤ዘኍ12፥10 ማቴ8፥2
13፥15 ቍ2
13፥17 ቍ6
13፥18 ዘፀ9፥9
13፥19 ቍ2:24: 42፤ዘሌ14፥37
13፥20 ቍ2
13፥23 ቍ6
13፥25 ቍ11
13፥26 ቍ4
13፥27 ቍ5
13፥28 ቍ2
13፥29 ቍ43:44
13፥31 ቍ4

[18]"አንድ ሰው በገላው ላይ ዕባጭ ወጥቶ
ቢድን፣ [19]ዕባጩ በነበረበት ቦታ ላይም
ነጭ ዕብጠት ወይም ነጣ ያለ ቀይ ቋቍቻ
ቢታይ፣ ካህኑ ዘንድ ይቅረብ። [20]ካህኑም
ይመርምረው፤ ከቈዳው በታች ዘልቆ የገባ
ቢሆን በቦታውም ያለው ጠጕር ቢነጣ፣
ሰውየው ርኩስ መሆኑን ካህኑ ያስታውቅ።
[21]ነገር ግን ካህኑ በሚመረምርበት ጊዜ ነጭ
ጠጕር በውስጡ ከሌለ፣ ዘልቆ ካልገባና
የከሰመ ቢሆን፣ ካህኑ ሰባት ቀን ያግልለው።
[22]በቈዳው ላይ ተስፋፍቶ ካገኘውም፣ ርኩስ
መሆኑን ካህኑ ያስታውቅ፤ የሚተላለፍ ነው።
[23]ቋቍቻው ግን ባለበት ከቈየና ወደ ሌላ
ስፍራ ካልተስፋፋ፣ የዕባጩ ጠባሳ እንጂ
ሌላ አይደለም፤ ካህኑም ንጹሕ መሆኑን
ያስታውቅ።

[24]"አንድ ሰው እሳት ቈዳውን ቢያቃ
ጥለውና በተቃጠለው ስፍራ ነጣ ያለ ቀይ
ወይም ነጭ ቋቍቻ ቢታይበት፣ [25]ካህኑ
ይመርምረው፤ ቋቍቻው ባለበትም ቦታ
ያለው ጠጕር ቢነጣና ከቈዳው በታች
ዘልቆ ቢገባ፣ በቃጠሎው ሰበብ ከውስጥ
የወጣ ተላላፊ በሽታ ነው፤ ሰውየው ርኩስ
መሆኑን ካህኑ ያስታውቅ፤ ተላላፊ የቈዳ
በሽታ ነው። [26]ነገር ግን ካህኑ በሚመ
ረምርበት ጊዜ ነጭ ጠጕር የሌለበት፣
ከቈዳውም በታች ዘልቆ ያልገባና የከሰመ
ቢሆን፣ ካህኑ ሰውየውን ሰባት ቀን ያግል
ለው። [27]በሰባተኛው ቀን ካህኑ ይመርም
ረው፤ በሽታውም በቈዳው ላይ ተስፋፍቶ
ቢያገኘው፣ ሰውየው ርኩስ መሆኑን ካህኑ
ያስታውቅ፤ ተላላፊ የቈዳ በሽታ ነው።
[28]ቋቍቻ ባለበት ከቈየና በቈዳው ላይ
ካልተስፋፋ፣ ይልቁንም እየከሰመ ከሄደ፣
በቃጠሎው ሰበብ የተከሠተ ዕብጠት ነውና
ካህኑ ንጹሕ መሆኑን ያስታውቅ፤ የቃጠ
ሎው ጠባሳ እንጂ ሌላ አይደለም።

[29]"በወንድ ወይም በሴት ዐናት ወይም
አገጭ ላይ ቍስል ቢወጣ፣ [30]ካህኑ ቍስሉን
ይመርምር፤ ከቈዳው በታች ዘልቆ ከገባ፣
በውስጡም ያለው ጠጕር ቢጫና ቀጭን
ከሆነ ያ ሰው ርኩስ መሆኑን ካህኑ ያስታ
ውቅ፤ የሚያሳክክ የራስ ወይም የአገጭ
ተላላፊ በሽታ ነው። [31]ካህኑ እንዲህ ዐይነ
ቱን ቍስል በሚመረምርበት ጊዜ፣ ከቈዳው
በታች ዘልቆ ካልገባና በውስጡም ጥቍር
ጠጕር ከሌለ፣ ካህኑ ሰውየውን ሰባት ቀን

[ሠ]2 በልማድ ለምጽ ይባላል፤ የዕብራይስጡ ቃል ከቈዳ ጋር ለተያያዘ በሽታ ሁሉ የሚገባ ነው። በዚህ ምዕራፍ ሌላም ስፍራ ይገኛል።
[የ]2 ወይም *ዘሮቹ*
[ደ]3 ወይም *ከሌላው የቈዳ ክፍል ጠልቆ ቢገባ፤* በዚህ ምዕራፍ በሌላ ስፍራም ይገኛል።

ያግልለው። 32ካህኑም በሰባተኛው ቀን
ቊስሉን ይመርምር፤ የሚያሳክከው ቦታ
ያልሰፋ፣ ቢጫ ጠጕር የሌለውና ከቈዳው
በታች ዘልቆ ያልገባ ከሆነ፣ 33ከቈሰለው
ቦታ በስተቀር ጠጕሩን ይላጭ፤ ካህኑ ሰባት
ተጨማሪ ቀን ሰውየውን ያግልል። 34ካህኑ
በሰባተኛው ቀን የሚያሳክከውን የሰውየውን
ቊስል ይመርምር፤ በቈዳው ላይ ካልሰፋና
ከቈዳው በታች ዘልቆ ካልገባ ካህኑ ያ
ሰው ንጹሕ መሆኑን ያስታውቅ፤ ልብሱን
አጥቦ ንጹሕ ይሁን። 35ንጹሕ መሆኑ ከተገለጠ
በኋላ ግን የሚያሳክከው ቊስል ተስፋፍቶ
ቢገኝ፣ 36ካህኑ ይመርምረው፤ ቊስሉ
በቈዳው ላይ ከሰፋ፣ ካህኑ የጠጕሩን ቢጫ
መሆን አለመሆን ማየት አያሻውም፤ ሰው
የው ርኩስ ነው። 37ነገር ግን ቊስሉ በካህኑ
አመለካከት ለውጥ ያላሳየ ከሆነና በውስጡ
ጥቊር ጠጕር ካበቀለ ቊስሉ ድኖአል፤
ሰውየው ነጽቶአል፤ ካህኑም ንጹሕ መሆኑን
ያስታውቅ።

38"በወንድ ወይም በሴት ቈዳ ላይ
ቋቊቻ ቢወጣ፣ 39ካህኑ ይመርምራቸው፤
ቋቊቻው ዳለቻ ከሆነ በቈዳ ላይ የወጣ
ጕዳት የማያስከትል ችፍታ ነው፤ ሰውየውም
ንጹሕ ነው።

40"አንድ ሰው የራሱ ጠጕር ከዐናቱ
አልቆ መላጣ ቢሆን ንጹሕ ነው። 41ጠጕሩ
ከፊት ለፊት ተመልጦ ራሰ በራ ቢሆንም
ንጹሕ ነው። 42ነገር ግን በመላጣው ወይም
በበራው ላይ ነጣ ያለ ቀይ ቊስል ቢወ
ጣበት፣ ያ ከመላጣው ወይም ከበራው የወጣ
ተላላፊ በሽታ ነው። 43ካህኑ ይመርምረው፤
በመላጣው ወይም በበራው ላይ ያበጠው
ተላላፊ የቈዳ በሽታ የሚመስል ነጣ ያለ
ቊስል ከሆነ፣ 44ሰውየው ደዌ አለበት፤
ርኵስም ነው፤ በራሱ ላይ ካለው ቊስል
የተነሣም ሰውየው ርኩስ መሆኑን ካህኑ
ያስታውቅ።

45"እንዲህ ያለ ተላላፊ በሽታ ያለበት
ሰው የተቀደደ ልብስ ይልበስ፤ ጠጕሩን
ይግለጥ፤[፳] እስከ አፍንጫውም ድረስ ተሸፋ
ፍኖ 'ርኩስ ነኝ! ርኩስ ነኝ!' እያለ ይጮኽ።
46ተላላፊ በሽታው እስካለበት ጊዜ ድረስ
ርኩስ ነው፤ ብቻውን ይቀመጥ፤ ከሰፈር
ውጪም ይኑር።

## በልብስ ላይ የሚታይ ተላላፊ በሽታ

47"ከበግ ጠጕር ወይም ከበፍታ የተሠራ
ማንኛውም ዐይነት ልብስ በተላላፊ በሽታ
ቢበከል፣ 48በሸማኔ ዕቃ ወይም በእጅ የተ
ሠራ ማንኛውም ዐይነት የበግ ጠጕር ወይም
የበፍታ ልብስ፣ ወይም ማንኛውም ቈዳ
ወይም ከቈዳ የተሠራ ነገር ቢሆን፣ 49በል
ብስ ወይም በዐጐዛ፣ በሸማኔ ዕቃ በተሠራ
ወይም በእጅ በተጠለፈ ወይም ከቈዳ በተ
ሠራ ዕቃ ላይ አረንጓዴ ወይም ቀይ መሳይ
ደዌ ቢከሠት፣ እየሰፋ የሚሄድ ተላላፊ
በሽታ ስለ ሆነ ካህኑ ይየው። 50ካህኑ ደዌውን
ይመርምር፤ በደዌ የተበከለውንም ዕቃ
ሰባት ቀን ያግልል። 51በሰባተኛውም ቀን
ይመርምረው፤ ደዌው በልብሱ፣ በሸማኔ ዕቃ
በተሠራው ወይም በእጅ በተጠለፈው ጨርቅ
ወይም ለማናቸውም አገልግሎት በሚውል
ዐጐዛ ላይ ተስፋፍቶ ቢገኝ፣ ክፉ ደዌ
ነው፤ ዕቃውም ርኩስ ነው። 52ልብሱን
ወይም በሸማኔ ዕቃ የተሠራውን ወይም በእጅ
የተጠለፈውን የበግ ጠጕር ወይም በፍታ
ወይም ደዌው ያለ በትን ማንኛውንም
ከቈዳ የተሠራ ዕቃ ያቃጥል፤ ደዌው ክፉ
ነውና፤ ዕቃው ይቃጠል።

53"ነገር ግን ካህኑ በሚመረምርበት ጊዜ
ደዌው በልብሱ ወይም በሸማኔ ዕቃ በተሠ
ራው ወይም በእጅ በተጠለፈው ጨርቅ
ላይ፣ ወይም ከቈዳ በተሠራው ዕቃ ላይ
ተስፋፍቶ ካልተገኘ፣ 54ካህኑ ደዌው ያለበት
ነገር እንዲታጠብ ይዘዝ፤ ዕቃውንም ሰባት
ቀን ደግሞ ያግልል። 55ደዌው ያለበት ዕቃ
ከታጠበ በኋላ ካህኑ ይመርምረው፤ ደዌው
ባይስፋፋም እንኳ መልኩን ካልለወጠ፣
ርኩስ ነው፤ ደዌው የወጣው በውስጥም
ሆነ በውጭ ዕቃው በእሳት ይቃጠል።
56ዕቃው ከታጠበ በኋላ ካህኑ በሚመረምርበት
ጊዜ ደዌው ከስሞ ቢገኝ፣ በደዌ የተበከ
ለውን ቦታ ከልብሱ ወይም ከቈዳው ወይም
በሸማኔ ዕቃ ከተሠራው ወይም በእጅ ከተ
ጠለፈው ጨርቅ ቀዶ ያውጣ። 57ነገር ግን
ደዌው በልብሱ ወይም በሸማኔ ዕቃ በተሠ
ራው ወይም በእጅ በተጠለፈው ጨርቅ
ላይ ወይም ከቈዳ በተሠራው ዕቃ ላይ
ቢታይ፣ መስፋፋቱ ስለ ሆነ ደዌው ያለበት
ማንኛውም ነገር በእሳት ይቃጠል። 58ታጥቦ
ከደዌ የጠራ ልብስ ወይም በሸማኔ ዕቃ
የተሠራ ወይም በእጅ የተጠለፈ ጨርቅ
ወይም ከቈዳ የተሠራ ማንኛውም ዕቃ እንደ
ገና ይታጠብ፤ ንጹሕም ይሆናል።"

59ከበግ ጠጕር ወይም ከበፍታ የተሠራ
ልብስ ወይም በሸማኔ ዕቃ የተሠራ ወይም
በእጅ የተጠለፈ ጨርቅ ወይም ከቈዳ
የተሠራ ማንኛውም ዕቃ በደዌ ቢበከል፣
ንጹሕ ወይም ርኩስ መሆኑን ለማወቅ ሕጉ
ይህ ነው።

## ከተላላፊ የቈዳ በሽታ የመንጻት ሥርዐት

14 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2"የታመመው ሰው እንዲ

13፥32 ቊ5
13፥34 ቊ5፤ ዘሌ11፥25
13፥36 ቊ30
13፥40 ዘሌ21፥5፤ 2ነገ2፥23፤ኢሳ3፥24፤ 15፥2፤22፥12፤ ሕዝ27፥31፤29፥18፤ አሞ8፥10፤ ሚክ1፥16
13፥45 ዘሌ5፥2፤ 10፥6፤ሕዝ24፥17፡ 22፤ሰቆ4፥15፤ ሚክ3፥7፤ሉቃ17፥12
13፥46 ዘኍ5፥1-4፤ 12፥14፤2ነገ7፥3፤ 15፥5
13፥49 ማር1፥44
13፥50 ሕዝ44፥23
13፥51 ቊ5፤ ዘሌ14፥44
13፥52 ቊ55፡57
14፥2 ዘሌ13፥57፤ ዘዳ24፥8፤ማቴ8፥2-4፤ማር1፥40-44፤ ሉቃ5፥12-14፤17፥14

[፳]45 ወይም *ራሱንም አይሸፍን*

ነጻ ወደ ካህኑ በሚወስዱት ጊዜ ሥርዐቱ
እንዲህ ነው:- 3ካህኑ ከሰፈር ወደ ውጭ
ወጥቶ ይመርምረው፤ ሰውየው ከተላላፊ
የቈዳ በሽታው[ገ] ተፈውሶ ከሆነ፣ 4ካህኑ
ስለሚነጻው ሰው፣ ለመብላት ከተፈቀደው
የወፍ ዐይነት ሁለት ከነሕይወታቸው፣ የዝ
ግባ ዕንጨት፣ ደመቅ ያለ ቀይ ድርና ሂሶጵ
እንዲያመጣ ይዘዝ:: 5ካህኑም ከወፎቹ አንዱን
በሸክላ ዕቃ ውስጥ ባለ የምንጭ ውሃ ላይ
እንዲታረድ ይዘዝ:: 6በሕይወት ያለውንም
ወፍ ከዝግባው ዕንጨት፣ ደመቅ ካለው
ቀይ ድርና ከሂሶጵ ጋር በምንጩ ውሃ
ላይ በታረደው ወፍ ደም ውስጥ ይንከር::
7ከተላላፊ በሽታ የሚነጻውንም ሰው ሰባት
ጊዜ ይርጨው፤ መንጻቱንም ያስታውቅ፤ በሕ
ይወት ያለውንም ወፍ ወደ ውጭ ይልቀ
ቀው::

8"የሚነጻው ሰው ልብሱን ይጠብ፤ ጠጕ
ሩን በሙሉ ይላጭ፤ ሰውነቱን በውሃ ይታጠብ፤
በሥርዐቱም መሠረት ንጹሕ ይሆናል::
ከዚህም በኋላ ወደ ሰፈር መግባት ይችላል፤
ነገር ግን ሰባት ቀን ከድንኳኑ ውጭ
ይቈይ:: 9በሰባተኛውም ቀን ጠጕሩን በሙሉ
ይላጭ፤ ራሱን፣ ጢሙን፣ ቅንድቡንና
ሌላውንም ጠጕር ሁሉ ይላጭ:: ልብሱን
ይጠብ፤ ሰውነቱን በውሃ ይታጠብ፤ ንጹሕም
ይሆናል::

10"በስምንተኛው ቀን ነውር የሌለባቸ
ውን ሁለት ተባዕት የበግ ጠቦቶችና ነውር
የሌለባትን አንዲት የዓመት እንስት በግ
ያቅርብ፤ እንዲሁም ለእህል ቍርባን የሚ
ሆን በዘይት የተለወሰ የኢፍ ሦስት ዐሥ
ረኛ[ጠ] የላመ ዱቄት ያቅርብ፤ ደግሞ አንድ
ሎግ[ጨ] ዘይት ያምጣ:: 11ሰውየው የነጻ
መሆኑን የሚያስታውቀው ካህን የሚነጻውን
ሰውና መሥዋዕቶቹን በመገናኛው ድንኳን
ደጃፍ ላይ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ያቅርብ::

12"ካህኑም ከተባዕቱ ጠቦቶች በመውሰድ
ከሎግ ዘይቱ ጋር የበደል መሥዋዕት አድርጎ
ያቅርብ፤ የሚወዘወዝ መሥዋዕት በማድረግም
*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ይወዝውዛቸው::
13ጠቦቱንም፣ የኀጢአት መሥዋዕትና የሚቃ
ጠል መሥዋዕት በሚታረድበት በተቀደሰው
ስፍራ ይረደው፤ የኀጢአት መሥዋዕቱ ለካ
ህኑ እንደሚሰጥ ሁሉ የበደል መሥዋዕቱም
ለካህኑ ይሰጥ፤ ይህም እጅግ የተቀደሰ
ነው:: 14ካህኑ ከበደል መሥዋዕቱ ደም ወስዶ
የሚነጻውን ሰው ቀኝ ጆሮ ታችኛውን ጫፍ፣
የቀኝ እጁን አውራ ጣትና የቀኝ እግሩን
አውራ ጣት ያስነካ:: 15ካህኑም ከሎግ ዘይት
ወስዶ በራሱ ግራ እጅ መዳፍ ውስጥ
ይጨምር፤ 16የቀኝ እጁንም ጣት በመዳፉ
በያዘው ዘይት ውስጥ በመንከር *በእግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) ፊት ሰባት ጊዜ በጣቱ ይርጭ::
17ካህኑ በመዳፉ ውስጥ ከቀረው ዘይት
ጥቂቱን ወስዶ የሚነጻውን ሰው ቀኝ ጆሮ
ታችኛውን ጫፍ፣ የቀኝ እጁን አውራ
ጣትና የቀኝ እግሩን አውራ ጣት በበደል
መሥዋዕቱ ደም ላይ ደርቦ ይቅባ:: 18በመ
ዳፉ ላይ የቀረውንም ዘይት በሚነጻው
ሰው ራስ ላይ ያድርግ፤ *በእግዚአብሔርም* (ያህዌ)
ፊት ያስተሰርይለት::

19"ካህኑም የኀጢአት መሥዋዕቱን ያቅ
ርብ፤ ከርኩሰቱ ለሚነጻውም ሰው ያስተሰ
ርይለት፤ ከዚህ በኋላ የሚቃጠለውን መሥ
ዋዕት ይረድ፤ 20ከእህል ቍርባኑም
ጋር በመሠዊያው ላይ በማቅረብ ያስተሰጠ
ርይለት፤ ሰውየውም ንጹሕ ይሆናል::

21"ሰውየው ድኻ ከሆነና እነዚህን ለማቅ
ረብ ዐቅሙ ካልፈቀደለት፣ ማስተሰረያ
እንዲሆነው የሚወዘወዝ አንድ ተባዕት
የበግ ጠቦት ለበደል መሥዋዕት፣ በዘይት
የተለወሰ የኢፍ አንድ ዐሥረኛ[ጸ] የላመ
ዱቄት ለእህል ቍርባን ያቅርብ፤ ደግሞም
አንድ ሎግ ዘይት ያምጣ፤ 22እንዲሁም
ሁለት ርግቦች ወይም ሁለት የዋኖስ
ጫጩቶች ዐቅሙ የፈቀደውን አንዱን ለኀጢ
አት መሥዋዕት፣ ሌላውን ለሚቃጠል መሥ
ዋዕት ያቅርብ::

23"እነዚህንም በስምንተኛው ቀን ስለ
መንጻቱ ሥርዐት ወደ ካህኑ ወደ መገናኛው
ድንኳን ደጃፍ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት
ያቅርብ:: 24ካህኑም ለበደል መሥዋዕት የሚ
ሆነውን የበግ ጠቦትና አንድ ሎግ ዘይት
ይቀበል፤ የሚወዘወዝ መሥዋዕት በማድረ
ግም *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ይወዝውዛቸው::
25ለበደል መሥዋዕት የሚሆነውንም የበግ
ጠቦት ይረድ፤ ከደሙም ጥቂት ወስዶ
የሚነጻውን ሰው የቀኝ ጆሮ ታችኛ ጫፍ፣
የቀኝ እጁን አውራ ጣትና የቀኝ እግሩን
አውራ ጣት ያስነካ፤ 26ከዘይቱም ጥቂቱን
በግራ እጁ መዳፍ ውስጥ ያፍስስ፤ 27የቀኝ
እጁንም ጣት በመዳፉ በያዘው ዘይት ውስጥ
በመንከር *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ሰባት
ጊዜ ይርጭ:: 28በመዳፉ ከያዘው ዘይት
ጥቂቱን ወስዶ የበደል መሥዋዕቱን ደም
ባስነካበት ቦታ፣ ይኸውም የሚነጻውን ሰው
ቀኝ ጆሮ ጫፍ፣ የቀኝ እጁን አውራ ጣትና
የቀኝ እግሩን አውራ ጣት ያስነካ:: 29ካህኑ

14፥3 ዘሌ13፥2:46
14፥4 ቍ6:49:51:52፤ዘፀ12፥22፤ዘኍ19፥6፤መዝ51፥7
14፥5 ቍ50
14፥6 ቍ4
14፥7 ቍ51:53፤2ነገ5፥10:14፤ኢሳ52፥15፤ሕዝ36፥25
14፥8 ቍ9:20፤ዘፀ29፥4፤ዘሌ11፥25፤13፥11፤15፥5፤17፥15፤22፥6፤ዘኍ5፥2:3፤12፥14:15፤19፥7:8:20፤ 31፥24፤2ዜና26፥21
14፥9 ዘሌ13፥5:6፤ዘኍ6፥9፤ዘዳ21፥12
14፥10 ቍ12:15:21:24፤ዘሌ2፥1፤4፥32 ዘኍ6፥10፤15፥9፤28፥20፤ማቴ8፥4፤ማር1፥44፤ሉቃ5፥14
14፥11 ዘኍ6፥10:16
14፥12 ዘፀ29፥24፤ዘሌ5፥18
14፥13 ዘፀ29፥11፤ዘሌ6፥24-30፤7፥7
14፥14 ዘፀ29፥20
14፥15 ቍ26
14፥16 ቍ27
14፥17 ቍ28
14፥18 ቍ31፤ዘሌ15፥15
14፥19 ቍ31፤ዘሌ5፥3፤15፥15
14፥20 ቍ8፤ዘሌ15፥30
14፥21 ቍ22:32፤ዘሌ5፥7
14፥22 ዘሌ5፥7፤15፥30
14፥23 ቍ10:11፤ዘሌ15፥14:29
14፥24 ቍ10:12፤ዘኍ6፥14
14፥25 ዘፀ29፥20
14፥26 ቍ15
14፥29 ቍ18

[ገ]3 በትውፊት ለምጽ ይባላል:: የዕብራይስጡ ቃል ከቈዳ ጋር ለተያያዘ በሽታ አንድ ቃል ነው፤ በዚህ ምዕራፍ በሌላ ስፍራም ይገኛል::
[ጠ]10 6.5 ሊትር ገደማ ይሆናል
[ጨ]10 0.3 ሊትር ገደማ ይሆናል፤ እንዲሁም ቍ 12:15:21:24 ይመ
[ጸ]21 2 ሊትር ገደማ ይሆናል

*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ያስተሰርይለት
ዘንድ በመዳፉ ከያዘው ዘይት የቀረውን
በሚነጻው ሰው ራስ ላይ ያፍስ፤ 30ካህኑም
ርግቦቹን ወይም የዋኖሶቹን ጫጩቶች የሰ
ውየው ዐቅም የፈቀደውን ይሠዋል፤ 31ከእነዚ
ህም አንዱን[ጳ] ለኀጢአት መሥዋዕት፣ ሌላ
ውን ለሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ ከእህሉ
ቍርባን ጋር ያቅርብ፤ በዚህም ሁኔታ
ካህኑ ለሚነጻው ሰው *በእግዚአብሔር* (ያህዌ)
ፊት ያስተሰርይለታል።"
32ተላላፊ የቈዳ በሽታ ይዞት የሚነጻ
በትን መደበኛ መሥዋዕት ለማቅረብ ዐቅም
ላነሠው ሰው ሕጉ ይህ ነው።

**ልብስ ላይ ከሚታይ ተላላፊ በሽታ መንጻት**

33*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴንና አሮንን
እንዲህ አላቸው፤ 34"ርስት አድርጌ ወደምሰ
ጣቸው ወደ ከነዓን ምድር በገባችሁ ጊዜ፣
በዚያ አገር አንዱን ቤት በተላላፊ በሽታ
የበከልሁ እንደሆን፣ 35ባለቤቱ ወደ ካህኑ
ሄዶ፣ 'በቤቴ ውስጥ ተላላፊ በሽታ የሚመ
ስል ነገር አይቻለሁ' ብሎ ይንገረው። 36ካህኑ
ወደዚያ ቤት በመግባት በሽታውን መርምሮ
ርኩስ መሆኑን ከማስታወቁ በፊት፣ ቤቱን
ባዶ እንዲያደርጉት ይዘዝ፤ ከዚህ በኋላ ካህኑ
ወደ ቤቱ ገብቶ ይመርምር። 37በግድ
ግዳው ላይ ያለውን ተላላፊ በሽታ በሚመረ
ምርበት ጊዜ፣ መልኩ ወደ አረንጓዴነት
ወይም ወደ ቀይነት የሚያደላ የተቦረቦረ
ነገር በግድግዳው ቢታይ፣ 38ካህኑ ከቤቱ
ወደ ደጅ ወጥቶ ቤቱን ሰባት ቀን ይዝ
ጋው። 39ካህኑም በሰባተኛው ቀን ቤቱን
ለመመርመር ይመለስ፤ ተላላፊው በሽታ
በግድግዳው ተስፋፍቶ ቢገኝ፣ 40የተበከሉት
ድንጋዮች ተሰርስረው እንዲወጡና ከከተማው
ውጭ ባለው ርኩስ ስፍራ እንዲጣሉ
ይዘዝ፤ 41የቤቱ ግድግዳ በሙሉ በውስጥ
በኩል እንዲፋቅና ፍቅፋቂው ከከተማው
ውጭ ባለው ርኩስ ስፍራ እንዲደፋ ያድ
ርግ። 42በወጡትም ድንጋዮች ቦታ ሌሎች
ድንጋዮች አምጥተው ይተኩ፤ ሌላም ጭቃ
ወስደው ቤቱን ይምረጉ።
43"ድንጋዮቹ ወጥተው፣ ቤቱ ከተፈቀ
ፈቀና ከተመረገ በኋላ ተላላፊው በሽታ
እንደገና በቤቱ ውስጥ ከታየ፣ 44ካህኑ ሄዶ
ይመርምረው፤ ተላላፊው በሽታ በቤቱ ውስጥ
ተስፋፍቶ ከተገኘ፣ አደገኛ በሽታ ነው፤
ቤቱም ርኩስ ነው። 45ስለዚህ ቤቱ ይፍረስ፤
ድንጋዩ፣ ዕንጨቱና ምርጊቱ በሙሉ ከከተማ
ውጭ ባለው ርኩስ ስፍራ ይጣል።
46"ቤቱ ተዘግቶ ሳለ ማንኛውም ሰው
ቢገባበት፣ ያ ሰው እስከ ማታ ድረስ ርኩስ
ይሆናል። 47በዚያ ቤት ገብቶ የተኛ ወይም
የበላ ማንኛውም ሰው ልብሶቹን ይጠብ።
48"ነገር ግን ቤቱ ከተመረገ በኋላ ካህኑ
ሊመረምረው በሚመጣበት ጊዜ ተላላፊው
በሽታ ሳይስፋፋ ቢገኝ፣ በሽታው ስለለቀ
ቀው ቤቱ ንጹሕ መሆኑን ያስታውቅ።
49ቤቱንም ለማንጻት ሁለት ወፎች፣ የዝግባ
ዕንጨት፣ ደመቅ ያለ ቀይ ድርና ሂሶጵ
ያቅርብ። 50ከወፎቹም አንዱን በሸክላ ዕቃ
ውስጥ ባለ የምንጭ ውሃ ላይ ይረድ።
51የዝግባውን ዕንጨት፣ ሂሶጱን፣ ደመቅ
ያለውን ቀይ ድርና በሕይወት ያለውን
ወፍ ወስዶ በታረደው ወፍ ደምና በም
ንጩ ውሃ ውስጥ ይንከር፤ ቤቱንም ሰባት
ጊዜ ይርጭ። 52ቤቱንም በወፉ ደም፣ በም
ንጩ ውሃ፣ በሕይወት ባለው ወፍ፣ በዝግ
ባው ዕንጨት፣ በሂሶጱና ደመቅ ባለው
ቀይ ድር ያንጻው። 53በሕይወት ያለውንም
ወፍ ከከተማ ወደ ውጭ ይልቀቀው፤ በዚህ
ሁኔታ ለቤቱ ያስተሰርይለታል፤ ቤቱም
ንጹሕ ይሆናል።"
54ይህ ሕግ ለማንኛውም ተላላፊ የቈዳ
በሽታ፣ ለሚያሳክክ ሕመም፣ 55በልብስና
በቤት ላይ ለሚመጣ ተላላፊ በሽታ፣ 56ለዕ
ብጠት፣ ለችፍታ ወይም ለቋቍቻ፣ 57አንድ
ነገር ንጹሕ ወይም ርኩስ መሆኑ የሚታወ
ቅበት ነው። ይህ ተላላፊ የቈዳ በሽታ
እንዲሁም በልብስና በቤት ላይ ለሚወጣ
ተላላፊ በሽታ የሚያገለግል ሕግ ነው።

**የሚያረክስ የሰውነት ፈሳሽ**

15 *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴንና አሮ
ንን እንዲህ አላቸው፤ 2"ለእስራ
ኤላውያን እንዲህ ብላችሁ ንገሯቸው፤
'ማንም ሰው ከሰውነቱ ፈሳሽ ነገር ቢወጣ
ያ ሰው ርኩስ ነው። 3ከሰውነቱ የሚወጣው
ፈሳሽ መፍሰሱን ቢቀጥል ወይም ባይቀጥል
ሰውየው ርኩስ ነው፤ ፈሳሹም ርኵሰት
የሚያስከትለው እንደዚህ ነው፦
4" 'ፈሳሽ ነገር የሚወጣው ሰው የተኛ
በት የትኛውም መኝታ ርኩስ ይሆናል፤ እርሱ
የተቀመጠበት ማንኛውም ነገር ርኩስ
ይሆናል። 5ዐልጋውን የነካ ማንኛውም
ሰው ልብሱን ይጠብ፤ ሰውነቱንም በውሃ
ይታጠብ፤ እስከ ማታ ድረስ ግን ርኩስ
ይሆናል። 6ፈሳሽ ነገር የሚወጣው ሰው
በተቀመጠበት በየትኛውም ነገር ላይ የተ
ቀመጠ ሰው ሁሉ ልብሱን ይጠብ፤ ሰው
ነቱንም በውሃ ይታጠብ፤ እስከ ማታ ድረስ
ግን ርኩስ ይሆናል።

14፥30 ዘሌ5፥7
14፥31 ቀኍ18፡19፡22፤ዘሌ5፥7፤15፥15፡30
14፥32 ቀኍ21፤ዘሌ13፥2
14፥34 ዘፍ12፥5፤17፥8፤48፥4፤ዘθ6፥4፤ዘኍ13፥2፤27፥12፤32፥22፤ዘዳ3፥27፤7፥1፤32፥49
14፥37 ዘሌ13፥19
14፥38 ዘሌ13፥4
14፥39 ዘሌ13፥5
14፥40 ቀኍ45
14፥44 ዘሌ13፥51
14፥46 ዘሌ11፥24
14፥47 ዘሌ11፥25
14፥48 ዘሌ13፥6
14፥49 1ነገ4፥33
14፥50 ቀኍ5
14፥51 ቀኍ4፡6፡7፤መዝ51፥7
14፥53 ቀኍ7፡20
14፥54 ዘሌ13፥2
14፥55 ዘሌ13፥47-52
14፥56 ዘሌ13፥2
14፥57 ዘሌ10፥10
15፥2 ቀኍ16፡32፤ዘሌ22፥4፤ዘኍ5፥2፤2ሳሙ3፥29፤ማቴ9፥20
15፥5 ዘሌ11፥25፤14፥8፤11፥24

[ጳ]31 የሰብዓ ሊቃናትና የሱርስት ትርጒሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ 31*የሰውየው ዐቅም የፈቀደውን ያህል አንዱን ለኀጢአት ይላል*

7“ ‘ፈሳሽ ነገር የሚወጣውን ሰው የነካ
ማንኛውም ሰው ልብሱን ይጠብ፤ ሰውነ
ቱንም በውሃ ይታጠብ፤ እስከ ማታ ድረስ
ግን ርኩስ ይሆናል።
8“ ‘ፈሳሽ ነገር የሚወጣው ሰው ንጹሕ
በሆነ ሰው ላይ ቢተፋ፣ የተተፋበት ሰው
ልብሱን ይጠብ፤ ሰውነቱንም በውሃ ይታ
ጠብ፤ እስከ ማታ ድረስ ግን ርኩስ ይሆ
ናል።
9“ ‘ፈሳሽ ነገር የሚወጣው ሰው የተቀ
መጠበት ኮርቻ ሁሉ ርኩስ ይሆናል፤ 10ከበ
ታቹ ያለውንም ነገር ሁሉ የነካ ማንም
ሰው እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ይሆናል። እነ
ዚህንም ነገሮች የሚያነሣ ማንም ሰው ልብ
ሱን ይጠብ፤ ሰውነቱንም በውሃ ይታጠብ፤
እስከ ማታ ድረስ ግን ርኩስ ይሆናል።
11“ ‘ፈሳሽ ነገር የሚወጣው ሰው እጁን
በውሃ ሳይታጠብ ሌላውን ሰው ቢነካ፣ የተ
ነካው ሰው ልብሱን ይጠብ፤ ሰውነቱንም
በውሃ ይታጠብ፤ እስከ ማታ ድረስ ግን
ርኩስ ይሆናል።
12“ ‘ፈሳሽ ነገር የሚወጣው ሰው የነካው
የሸክላ ዕቃ ይሰበር፤ ከዕንጨት የተሠራ ዕቃ
ከሆነ በውሃ ይታጠብ።
13“ ‘ፈሳሽ ነገር የሚወጣው ሰው ከፈሳሹ
ሲነጻ፣ በሕጉ መሠረት ለመንጻቱ ሰባት
ቀን ይቍጠር፤ ልብሱን ይጠብ፤ ሰውነቱንም
በምንጭ ውሃ ይታጠብ፤ ንጹሕም ይሆናል።
14በስምንተኛውም ቀን ሁለት ርግቦች ወይም
ሁለት የዋኖስ ጫጩቶች ይዞ በመገናኛው
ድንኳን ደጃፍ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት
በመቅረብ ለካህኑ ይስጥ። 15ካህኑም አንዱን
ለኀጢአት መሥዋዕት፣ ሌላውንም ለሚቃጠል
መሥዋዕት ያቅርብ፤ በዚህ መሠረት ስለ
ፈሳሹ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ለሰውየው
ያስተሰርይለታል።
16“ ‘አንድ ሰው ዘሩ በሚፈስበት ጊዜ
ሰውነቱን በሙሉ በውሃ ይታጠብ፤ እስከ
ማታ ድረስ ግን ርኩስ ይሆናል። 17የፈሰ
ሰው ዘር የነካው ማንኛውም ልብስ ወይም
ቍርበት በውሃ ይታጠብ፤ እስከ ማታ
ድረስ ግን ርኩስ ይሆናል። 18አንድ ሰው
ከአንዲት ሴት ጋር ግብረ ሥጋ ፈጽሞ ዘር
ቢፈስው፣ ሁለቱም በውሃ ይታጠቡ፤ እስከ
ማታ ድረስ ግን ርኩሳን ይሆናሉ።
19“ ‘ሴት ጊዜውን እየጠበቀ የሚመጣው
የደም መፍሰስ ቢኖርባት፣ የወር አበባዋ
ርኵሰት እስከ ሰባት ቀን ይቆያል፤ በዚህ
ጊዜ ማንም ሰው ቢነካት እስከ ማታ ድረስ
ርኩስ ይሆናል።
20“ ‘በወር አበባዋ ጊዜ የምትተኛበት
ማንኛውም ነገር ርኩስ ይሆናል፤ የተቀ

15፥7 ቀኍ16፡19፤ ዘሌ22፥4፡5
15፥8 ዘኍ12፥14
15፥10 ዘኍ19፥10
15፥12 ዘሌ6፥28፤ 11፥32
15፥13 ቀኍ5፤ ዘሌ8፥33
15፥14 ዘሌ14፥22
15፥15 ዘሌ5፥7፤ 14፥18፡19፡31
15፥16 ቀኍ2፡5፤ ዘዳ23፥10፡11
15፥18 1ሳሙ21፥4
15፥19 ቀኍ24

15፥21 ቀኍ27
15፥24 ቀኍ19፤ ዘሌ12፥2፤18፥19፤ 20፥18፤ሕዝ18፥6
15፥25 ማቴ9፥20፤ ማር5፥25፤ሉቃ8፥43
15፥29 ዘሌ14፥22
15፥30 ዘሌ5፥10፤ 14፥20፡31፤18፥19፤ 2ሳሙ11፥4፤ማር5፥25፤ሉቃ8፥43
15፥31 ዘሌ20፥3፤ ዘኍ5፥3፤19፥13፡20፤ 2ሳሙ15፥25፤ 2ነገ21፥7፤ መዝ33፥14፤74፥7፤ 76፥2፤ሕዝ5፥11፤ 23፥38
15፥32 ቀኍ2
15፥33 ቀኍ19፡24፡ 25

መጠችበትም ነገር ርኩስ ይሆናል። 21መኝ
ታዋን የነካ ማንኛውም ሰው ልብሱን
ይጠብ፤ ሰውነቱንም በውሃ ይታጠብ፤ እስከ
ማታ ድረስ ግን ርኩስ ይሆናል። 22የተቀ
መጠችበትን ማንኛውም ነገር የነካ ሰው
ልብሱን ይጠብ፤ ሰውነቱንም በውሃ
ይታጠብ፤ እስከ ማታ ድረስ ግን ርኩስ
ይሆናል፤ 23መኝታዋን ወይም የተቀመጠ
ችበትን ማንኛውም ነገር የነካ ሰው እስከ
ማታ ድረስ ርኩስ ይሆናል።
24“ ‘አንድ ሰው ከእርሷ ጋር ቢተኛና
የወር አበባዋ ቢነካው፣ እስከ ሰባት ቀን
ድረስ ርኩስ ይሆናል፤ እርሱ የሚተኛበት
መኝታ ሁሉ ርኩስ ይሆናል።
25“ ‘ሴት ከወር አበባዋ ጊዜ ሌላ ብዙ
ቀን ደም ቢፈስሳት፣ ወይም የወር አበባዋ
ጊዜ ካለፈ በኋላ የደሙ መፍሰስ ባይቋረጥ፣
ልክ እንደ ወር አበባዋ ጊዜ፣ ደም መፍ
ሰሱ እስኪቆም ድረስ ርኩስ ትሆናለች።
26ደሟ መፍሰሱን በቀጠለበት ጊዜ ሁሉ፣
የምትተኛበት ማንኛውም መኝታ ልክ በወር
አበባዋ ጊዜ እንደነበረው መኝታ ርኩስ
ይሆናል፤ የምትቀመጥበትም ማንኛውም
ነገር ልክ እንደ ወር አበባዋ ጊዜ ርኩስ
ይሆናል። 27እነዚህንም የሚነካ ማንኛውም
ሰው ርኩስ ይሆናል፤ ልብሱን ይጠብ፤ ሰው
ነቱንም በውሃ ይታጠብ፤ እስከ ማታ
ድረስ ግን ርኩስ ይሆናል።
28“ ‘ከደምዋ ፍሳሽ ሳትነጻ ሰባት ቀን
ትቍጠር፤ ከዚያም በኋላ በሥርዐቱ መሠ
ረት ንጹሕ ትሆናለች። 29በስምንተኛውም
ቀን ሁለት ርግቦች ወይም ሁለት የዋኖስ
ጫጩቶች ይዛ በመቅረብ በመገናኛው
ድንኳን ደጃፍ ለካህኑ ትሰጣለች። 30ካህኑም
አንዱን ለኀጢአት መሥዋዕት፣ ሌላውንም
ለሚቃጠል መሥዋዕት ያቅርብ፤ በዚህ
መሠረት ስለፈሳሽዋ ርኵሰት *በእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ፊት ያስተሰርይላታል።
31“ ‘በመካከላቸው ያለችውን ማደሪያዬን[θ]
እንዳያረክሱና በርኵሰታቸው እንዳይሞቱ፣
እስራኤላውያንን ከሚያረክሳቸው ነገር
ለዩአቸው።’ ”
32ፈሳሽ ነገር የሚወጣውን፣ ዘሩም በመ
ፍሰሱ ርኩስ የሆነውን ሰው ሁሉ፣ 33በወር
አበባ ላይ ያለችን ሴት፣ ፈሳሽ ነገር የሚ
ወጣቸውን ወንድ ወይም ሴት፣ በሥርዐቱ
መሠረት ርኩስ ከሆነች ሴት ጋር የሚ
ተኛውን ወንድ በሚመለከት ሕጉ ይኸው
ነው።

[θ]31 ወይም *የመገናኛ ድንኳኔን*

## የስርየት ቀን

16፥2-34 ተጓ ምብ – ዘሌ 23፥26-32፤ ዘኍ 29፥7-11

16 *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት በቀረቡ
ጊዜ ከሞቱት፣ ከሁለቱ የአሮን
ልጆች ሞት በኋላ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን
ተናገረው:: 2*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን
እንዲህ አለው “እኔ በስርየቱ መክደኛ ላይ
በደመና ውስጥ እገለጣለሁና፣ ወንድምህ
አሮን በመጋረጃው ውስጥ ወዳለው ወደ
ቅድስተ ቅዱሳን ማለት በታቦቱ ላይ
ወዳለው ወደ ስርየቱ መክደኛ ፊት፣ በፈ
ለገ ጊዜ ሁሉ እንዳይገባና እንዳይሞት
ንገረው:: 3ወደ ተቀደሰው ስፍራ በሚገባ
በት ጊዜ፣ አሮን እንዲህ ያድርግ:- ለኀጢ
አት መሥዋዕት አንድ ወይፈን፣ ለሚቃጠል
መሥዋዕት አንድ አውራ በግ ይዞ ይምጣ፤
4የተቀደሰውን የበፍታ ቀሚስ ይልበስ፤
በሰውነቱ ላይ የሚያርፈውን ከበፍታ የተ
ሠራውን የውስጥ ሱሪ ያጥልቅ፤ የበፍታውን
መታጠቂያ ይታጠቅ፤ የበፍታውን መጠ
ምጠሚያ ይጠምጥም፤ ልብሶቹ የተቀደሱ
በመሆናቸው እነዚህን ከመልበሱ በፊት
ሰውነቱን በውሃ ይታጠብ:: 5ከእስራኤል
ማኅበረ ሰብ ለኀጢአት መሥዋዕት ሁለት
ተባዕት ፍየሎች፣ ለሚቃጠል መሥዋዕት
አንድ አውራ በግ ይውሰድ::

6“አሮን ለራሱና ለቤተ ሰቡ ማስተሰረያ
ይሆን ዘንድ፣ ወይፈኑን የኀጢአት መሥ
ዋዕት አድርጎ ስለ ራሱ ያቅርብ፤ 7ሁለ
ቱንም አውራ ፍየሎች ወስዶ በመገናኛው
ድንኳን ደጃፍ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት
ያቁማቸው:: 8አሮንም አንዱን ዕጣ *ለእግ
ዚአብሔር* (ያህዌ)፣ ሌላውን ለሚለቀቀው
ፍየል[ፊ] ለማድረግ በሁለቱ ፍየሎች ላይ ዕጣ
ይጣል:: 9በዕጣ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) የደ
ረሰውንም ፍየል አምጥቶ ለኀጢአት መሥ
ዋዕት በማድረግ ይሠዋ:: 10ወደ ምድረ በዳ
ተለቅቆ ማስተሰረያ ይሆን ዘንድ፣ እንዲ
ለቀቅ ዕጣ የወጣበትን ፍየል ከነሕይወቱ
*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ያቅርብ::

11“አሮን ለራሱና ለቤተ ሰቡ ማስተሰረያ
ይሆን ዘንድ ወይፈኑን የኀጢአት መሥ
ዋዕት አድርጎ ስለ ራሱ ያቅርብ፤ ወይፈኑ
ንም ስለ ራሱ የኀጢአት መሥዋዕት አድርጎ
ይረድ:: 12*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ካለው
መሠዊያ ፍም ተወስዶ የተሞላበትን ጥና
ይያዝ፤ ሁለት እጅ ሙሉ መልካም መዐዛ
ያለው ዕጣን ይውሰድ፤ እነዚህንም ወደ
መጋረጃው ውስጥ ይዞ ይግባ:: 13እንዳይሞ
ትም የዕጣኑ ጢስ በምስክሩ ላይ ያለውን
ስርየት መክደኛ ይሸፍነው ዘንድ፣ *በእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ፊት ዕጣኑን በእሳቱ ላይ

16፥1 ዘሌ10፥10
16፥2 ዘፀ25፥22፤ 26፥34:33፤30፥10፤ 40፥34፤2ሳሙ22፥10፤ ዕብ6፥19፤9፥7:25፤ 10፥19፤6፥19
16፥3 ቍ5:6፤ ዘሌ4፥1-12፤ ዕብ9፥24:25
16፥4 ቍ32፤ ዘፀ28፥39:42፤29፥4: 29:30፤ዘሌ8፥13፤ 21፥10፤ዘኍ20፥26: 28፤ሕዝ9፥2፤ 44፥17-18፤ዕብ10፥22
16፥5 ቍ20፤ ዘሌ4፥3:13-21፤ 2ዜና29፥23፤ መዝ50፥9
16፥6 ዘሌ9፥7፤ ዕብ7፥27፤9፥7:12
16፥8 ቍ10፥26፤ ዘኍ26፥55:56፤ 33፥54፤34፥13፤ ኢሱ4፥2፤18፥6፤ መሳ20፥9፤ ነህ10፥34፤አስ3፥7፤ 9፥24፤ መዝ22፥18፤ ምሳ16፥33
16፥10 ኢሳ53፥4-10፤ሮሜ3፥25
16፥11 ቍ6:24:33
16፥12 ዘፀ25፥6፤ 30፥34-38፤ ዘሌ10፥1፤ራእ8፥5
16፥13 ዘፀ25፥17፤ 28፥43
16፥14 ዘሌ4፥5: 6፤ዕብ9፥7:13:25
16፥15 ዘሌ4፥13-21፤ ዘኍ19፥19፤ ኢሳ52፥15፤ ሕዝ36፥25፤ ዕብ7፥27፤9፥3:7: 12፤13፥11
16፥16 ዘፀ26፥33፤ 29፥4:36፤40፥2፤ ሮሜ3፥25፤ዕብ9፥25
16፥18 ዘሌ4፥7:25
16፥19 ሕዝ43፥20
16፥20 ቍ5
16፥21 ዘፀ29፥10፤ ዘሌ5፥5
16፥22 ዘፀ28፥38፤ ኢሳ53፥12
16፥23 ዘፀ28፥42፤ ሕዝ42፥14
16፥24 ቍ3-5:11፤ ዘሌ1፥3፤6፥16

ይጨምረው:: 14ከወይፈኑም ደም ወስዶ
በስርየቱ መክደኛ ፊተኛው ወገን ላይ
በጣቱ ይርጭ፤ ደግሞም በስርየቱ መክደኛ
ትይዩ በጣቱ ሰባት ጊዜ ይርጭ::

15“ፍየሉንም ለሕዝቡ የኀጢአት መሥ
ዋዕት አድርጎ ይረደው፤ ደሙንም ወደ
መጋረጃው ውስጥ ወስዶ በወይፈኑ ደም
እንዳደረገው በዚህኛው ያድርግ፤ ደሙን
በስርየቱ መክደኛ ላይ፣ እንዲሁም በመክ
ደኛው ትይዩ ይርጭ:: 16ከእስራኤላውያን
ርኵሰትና ዐመፅ፣ ከየትኛውም ኀጢአታ
ቸው ይነጻ ዘንድ በዚህ ሁኔታ ለቅድስተ
ቅዱሳኑ ያስተሰርይለታል፤ በርኵሰታቸው
መካከል በእነርሱ ዘንድ ላለችውም የመገ
ናኛዋ ድንኳን እንደዚሁ ያደርጋል:: 17አሮን
ለማስተሰረይ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ከገባ
በት ጊዜ ጀምሮ ለራሱ፣ ለቤተሰቡና ለእስ
ራኤል ማኅበረ ሰብ ሁሉ አስተሰርዮ
እስኪወጣ ድረስ ማንም ሰው በመገናኛው
ድንኳን ውስጥ አይገኝ::

18“ከዚያም መጥቶ *በእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ፊት ወዳለው መሠዊያ ይምጣ፤ ለመ
ሠዊያውም ያስተሰርይለት፤ ከወይፈኑና
ከፍየሉ ደም ወስዶ የመሠዊያውን ቀንዶች
ሁሉ ያስነካ፤ 19ከእስራኤላውያንም ርኵሰት
መሠዊያውን ለማንጻትና ለመቀደስ ከደሙ
ወስዶ በጣቱ ሰባት ጊዜ ይርጭበት::

20“አሮን ለቅድስተ ቅዱሳኑ፣ ለመገናኛው
ድንኳንና ለመሠዊያው የሚያደርገውን ስር
የት ከፈጸመ በኋላ በሕይወት ያለውን ፍየል
ወደ ፊት ያቅርበው፤ 21ሁለት እጆቹን በሕ
ይወት ባለው ፍየል ራስ ላይ ይጫን፤
በላዩም የእስራኤላውያንን ክፋትና ዐመፅ፣
ኀጢአታቸውን ሁሉ በሙሉ ይናዘዝበት፤
እነዚህንም በፍየሉ ራስ ላይ ይጫን፤ ፍየሉ
ንም ለዚሁ ተግባር በተመደበ ሰው እጅ
ወደ ምድረ በዳ ይስደደው:: 22ፍየሉም ኀጢ
አታቸውን ሁሉ ተሸክሞ ወደ ምድረ በዳ
ይሄዳል፤ ሰውየውም ፍየሉን ሰው ሊኖርበት
በማይችል ስፍራ ይልቀቀው::

23“ከዚህ በኋላ አሮን ወደ መገናኛው
ድንኳን ሄዶ፣ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ሊገባ
ሲል የለበሳቸውን የበፍታ ልብሶች አው
ልቆ፣ በዚያው ይተዋቸው:: 24በተቀደሰውም
ስፍራ ሰውነቱን በውሃ ይታጠብ፤ የዘወ
ትር ልብሱንም ይልበስ፤ ከዚያም ወጥቶ
ለራሱ ማስተሰረያ የሚቃጠል መሥዋዕት
ያቅርብ፣ ለሕዝቡም ማስተሰረያ የሚቃጠል
መሥዋዕት ያቅርብ:: 25የኀጢአት መሥዋዕ
ቱንም በመሠዊያው ላይ ያቃጥል::

ፊ8 የሚወገደው ፍየል ማለት ነው፤ ዕብራይስጡ *ዐዛዜል* ይላል፤ እንዲሁም ቍ 10:26 ይመ

26“የሚለቀቀውን ፍየል የወሰደው ሰው
ልብሱን ይጠብ፤ ሰውነቱንም በውሃ ይታ
ጠብ፤ ከዚህ በኋላ ወደ ሰፈር መግባት
ይችላል። 27ደማቸው ለማስተሰረያነት ወደ
ቅድስተ ቅዱሳን የገባው፣ ለኀጢአት መሥ
ዋዕት የቀረቡት ወይፈንና ፍየል ከሰፈር
ውጭ ተወስደው ቈዳቸው፣ ሥጋቸውና
ፈርሳቸው ይቃጠል። 28እነዚህንም የሚያ
ቃጥል ሰው ልብሱን ይጠብ፤ ሰውነቱንም
በውሃ ይታጠብ፤ ከዚህ በኋላ ወደ ሰፈር
መግባት ይችላል።

29“ለእናንተ የተሰጣችሁ የዘላለም ሥርዐት
ይህ ነው፦ ሰባተኛው ወር በገባ በዐሥረ
ኛው ቀን ሰውነታችሁን አድክሙ፤[ፐ] የአገሩ
ተወላጅም ሆነ በመካከላችሁ የሚኖር መጻ
ተኛ ምንም ሥራ አይሥራ፤ 30የምትነጹበት
ስርየት በዚች ዕለት ይደረግላችኋልና በእግዚ
አብሔርም (ያህዌ) ፊት ከኀጢአታችሁ ሁሉ
ትነጻላችሁ። 31ይህች የፍጹም ዕረፍት ሰን
በት ናት፤ ሰውነታችሁን አድክሙባት፤
የዘላለም ሥርዐት ናት። 32ሊቀ ካህናት
ለመሆን አባቱን በመተካት የተቀባና የተሾመ
ካህን ያስተሰርይ፤ የተቀደሰውንም የበፍታ
ልብስ ይልበስ፤ 33ለቅድስተ ቅዱሳኑ፣ ለመ
ገናኛው ድንኳንና ለመሠዊያው፣ ለካህና
ቱና ለማኅበረ ሰቡ ሁሉ ያስተስርይ።

34“ይህ የዘላለም ሥርዐት ይሁናችሁ፤
በዚህም ሥርዐት መሠረት ለእስራኤላው
ያን ኀጢአት ሁሉ በዓመት አንድ ጊዜ
ስርየት ይደረግ።” እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን
እንዳዘዘ እንዲሁ ተደረገ።

### ደም መብላት ስለ መከልከሉ

**17** እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2“ለአሮንና ለልጆቹ፣ ለእስ
ራኤላውያንም ሁሉ እንዲህ ብለህ ንገራ
ቸው፤ ‘እግዚአብሔር (ያህዌ) ያዘዘው ይህ ነው፤
3ማንኛውም እስራኤላዊ በሰፈር ውስጥ
ወይም ከሰፈር ውጭ በሬ፣[ሀ] በግ ወይም
ፍየል ቢያርድ፣ 4በእግዚአብሔር (ያህዌ) ማደ
ሪያ ፊት ለእግዚአብሔር (ያህዌ) መሥዋዕት
አድርጎ ለማቅረብ ወደ መገናኛው ድንኳን
ደጃፍ ባያመጣው፣ ያ ሰው በከንቱ ደም
እንዳፈሰሰ ይቈጠራል፤ ደም በማፍሰሱም
ከወገኖቹ ተለይቶ ይጥፋ። 5እስራኤላውያን
የሚሠዉትን መሥዋዕት ወደ እግዚአብሔር
(ያህዌ) የሚያመጡበት ምክንያት ከዚሁ የተነሣ
ነው። ይህንም ካህኑ ዘንድ በመገናኛው
ድንኳን ደጃፍ አምጥተው ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) የኅብረት መሥዋዕት[ሰ] በማድረግ ያቅ
ርቡ። 6ካህኑም ደሙን በመገናኛው ድን
ኳን ደጃፍ ባለው በእግዚአብሔር (ያህዌ) መሠ
ዊያ ላይ ይርጭ፤ ሥቡንም እግዚአብሔ

16፥26 ቍ8፤ ዘሌ11፥25፤1 4፥8
16፥27 ዘፀ29፥14
16፥28 ዘኍ19፥8፡10
16፥29 ቍ31፤ ዘፀ12፥14፡19፤ 31፥15፤ዘሌ23፥27፡28፡32፤25፥9፤ ዘኍ29፥7፤ኢሳ58፥3
16፥30 ዘፀ30፥10፤ መዝ51፥2፤ኤር33፥8 ሕዝ36፥33፤ ዘካ13፥1፤ኤፌ5፥26
16፥31 ዕዝ8፥21፤ ኢሳ58፥3፡5፤ ዳን10፥12፤ ሐሥ27፥9
16፥32 ቍ4፤ ዘፀ28፥2፤30፥30
16፥33 ቍ11፡16-18፤ሕዝ45፥18
16፥34 ዘፀ27፥21፤ ዕብ9፥7፡25
17፥2 ዘሌ10፥6፡12
17፥3 ዘሌ3፥7፤ 7፥23
17፥4 ቍ9፤ ዘፍ17፥14፤ ዘዳ12፥5-21፤ 1ነገ8፥4፤2ዜና1፥3
17፥5 ዘሌ3፥1፤ ሕዝ43፥27
17፥6 ዘሌ1፥9፤ 3፥2፤4፥18
17፥7 ዘፍ9፥12፤ ዘፀ12፥14፤22፥20፤ 34፥15፤ኤር3፥6፡9፤ ሕዝ23፥3፤ 1ቆሮ10፥20
17፥9 ቍ4፤ ዘሌ1፥3፤3፥7
17፥10 ዘፍ9፥4
17፥11 ቍ14፤ ዕብ9፥22
17፥13 ዘሌ7፥26፤ ሕዝ24፥7፤33፥25፤ ሐሥ15፥20
17፥14 ዘፍ9፥4
17፥15 ዘፀ22፥31፤ ዘሌ7፥24፤11፥40፤ 14፥8
17፥16 ዘሌ5፥1
18፥2 ዘፍ17፥7
18፥3 ቍ24-30፤ ዘፀ23፥24፤ ዘዳ18፥9፤ 2ነገ16፥3፤17፥8፤ 1ዜና5፥25

ር (ያህዌ) ደስ የሚያሰኝ ሽታ እንዲሆን
ያቃጥል። 7ከዚህ በፊት ላመነዘሩባቸው አጋ
ንንት[ሐ] ከእንግዲህ ወዲህ ማንኛውንም መሥ
ዋዕት ሊሠዉ አይገባም። ይህ ለእነርሱና
ከእነርሱ በኋላ ለሚነሣው ትውልድ ሁሉ
የዘላለም ሥርዐት ይሁን።’

8“እንዲህም በላቸው፤ ‘የሚቃጠል መሥ
ዋዕት ወይም ሌላ መሥዋዕት የሚያቀርብ
ማንኛውም እስራኤላዊ ወይም በመካከላቸው
የሚኖር ማንኛውም መጻተኛ፣ 9ወደ መገና
ኛው ድንኳን ደጃፍ ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
ባያቀርብ፣ ያ ሰው ከወገኖቹ ተለይቶ ይጥፋ።

10“ ‘ማንኛውም እስራኤላዊ ወይም በመካ
ከላቸው የሚኖር ማንኛውም መጻተኛ ደም
ቢበላ፣ ደም በሚበላው በዚያ ሰው ላይ
ፊቴን አከብድበታለሁ፤ ከወገኖቹም ለይቼ
አጠፋዋለሁ፤ 11የፍጡር ሕይወት በደሙ
ውስጥ ነውና፤ በመሠዊያ ላይ ለሕይወታችሁ
ማስተስረያ እንዲሆን ደሙን ሰጥቻችኋለሁ፤
ለሰውም ሕይወት ስርየት የሚያስገኝ ደም
ነው። 12ስለዚህ እስራኤላውያንን፣ “ከእናንተ
ማንም ደም አይብላ፤ በመካከላችሁ የሚኖር
መጻተኛም ቢሆን ደም አይብላ” አልሁ።

13“ ‘እንዲበላ የተፈቀደውን ማንኛውንም
እንስሳ ወይም ወፍ አድኖ የያዘ ማንኛውም
እስራኤላዊ ወይም በመካከላችሁ የሚኖር
ማንኛውም መጻተኛ ደሙን ከውስጡ ያፍ
ስስ፤ ዐፈርም ያልብሰው፤ 14የማንኛውም
ፍጡር ሕይወት ደሙ ነውና። ስለዚህ እስ
ራኤላውያንን፣ “የፍጡር ሁሉ ሕይወት
ደሙ ነውና የማንኛውንም ፍጡር ደም አት
ብሉ፤ የበላው ሰው ሁሉ ተለይቶ ይጥፋ”
አልኋቸው።

15“ ‘ሞቶ የተገኘውን ወይም አውሬ
የዘነጠለውን የበላ ማንኛውም የአገር ተወ
ላጅ ወይም መጻተኛ ልብሱን ይጠብ፤ ሰው
ነቱንም በውሃ ይታጠብ፤ በሥርዐቱ መሠ
ረት እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ይሆናል፤
ከዚያም በኋላ ንጹሕ ይሆናል። 16ልብሱን
ባያጥብ፣ ሰውነቱንም ባይታጠብ ግን ኀጢ
አት ሠርቶአልና ይጠየቅበታል።’ ”

**18** እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2“ለእስራኤላውያን እንዲህ
ብለህ ንገራቸው፤ ‘እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ)
አምላካችሁ (ኤሎሂም) ነኝ፤ 3በኖራችሁበት በግብፅ
እነርሱ እንደሚያደርጉት አታድርጉ፤ እኔ

[ፐ]29 ወይም ጹሙ፤ እንዲሁም ቍ 31 ይመ
[ሀ]3 የዕብራይስጡ ቃል ተባዕትና እንስትን ሊያጠቃልል ይችላል።
[ሰ]5 በትውፊት የሰላም መሥዋዕት ይባላል
[ሐ]7 ወይም የፍየል ጣዖታት

በማስገባችሁ በከነዓን እንደሚያደርጉትም
አታድርጉ፤ ልማዳቸውንም አትከተሉ። 4ሕጌን
ታዘዙ፤ ሥርዐቴንም በጥንቃቄ ጠብቁ፤ እኔ
*እግዚአብሔር* አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ።
5ሥርዐቴንና ሕጌን ጠብቁ፤ እነዚህን የሚ
ጠብቅ በሕይወት ይኖርባቸዋልና፤ እኔ
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ።
6“ ‘ማንም ሰው ግብረ ሥጋ ለመፈጸም
ወደ ማንኛውም የሥጋ ዘመዱ አይቅረብ፤
እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ።
7“ ‘ከእናትህ ጋር ግብረ ሥጋ በመፈ
ጸም አባትህን አታዋርድ፤ እናትህ ናት፤
ከእርሷ ጋር በግብረ ሥጋ አትገናኝ።
8“ ‘ከአባትህ ሚስት ጋር ግብረ ሥጋ
አትፈጽም፤ ይህ አባትህን ያዋርዳል።
9“ ‘ከእኅትህ ጋር ግብረ ሥጋ አትፈ
ጽም፤ በቤት ወይም በውጭ የተወለደች
ብትሆን ከአባትህ ወይም ከእናትህ ሴት
ልጅ ጋር በግብረ ሥጋ አትገናኝ።
10“ ‘ከወንድ ልጅህ ሴት ልጅ ወይም
ከሴት ልጅህ ሴት ልጅ ጋር ግብረ ሥጋ
አትፈጽም፤ ይህ አንተን ያዋርዳል።
11“ ‘የአባትህ ሚስት፣ ለአባትህ ከወለደ
ቻት ሴት ልጅ ጋር ግብረ ሥጋ አትፈ
ጽም፤ እኅትህ ናት።
12“ ‘ከአባትህ እኅት ጋር ግብረ ሥጋ
አትፈጽም፤ እርሷ የአባትህ የሥጋ ዘመድ
ናት።
13“ ‘ከእናትህ እኅት ጋር ግብረ ሥጋ
አትፈጽም፤ እርሷ የእናትህ የሥጋ ዘመድ
ናትና።
14“ ‘ከአባትህ ወንድም ሚስት ጋር ግብረ
ሥጋ በመፈጸም፣ የአባትህን ወንድም አታዋ
ርድ፤ እርሷ አክስትህ ናት።
15“ ‘ከምራትህ ጋር ግብረ ሥጋ አትፈ
ጽም፤ የልጅህ ሚስት ናት፤ ከእርሷም ጋር
በግብረ ሥጋ አትገናኝ።
16“ ‘ከወንድምህ ሚስት ጋር ግብረ ሥጋ
አትፈጽም፤ ይህ ወንድምህን ያዋርዳል።
17“ ‘ከእናቲቱና ከሴት ልጇ ጋር ግብረ
ሥጋ አትፈጽም፤ ከወንድ ልጇ ሴት ልጅ
ወይም ከሴት ልጇ ሴት ልጅ ጋር ግብረ
ሥጋ አትፈጽም፤ እነርሱ የሥጋ ዘመዶቿ
ናቸው፤ ይህም ጸያፍ ነው።
18“ ‘ሚስትህ በሕይወት እያለች እኅቷን
ጣውንት አድርገህ አታግባት፤ ከእርሷም ጋር
ግብረ ሥጋ አትፈጽም።
19“ ‘በወር አበባዋ ርኵሰት ጊዜ ግብረ
ሥጋ ለመፈጸም ወደ ሴት አትቅረብ።
20“ ‘ከባልንጀራህ ሚስት ጋር ግብረ ሥጋ
በመፈጸም፣ ራስህን በእርሷ አታርክስ።
21“ ‘ከልጆችህ ማንኛውንም ለሞሎክ
እንዲሠዋ[መ] አሳልፈህ አትስጥ፤ የአምላክህንም
(ኤሎሂም) ስም አታርክስ፤ እኔ *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ነኝ።
22“ ‘ከሴት ጋር እንደሚደረገው ሁሉ
ከወንድ ጋር አትተኛ፤ ይህ አስጸያፊ ነው።
23“ ‘ከእንስሳ ጋር ግብረ ሥጋ በመፈ
ጸም ራስህን አታርክስ። ሴትም ከእንስሳ ጋር
ግብረ ሥጋ ለመፈጸም ራስዋን አታቅርብ፤
ይህ አስጸያፊ ምግባር ነው።
24“ ‘ከእነዚህ በአንዱ እንኳን ራሳችሁን
አታርክሱ፤ ከፊታችሁ የማሳድዳቸው አሕ
ዛብ በእነዚህ ሁሉ ረክሰዋልና። 25ምድሪ
ቱም ሳትቀር ረከሰች፤ እኔም ስለ ኀጢአቷ
ቀጣኋት፤ ስለዚህ የሚኖሩባትን ሰዎች
ተፋቻቸው። 26እናንተ ግን ሥርዐቴንና ሕጌን
ጠብቁ፤ እናንተ የአገር ተወላጆችና በመካከ
ላችሁ የሚኖሩ መጻተኞች ከእነዚህ አስ
ጸያፊ ድርጊቶች ማንኛውንም አትፈ
ጽሙ። 27ከእናንተ በፊት በምድሪቱ የኖሩ
ሰዎች እነዚህን አስጸያፊ ነገሮች ሁሉ ስለ
ፈጸሙ፣ ምድሪቱ ረክሳለች። 28እናንተም
ምድሪቱን ብታረክሷት፣ ከእናንተ በፊት
የነበረውን ሕዝብ እንደ ተፋች እንዲሁ
እናንተንም ትተፋችኋለች።
29“ ‘ከእነዚህ አስጸያፊ ድርጊቶች ማንኛ
ውንም የሚፈጽም ሰው ሁሉ ከወገኑ ተለ
ይቶ ይጥፋ። 30ትእዛዜን ጠብቁ፤ ከእናንተ
በፊት በምድሪቱ የኖሩ ሰዎች ካደረጓቸው
አስጸያፊ ድርጊቶች አንዱንም አትፈጽሙ፤
በእነዚህም ራሳችሁን አታርክሱ፤ እኔ *እግዚ
አብሔር* አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ።

## ልዩ ልዩ ሕግጋት

19 *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2“ለመላው የእስራኤል ሕዝብ
ጉባኤ እንዲህ ብለህ ተናገራቸው፤ ‘እኔ
*እግዚአብሔር* አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ቅዱስ
ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ።
3“ ‘ከእናንተ እያንዳንዱ እናቱንና አባቱን
ያክብር፤ ሰንበታቴን ጠብቁ፤ እኔ *እግዚ
አብሔር* አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ።
4“ ‘ወደ ጣዖታት ዘወር አትበሉ፤ ወይም
ከቀለጠ ብረት ለራሳችሁ አማልክት አትሥሩ፤
እኔ *እግዚአብሔር* አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ።
5“ ‘የኅብረት መሥዋዕት[ሠ] ለ*እግዚአብሔር*
(ያህዌ) በምታቀርቡበት ጊዜ፣ መሥዋዕታችሁ

18፥4 ቍ2፤ ዘፍ26፥5፤ዘዳ4፥1፤ 1ነገ11፥11፤ ኤር44፥10፡23፤ ሕዝ11፥12
18፥5 ዘፍ26፥5፤ ዘዳ4፥1፤ነህ9፥29፤ ኢሳ55፥3፤ሕዝ18፥9፤ 20፥11፤አሞ5፥4-6፤ ማቴ19፥17፤ ሮሜ10፥5፤ገላ3፥12
18፥7 ቍ8፤ ዘሌ20፥11፤ዘዳ27፥20 ሕዝ22፥10
18፥8 ዘፍ35፥22፤ ዘሌ20፥11፤ዘዳ22፥30 27፥20፤1ቆሮ5፥1
18፥9 ቍ11፤ ዘሌ20፥17፤ዘዳ27፥22 2ሳሙ13፥13፤ ሕዝ22፥11
18፥12 ቍ13፤ ዘሌ20፥19
18፥13 ቍ12፡14፤ ዘሌ20፥20
18፥14 ቍ13
18፥15 ዘፍ11፥31፤ 38፥16፤ሕዝ22፥11
18፥16 ዘሌ20፥21፤ ማቴ14፥4፤ማር6፥18
18፥17 ዘሌ20፥14፤ ዘዳ27፥23
18፥18 ዘፍ30፥1
18፥19 ዘሌ15፥24፡ 25-30
18፥20 ዘፀ20፥14፤ ማቴ5፥27፡28፤ 1ቆሮ6፥9፤ዕብ13፥4
18፥21 ዘፀ6፥2፤ ዘሌ19፥12፤ 20፥2-5፤21፥6፤ ዘዳ9፥4፤12፥31፤ 18፥10፤1ነገ11፥5፡7፡3 3፤2ነገ16፥3፤17፥17፤ 21፥6፤ 23፥10፤ 2ዜና28፥1-4፤33፥6፤ መዝ106፥37፡38፤ ኢሳ48፥11፤57፥5፡9፤ ኤር7፥30፡31፤19፥5፤ 32፥35፤49፥1፤ ሕዝ 16፥20፤22፥26፤ 36፥20፤አሞ2፥7፤ ሶፎ1፥5፤ሚክ6፥7፤ ሚል1፥12
18፥22 ዘፍ19፥5፤ ዘሌ20፥13፤ዘዳ23፥18 ሮሜ1፥27፤1ቆሮ6፥9
18፥23 ዘፀ22፥19፤ ዘሌ20፥15፤ ዘዳ27፥21
18፥24 ቍ3፡27፡ 30፤ዘሌ20፥23፤ ዘዳ9፥4፤18፥12
18፥25 ቍ28፤ ዘሌ20፥22፡23፤ ዘኍ35፥34፤ዘዳ9፥5፤1 2፥31፤18፥12፤21፥23 ፤ኢዮ20፥15፤ ኤር51፥34
18፥26 ዘፍ26፥5
18፥28 ቍ25፤ ዘሌ20፥22፤ዕዝ9፥11፤ ሰቆ1፥17

18፥30 ቍ2፤ ዘሌ8፥35 19፥2 ዘፀ20፥2፤ 15፥11፤ዘሌ11፥44፤ 20፥26፤ዘኍ14፥5፤መዝ68፥26፤1ጴጥ1፥16 19፥3 ዘፀ20፥8፡12፤ ዘሌ11፥44 19፥4 ዘፀ20፥4፤ዘሌ11፥44፤መሳ17፥3፤መዝ96፥5፤ 115፥4-7፤ 135፥15

[መ]21 ወይም *በእሳት ውስጥ እንዲያልፍ*
[ሠ]5 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል

ተቀባይነት እንዲያገኝላችሁ አድርጋችሁ
አቅርቡ። 6*መሥዋዕቱም* ባቀረባችሁት ዕለት
ወይም በማግሥቱ ይበላ፤ እስከ ሦስተኛው
ቀን የተረፈ ማንኛውም ነገር ይቃጠል።
7በሦስተኛውም ቀን ቢበላ ርኩስ ነው፤
ተቀባይነትም የለውም። 8ከ*መሥዋዕቱ* የሚ
በላ ማንኛውም ሰው *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ)
የተቀደሰውን ነገር አርክሶአልና ይጠየቅበ
ታል፤ ያም ሰው ከወገኑ ተለይቶ ይጥፋ።
9" 'የምድራችሁን መከር በምትሰበስ
ቡበት ጊዜ፣ በእርሻችሁ ዳርና ዳር ያለውን
አትጨዱ፤ ቃርሚያውንም አትልቀሙ።
10የወይንህን እርሻ አትቃርም፤ የወደቀውንም
አትልቀም፤ ለድኾችና ለመጻተኞች ተውላቸው፤
እኔ *እግዚአብሔር* አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ።
11" 'አትስረቁ፤
" 'አትዋሹ፤
" 'ከእናንተ አንዱ ሌላውን አያታል።
12" 'በስሜ በሐሰት አትማሉ፤ በዚህም
የአምላካችሁን (ኤሎሂም) ስም አታርክሱ፤ እኔ
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ።
13" 'ባልንጀራህን አታጭበርብር፤ አትቀ
ማውም፤
" 'የሙያተኛውን ደመወዝ ሳትከፍል
አታሳድር።
14" 'ደንቈሮውን አትርገም፤ በዐይነ
ስውሩም ፊት ዕንቅፋት አታኑር፤ ነገር
ግን አምላክህን (ኤሎሂም) ፍራ፤ እኔ *እግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) ነኝ።
15" 'ፍርድ አታዛቡ፤ ለድኻው አታድ
ላለት፤ ለትልቁም ሰው ልዩ አክብሮት
አትስጥ፤ ለብርቱው አታዳላ፤ ነገር ግን
ለባለንጀራህ በትክክል ፍረድ።
16" 'በሕዝብህ መካከል ሐሜት አትንዛ፤
" 'የባልንጀራህን ሕይወት አደጋ ላይ
የሚጥል ማንኛውንም ነገር አታድርግ፤ እኔ
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ።
17" 'ወንድምህን በልብህ አትጥላው፤ የበ
ደሉ ተካፋይ እንዳትሆን ባልንጀራህን በግ
ልጽ ገሥጸው።
18" 'ወገንህን አትበቀል፤ ወይም ምቀኛ
አትሁንበት፤ ነገር ግን ባልንጀራህን እንደ
ራስህ ውደድ፤ እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ።
19" '*ሥርዐቴን* ጠብቁ፤
" 'የተለያዩ እንስሳትን አታዳቅል፤
" 'በዕርሻህ ላይ ሁለት ዐይነት ዘር
አትዝራ፤
" 'ከሁለት ዐይነት ነገር የተሠራ ልብስ
አትልበስ።
20" 'አንድ ሰው ለሌላ ከታጨች ሴት
ባሪያ ጋር ግብረ ሥጋ ቢፈጽም፣ ሴቲቱም
ያልተዋጀች ወይም ነጻ ያልወጣች ብትሆን
ይቀጣል፤ ነገር ግን ሴቲቱ ነጻ ስላልወጣች
አይገደሉም። 21ሰውየውም ለበደል *መሥ
ዋዕት* የሚሆን አንድ አውራ በግ ወደ
*መገናኛው ድንኳን* ደጃፍ *ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ያምጣ። 22ካህኑም በበደል *መሥዋዕቱ*
አውራ በግ፣ ሰውየው ስለ ሠራው ኀጢ
አት *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ያስተሰር
ይለታል፤ ኀጢአቱም ይቅር ይባልለታል።
23" 'ወደ ምድሪቱ ገብታችሁ ማንኛ
ውንም ዐይነት ፍሬ የሚሰጥ ዛፍ በምትተ
ክሉበት ጊዜ፣ ፍሬው ለመብላት የተከለከለ
*መሆኑን* ዕወቁ፤ ለሦስት ዓመትም የተከለ
ከለ[a] በመሆኑ አይበላ። 24በአራተኛውም
ዓመት ፍሬው ሁሉ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ)
የተቀደሰ የምስጋና *መሥዋዕት* ይሆናል።
25በአምስተኛው ዓመት ግን ፍሬውን ትበላላ
ችሁ፤ በዚህም ሁኔታ ፍሬው ይበዛላች
ኋል፤ እኔ *እግዚአብሔር* አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም)
ነኝ።
26" 'ደም ያለበትን ማንኛውንም ሥጋ
አትብሉ፤
" 'ጥንቈላ ወይም አስማት አትሥሩ።
27" 'የራስ ጠጕራችሁን ዙሪያ አትከር
ክሙ፤ ጢማችሁንም አሳጥራችሁ አትቀ
ረጡ።
28"ለሞተ ሰው ሰውነታችሁን አትንጩ፤
በሰውነታችሁም ላይ ንቅሳት አታድርጉ፤
እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ።
29" 'ምድሪቱ ወደ ግልሙትና አዘንብላ
በርኵሰት እንዳትሞላ፣ ሴት ልጅህ ጋለሞታ
ትሆን ዘንድ አታዋርዳት።
30" 'ሰንበታቴን ጠብቁ፤ መቅደሴንም
አክብሩ፤ እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ።
31"'እንዳትረክሱባቸው ወደ ሙታን ጠሪ
ዎች ዘወር አትበሉ፤ መናፍስት ጠሪዎችንም
አትፈልጉ፤ እኔ *እግዚአብሔር* አምላካችሁ
(ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ።
32"ዕድሜው ለገፋ ተነሥለት፤ ሽማግ
ሌውን አክብር፤ አምላክህንም (ኤሎሂም) ፍራ፤ እኔ
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ።
33" '*መጻተኛ* በምድራችሁ ላይ አብሮ
አችሁ በሚኖርበት ጊዜ አትበድሉት፤
34አብሮአችሁ የሚኖረው መጻተኛ እንደ ገዛ
ወገናችሁ ይታይ፤ እንደ ራሳችሁም ውደ
ዱት፤ እናንተም በግብፅ መጻተኞች ነበራ

19፥6 ዘሌ7፥16-17
19፥7 ዘሌ7፥18
19፥8 ዘፍ17፥14፤ ዘሌ5፥1፤22፥2፡15፡16 ዘኍ18፥32
19፥9 ዘሌ23፥10፡22፤ዘዳ24፥19-22፤ ሩት2፥2፡3፡7፡16፡17፤ ኢዮ24፥10
19፥10 ቆላ9፤ ዘዳ24፥19፡20፡21
19፥11 ዘፀ20፥15፡16፤23፥4፤ዘሌ6፥2፤ ሉቃ3፥14፤ኤፌ4፥25
19፥12 ዘፀ3፥13፤ 20፥7፤ዘዳ18፥19፤ ኢሳ42፥8፤ኤር5፥2፤ 7፥9፤34፥16፤44፥16፡ 26፤ምሳ18፥10፤ ሚል3፥5፤ማቴ5፥33፤
19፥13 ዘፀ20፥15፤ 22፥15፡25-27፤ ዘሌ25፥14፡17፤ ዘዳ24፥15፤ኢዮ7፥2፤ 24፥12፤31፥39፤ ኢሳ16፥14፤ ኤር22፥13፤ ሚል3፥5፤ማቴ20፥8፤ 1ጢሞ5፥18፤ያዕ5፥4
19፥14 ቆላ32፤ ዘፀ4፥11፤ዘሌ21፥18፤ 25፥17፡36፤ዘዳ27፥18
19፥15 ዘፀ23፥2፡8፤ ዘዳ24፥17፤ኢዮ13፥8፡ 10፤32፥21፤34፥19፤ ምሳ24፥23፤28፥21፤ ሚል2፥9፤ያዕ2፥1-4
19፥16 ዘፀ23፥7፤ ዘዳ10፥17፤27፥25፤ መዝ15፥3፡5፤31፥13፤ 41፥6፤101፥5፤ ኤር6፥28፤9፥4፤ ሕዝ22፥9፡12
19፥17 ማቴ18፥15፤ 1ዮሐ2፥9
19፥18 ቆላ34፤ ዘፍ4፥23፤ዘፀ12፥48፤ 20፥16፤መዝ103፥9፤ ማቴ5፥43፤19፥16፤ 22፥39፤ማር12፥31፤ ሉቃ10፥27፤ ዮሐ13፥34፤ ሮሜ12፥19፤ ገላ5፥14፤ ዕብ10፥30፤ያዕ2፥8
19፥19 ዘፍ26፥5፤ ዘዳ22፥9፡11
19፥20 ዘዳ22፥23-27
19፥21 ዘሌ5፥15
19፥22 ዘሌ5፥15
19፥24 ዘፀ22፥29
19፥26 ዘፍ9፥4፤ 30፥27፤ዘፀ22፥18፤ 2ነገ17፥17፤ ኢሳ44፥25
19፥27 ዘሌ21፥5፤ ዘዳ14፥1፤ 2ሳሙ10፥4-5፤ ኤር41፥5፤48፥37፤ ሕዝ5፥1-5
19፥28 ዘሌ21፥5፤ ዘዳ14፥1፤1ነገ18፥28፤ ኤር16፥6፤41፥5፤47፥5 19፥29 ዘፍ34፥7፤ ዘሌ21፥9፤ዘዳ23፥18
19፥30 ዘፀ20፥8፤ ዘሌ26፥2 19፥31 ዘፀ22፥18፤ ዘሌ20፥6፤ 1ሳሙ28፥7-20፤1ዜና10፥13፤ 2ነገ21፥6፤23፥24፤ኢሳ8፥19፤19፥3፤ 29፥4፤47፥12፤65፥4 19፥32 ቆላ14፤ ዘሌ11፥44፤25፥17፤ 1ነገ12፥8፤ኢዮ29፥8፤ 32፥4፤ምሳ23፥22፤ ሰቆ5፥12፤1ጢሞ5፥1
19፥34 ቆላ፤ዘፀ12፥48፤22፥1፤23፥9፤ዘዳ10፥19፤23፥7፤መዝ146፥9

[a]23 ዕብራይስጡ *ያልተገረዘ* ይላል

ችሁና፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ (ያህዌ
ኤሎሂም) ነኝ፡፡
35“ ‘በመስፈሪያ ወይም በሚዛን አታጭ
በርብሩ፡፡ 36እውነተኛ መለኪያ፣ እውነተኛ
መመዘኛ፣ እውነተኛ የኢፍ[ሰ] መስፈሪያ፣
እውነተኛ የኢን[ሸ] መስፈሪያ ይኑራችሁ፡፡
ከግብፅ ምድር ያወጣኋችሁ እኔ እግዚአብሔር
አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ፡፡ 37“ ‘ሥርዐቴንና
ሕጌን ሁሉ ጠብቁ፤ ተከተሏቸውም፤ እኔ
እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ፡፡’ ”

## ኀጢአት የሚያስከትለው ቅጣት

20 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2“ለእስራኤላውያን እንዲህ
በላቸው፤ ‘ከልጆቹ አንዱን ለሞሎክ የሚሰጥ[ቀ]
ማንኛውም እስራኤላዊ ወይም በእስራኤል
የሚኖር መጻተኛ ይገደል፤ እርሱንም የአ
ገሩ ሕዝብ በድንጋይ ይውገረው፡፡ 3ልጁን
ለሞሎክ በመስጠት መቅደሴን አርክሶአልና፣
ቅዱሱን ስሜንም አቃልሎአልና፣ በዚያ ሰው
ላይ ጠላት እሆንበታለሁ፤ ከወገኖቹም ለይቼ
አጠፋዋለሁ፡፡ 4የአገሩ ሕዝብ፣ ሰውየው
ልጁን ለሞሎክ ሲሰጥ አይተው ቸል ቢሉ፣
ባይገድሉትም፣ 5በዚያ ሰውና በቤተ ሰቡ
ላይ ጠላት እሆናለሁ፤ እርሱንና ከሞሎክ
ጋር በማመንዘር እርሱን የተከተሉትን
ሁሉ ከሕዝባቸው መካከል ለይቼ አጠፋ
ቸዋለሁ፡፡
6“ ‘ወደ ሙታን ጠሪዎችና ጠንቋዮች
ዘወር በማለት፣ በሚከተላቸውና ከእነርሱም
ጋር በሚያመነዝር ሰው ላይ ጠላት እሆንበ
ታለሁ፤ ከወገኖቹም ለይቼ አጠፋዋለሁ፡፡
7“ ‘ራሳችሁን ቀድሱ፤ ቅዱሳንም ሁኑ፤
እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝና፡፡
8ሥርዐቴን ጠብቁ፤ አድርጉትም፤ የምቀድ
ሳችሁ እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ፡፡[በ]
9“ ‘አባቱን ወይም እናቱን የሚረግም
ማንኛውም ሰው ይገደል፤ አባቱን ወይም
እናቱን ረግሞአልና፤ ደሙ በራሱ ላይ ነው፡፡
10“ ‘አንድ ሰው ከባልንጀራው ሚስት
ጋር ቢያመነዝር፣ አመንዝራውና
አመንዝራዪቱ ይገደሉ፡፡
11“ ‘አንድ ሰው ከአባቱ ሚስት ጋር
ግብረ ሥጋ ቢፈጽም አባቱን አዋርዶአል፤
ሰውየውና ሴትዮዋ ይገደሉ፤ ደማቸው በራ
ሳቸው ላይ ነው፡፡
12“ ‘አንድ ሰው ከልጁ ሚስት ጋር
ግብረ ሥጋ ቢፈጽም፣ ሁለቱም ይገደሉ፤ ነውር
አድርገዋልና ደማቸው በራሳቸው ላይ ነው፡፡
13“ ‘አንድ ወንድ ከሴት ጋር ግብረ
ሥጋ እንደሚፈጽም ሁሉ ከወንድ ጋር ቢፈ
ጽም፣ ሁለቱም አስጸያፊ ድርጊት ፈጽመ
ዋልና ይገደሉ፤ ደማቸው በራሳቸው ላይ
ነው፡፡
14“ ‘አንድ ሰው አንዲትን ሴትና እናትዋን
ቢያገባ፣ አድራጎቱ ጸያፍ ነው፤ በመካከ
ላችሁ እንዲህ ዐይነት ርኵሰት እንዳይገኝ
ሰውየውና ሴቶቹ በእሳት ይቃጠሉ፡፡
15“ ‘ማንኛውም ሰው ከእንስሳ ጋር ግብረ
ሥጋ ቢፈጽም፣ ይገደል፤ እንስሳዪቱንም
ግደሏት፡፡
16“ ‘አንዲት ሴት ወደ እንስሳ ቀርባ
ግብረ ሥጋ ብትፈጽም፣ ሴቲቱንና እንስ
ሳውን ግደሉ፤ ደማቸው በራሳቸው ላይ ነው፡፡
17“ ‘አንድ ሰው የአባቱ ወይም የእናቱ
ልጅ የሆነችውን እኅቱን አግብቶ ግብረ
ሥጋ ቢፈጽም፣ አድራጎቱ አሳፋሪ ነው፤
በሕዝባቸው ፊት ከሕዝባቸው ተለይተው
ይጥፉ፡፡ ሰውየው እኅቱን አዋርዶአልና ይጠ
የቅበታል፡፡
18“ ‘ማንኛውም ሰው በወር አበባዋ ጊዜ
ከሴት ጋር ግብረ ሥጋ ቢፈጽም፣ የፈሳሿን
ምንጭ ገልጦአልና፣ እርሷም የፈሳሿን ምንጭ
ገልጣለችና፣ ሁለቱም ከሕዝባቸው መካከል
ተለይተው ይጥፉ፡፡
19“ ‘ከእናትህም ሆነ ከአባትህ እኅት ጋር
ግብረ ሥጋ አትፈጽም፤ ይህ የሥጋ ዝምድ
ናን ማቃለል ስለ ሆነ ሁለታችሁም ትጠየ
ቁበታላችሁ፡፡
20“ ‘ማንኛውም ሰው ከአጎቱ ሚስት
ጋር ግብረ ሥጋ ቢፈጽም፣ አጎቱን አዋርዶ
አልና ሁለቱም ይጠየቁበታል፤ ያለ ልጅም
ይሞታሉ፡፡
21“ ‘ማንኛውም ሰው የወንድሙን ሚስት
ቢያገባ አድራጎቱ ርኵሰት ነው፤ ወንድሙን
አዋርዶአልና፣ ያለ ልጅም ይቀራሉ፡፡
22“ ‘እንድትኖሩባት እናንተን የማስገባባት
ምድር እንዳትተፋችሁ ሥርዐቴንና ሕጌን
ጠብቁ፤ አድርጉም፡፡ 23ከፊታችሁ የማሳድ
ዳቸውን አሕዛብ ልማድ አትከተሉ፤ እነዚ
ህን ሁሉ በማድረጋቸው ተጸየፍኋቸው፡፡
24እናንተ ግን፣ “ምድራቸውን ትወርሳላችሁ፤
ማርና ወተት የምታፈሰውን አገር ርስት
አድርጌ እሰጣችኋለሁ” አልኋችሁ፤ ከአሕ
ዛብ የለየኋችሁ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ
(ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ፡፡
25“ ‘ንጹሕ በሆኑትና ንጹሕ ባልሆኑት
እንስሳት እንዲሁም ንጹሕ በሆኑትና ንጹሕ

19፥35 ዘዳ25፥13-16
19፥36 ዘፀ12፥17፤ ዘዳ25፥13-15፤ መሳ6፥19፤ 1ሳሙ1፥24፤17፥17፤ ሩት2፥17፤ኢዮ31፥6፤ ምሳ11፥1፤ 20፥10፤ ሕዝ45፥10፡11፤ ሆሴ12፥7፤ ሚክ6፥11
19፥37 ዘፍ26፥5፤ 2ነገ17፥37፤ 2ዜና7፥17፤ መዝ119፥5፤ ሕዝ18፥9
20፥2 ቍ10፡27፤ ዘፍ26፥11፤ ዘፀ19፥12፤ ዘሌ24፥14፤ዘኍ15፥35፡36፤ዘዳ21፥21፤ ኢሱ7፥25
20፥3 ቍ5፡6፤ ዘሌ15፥31፤18፥21፤ 23፥30፤መዝ74፥7፤ 79፥1፤ኤር7፥30፤ ሕዝ5፥11
20፥4 ዘዳ17፥2-5
20፥6 ቍ3፤ ዘሌ19፥31
20፥7 ዘፀ6፥2፤ 20፥2፤29፥1፤31፥13፤ ዘሌ11፥44፡45፤ ኤፌ1፥4፤1ጴጥ1፥16
20፥8 ዘፍ26፥5፤ ዘፀ31፥13፤ሕዝ20፥12
20፥9 ቍ11፤ ዘፀ20፥12፤21፥17፤ ዘዳ21፥20፥21፤ 22፥30፤27፥16፤ ኢሱ2፥19፤ 2ሳሙ1፥16፤3፥29፤ 1ነገ2፥37፤ ኤር35፥16፤ ሕዝ18፥13፤22፥7፤ 33፥4፡5፤ሚል1፥6፤ 2፥10፤ማቴ15፥4፤ ማር7፥10
20፥10 ዘፍ38፥24፤ ዘፀ20፥14፤21፥12፤ ዘዳ5፥18፤22፥22፤ ዮሐ8፥5
20፥11 ቍ9፤ ዘሌ18፥7፡8
20፥12 ዘፍ11፥31፤ 38፥16
20፥13 ዘሌ18፥22
20፥14 ዘሌ18፥17፤ 21፥9፤ዘሌ18፥8፤ ዘኍ16፥39፤ዘዳ27፥23፤መሳ14፥15፤15፥6
20፥15 ቍ10፤ ዘፀ22፥19
20፥17 ዘፍ17፥14፤ ዘሌ5፥1፤18፥9
20፥18 ዘሌ15፥24፤ ሕዝ18፥6
20፥19 ዘሌ18፥12
20፥20 ቍ21፤ ዘፍ15፥2፤ዘሌ18፥13
20፥21 ቍ20፤ ዘሌ18፥16፤ማቴ14፥4፤ማር6፥18
20፥22 ዘፍ26፥5፤ ዘሌ18፥25-28 20፥23 ዘሌ18፥3፡ 24፡25
20፥24 ዘፀ3፥8፤ 33፥16፤ዘኍ14፥8፤ 16፥14
20፥25 ዘሌ10፥10፤ ዘዳ14፥3-21፤ ሐሥ10፥14

[ሰ]36 ኢፍ የደረቅ ነገር መለኪያ/መስፈሪያ ነው
[ሸ]36 ኢን የፈሳሽ ነገር መለኪያ ነው
[ቀ]2 ወይም *የሚሠዋ*፤ እንዲሁም ቍ 3፡4 ይመ
[በ]8 ወይም *ቅዱስ አድርጌ የምለያችሁ*

ባልሆኑት ወፎች መካከል ልዩነት አድርጉ::
ርኩስ ነው ብዬ በለየሁት በማንኛውም
እንስሳ ወይም ወፍ ወይም በምድር ላይ
በሚንቀሳቀስ በማንኛውም ነገር ራሳችሁን
አታርክሱ:: 26እናንተ ለእኔ ቅዱሳን ትሆኑ
ልኛላችሁ፤[ተ] እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ቅዱስ
ነኝና፤ የኔ ትሆኑ ዘንድ ከአሕዛብ መካከል
ለይቻችኋለሁ::
27“ ‘ከመካከላችሁ ሙታን ጠሪ ወይም
መናፍስት ጠሪ የሆነ ማንኛውም ወንድ
ወይም ሴት ይገደል፤ በድንጋይም ይወገሩ፤
ደማቸው በራሳቸው ላይ ነው::’ ”

## ለካህናት የተሰጠ መመሪያ

21 *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ “ለካህናቱ ለአሮን ልጆች
ንገራቸው፤ እንዲህም በላቸው፤ ‘ማንኛውም
ሰው ከዘመዶቹ መካከል ስለ ሞተው ሰው
ራሱን አያርክስ፤ 2ነገር ግን የቅርብ ዘመ
ዶቹ ስለሆኑት እናቱ፣ አባቱ፣ ወንድ ልጁ፣
ሴት ልጁ፣ ወይም ወንድሙ፣ 3እንዲሁም
ባለማግባቷ ከእርሱ ጋር ስለ ምትኖር
እኅቱ ራሱን ሊያረክስ ይችላል:: 4ከእርሱ
ጋር በጋብቻ ለሚዛመዱት[ቸ] ግን ራሱን
አያርክስ::
5“ ‘ካህናት ዐናታቸውን አይላጩ፤ የጢ
ማቸውን ዙሪያ አይላጩ፤ ሰውነታቸውንም
አይንጩ፤ 6ለአምላካቸው (ኤሎሂም) የተቀደሱ
ይሁኑ፤ የአምላካቸውንም (ኤሎሂም) ስም አያርክሱ::
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በእሳት የሚቀርበውን
መሥዋዕት የአምላካቸውን (ኤሎሂም) ምግብ
ስለሚ ያቀርቡ ቅዱሳን ይሁኑ::
7“ ‘ካህናት በዝሙት የረከሱትንም ሆነ
ከባሎቻቸው የተፋቱትን ሴቶች አያግቡ፤
*ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) የተቀደሱ ናቸውና::
8የአምላክህን (ኤሎሂም) ምግብ የሚያቀርብ ነውና
ቀድሰው፤ እኔ የምቀድሳችሁ[ኀ] *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ቅዱስ ነኝና ቅዱስ ይሁንላችሁ::
9“ ‘የካህን ሴት ልጅ ዝሙት አዳሪ
ሆና ራሷን ብታረክስ፣ አባቷን ታዋርዳለች፤
በእሳት ትቃጠል::
10“ ‘ከወንድሞቹ መካከል ተለይቶ በራሱ
ላይ ዘይት የፈሰሰበትና የክህነት ልብስ
እንዲለብስ የተቀባው ካህን የራስ ጠጕሩን
አይንጭ፤[ነ] ወይም ልብሱን አይቅደድ::
11አስከሬን ወዳለበት ስፍራ አይግባ፤ ስለ
አባቱም ሆነ ስለ እናቱ ራሱን አያርክስ::
12የተቀደሰበት የአምላኩ (ኤሎሂም) የቅባት ዘይት
በላዩ ስለ ሆነ የአምላኩን (ኤሎሂም) መቅደስ ትቶ
በመሄድ መቅደሱን አያርክስ፤ እኔ *እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ነኝ::
13“ ‘ካህኑ የሚያገባት ሴት ድንግል
ትሁን:: 14ባል የሞተባትን፣ የተፋታችውን
ወይም በዝሙት ዐዳሪነት የረከሰችውን
ሴት አያግባ፤ ነገር ግን ከወገኖቹ መካከል
ድንግሊቱን ያግባ:: 15በወገኖቹ መካከል
ዘሩን አያርክስ:: እርሱን የምቀድሰው[ኘ]
እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ::’ ”
16*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 17“አሮንን እንዲህ በለው፤ ‘በሚቀ
ጥሉት ትውልዶች ከዘርህ እንከን ያለበት
ማንኛውም ሰው የአምላኩን (ኤሎሂም) ምግብ
ይሠዋ ዘንድ አይቅረብ:: 18ዕውር ወይም
አንካሳ፣ የፊቱ ገጽታ ወይም የሰውነቱ
ቅርጽ የተበላሸ ማንኛውም የአካል ጕድ
ለት ያለበት ሰው አይቅረብ:: 19እንዲሁም
እግሩ ወይም እጁ ሽባ የሆነ፣ 20ጐባጣ
ወይም ድንክ፣ ማንኛውም ዐይነት የዐይን
እንከን ያለበት፣ የሚያዥ ቍስል ወይም
እከክ ያለበት ወይም ጃንደረባ አይቅረብ::
21ከካህኑ ከአሮን ዘር ማንኛውም ዐይነት
የአካል ጕድለት ያለበት ሰው *ለእግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) በእሳት የሚቀርብ መሥዋዕት
ሊያቀርብ አይምጣ፤ እንከን ያለበት ስለ
ሆነ፣ የአምላኩን (ኤሎሂም) ምግብ ለማቅረብ
አይምጣ:: 22እርሱም የተቀደሰውንና እጅግ
ቅዱስ የሆነውን የአምላኩን (ኤሎሂም) ምግብ
ይብላ:: 23ነገር ግን እንከን ያለበት ስለሆነ
መቅደሴን እንዳያረክስ ወደ መጋረጃው
አይቅረብ ወይም ወደ መሠዊያው አይጠጋ፤
የምቀድሳቸው[አ] እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
ነኝ::’ ”
24ሙሴም ይህን ለአሮን፣ ለልጆቹና
ለእስራኤላውያን ሁሉ ነገራቸው::

22 *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2“እስራኤላውያን ቀድሰው
ለእኔ የለዩትን ቅዱስ መሥዋዕት በአክ
ብሮት ባለመያዝ፣ ቅዱስ ስሜን እንዳ
ያረክሱ ለአሮንና ለልጆቹ ንገራቸው፤ እኔ
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ::
3“እንዲህም በላቸው፤ ‘በሚቀጥሉት ትውል
ዶች ከዘርህ በሥርዐቱ መሠረት ንጹሕ
ያልሆነ ማንኛውም ሰው፣ እስራኤላውያን
*ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) ለይተው ወዳቀረቡት
ቅዱስ መሥዋዕት ቢቀርብ ያ ሰው ከፊቴ
ይወገድ፤ እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ::
4“ ‘ከአሮን ዘር ተላላፊ የቈዳ በሽታ[ከ]
ያለበት ወይም ከሰውነቱ ፈሳሽ ነገር የሚወ

20፥26 ቍ8፤ ዘፀ33፥16፤ዘሌ19፥2፤ ዘዳ14፥2፤ኢሱ24፥19 2ነገ19፥22፤ መዝ99፥3
20፥27 ቍ2፤ ዘፀ22፥18፤ ዘሌ19፥31፤24፥14
21፥1 ቍ11፤ ዘፀ28፥1፤ዘሌ1፥5፤ 5፥3፤13፥3፤ዘኍ5፥2፤ 6፥6፤19፥11፤31፥19
21፥2 ቍ11
21፥3 ዘኍ6፥6
21፥5 ዘሌ13፥40፤ 19፥28፤ኤር7፥29፤ 16፥6፤ሕዝ5፥1፤ 44፥20
21፥6 ቍ8:17: 22፤ዘፀ19፥22፤ ዘሌ3፥11፤10፥3፤18፥ 21፤22፥25፤ዕዝ8፥28
21፥7 ቍ13:14፤ ሕዝ44፥22
21፥8 ቍ6፤ ዘፀ31፥13፤ዘሌ3፥11
21፥9 ዘፍ38፥24፤ ዘሌ19፥29
21፥10 ዘፀ29፥7፤ ዘሌ8፥7-9:13፤ 10፥6፤16፥4
21፥11 ቍ2፤ ዘሌ19፥28፤ዘኍ5፥2፤ 6፥6፤9፥6፤19፥11:13: 14፤31፥19
21፥12 ዘፀ25፥8፤ 28፥41
21፥13 ሕዝ44፥22
21፥17 ቍ6:18: 21:23
21፥18 ዘሌ19፥14፤ 22፥19-25፤ 2ሳሙ4፥4፤9፥3፤ 19፥26
21፥20 ዘሌ22፥24፤ ዘዳ23፥1፤ኢሳ56፥3
21፥21 ቍ17፤ ዘሌ3፥11፤22፥19
21፥22 1ቆሮ9፥13
21፥23 ቍ17፤ ዘፀ25፥8፤ዘሌ20፥8
22፥2 ዘፀ20፥7፤ ዘሌ19፥8፤ሕዝ44፥8፤ ማቴ5፥33
22፥3 ዘሌ7፥20:21፤ ዘኍ19፥13፤ ዕዝ8፥28
22፥4 ዘሌ15፥2-15፤ 11፥24-28:39

[ተ]26 ወይም ለእኔ *ቅዱሳን ትሆኑልኛላችሁ*
[ቸ]4 ወይም *እንደ መሪነቱ በሕዝቡ መካከል ራሱን አያርክስ::*
[ኀ]8 ወይም *ቅዱስ አድርጌ የምለያችሁ እኔ እግዚአብሔር*
[ነ]10 ወይም *ጠጕሩን አይላጭ::*
[ኘ]15 ወይም *ቅዱስ አድርጌ የምለየው*
[አ]23 ወይም ቅዱስ አድርጌ የምለያቸው
[ከ]4 በትውፊት ለምጽ ይባላል፤ የዕብራይስጡ ቃል ለምጽ ብቻ ሳይሆን ከቈዳ ጋር የተያያዘ በሽታን ያመለክታል

ጣው ማንኛውም ሰው እስኪነጻ ድረስ
ቅዱሱን *መሥዋዕት* አይብላ፤ እንዲሁም
በአስከሬን የረከሰውን ነገር ወይም የዘር
ፈሳሽ ያለበትን ሰው ቢነካ፣ 5ወይም በደ
ረቱ የሚሳብ የሚያረክስ ነገርን ወይም
የሚያረክስ ማንኛውንም ሰው ቢነካ፣ የቱንም
ዐይነት ርኵሰት ቢሆን፣ 6እንዲህ ያለውን
ማንኛውንም ነገር የሚነካ እስከ ማታ
ድረስ ርኩስ ይሆናል፤ ሰውነቱንም በውሃ
ካልታጠበ፣ ለእግዚአብሔር የተቀደሰውን
*መሥዋዕት* አይብላ። 7ፀሓይ በምትጠልቅበት
ጊዜ ንጹሕ ይሆናል፤ ከዚያም በኋላ የተቀ
ደሰውን *መሥዋዕት* መብላት ይችላል፤
ምግቡ ነውና። 8እንዳይረክስ ማንኛውንም
ሞቶ የተገኘውን ወይም አውሬ የዘነጠለውን
አይብላ፤ እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ።
9“ ‘ካህናት ትእዛዛቴን በመናቅ በደለኛ
እንዳይሆኑና እንዳይሞቱ ይጠብቋቸው፤ የምቀ
ድሳቸው[ኸ] እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ።
10“ ‘ከካህን ቤተሰብ በቀር የካህኑ እንግ
ዳም ሆነ ቅጥር ሠራተኛ የተቀደሰውን
*መሥዋዕት* አይብላ። 11ነገር ግን ካህኑ በገ
ንዘብ የገዛው ወይም በቤቱ የተወለደ ባሪያ
ቢኖረው፣ ያ ባሪያ ከካህኑ ድርሻ መብላት
ይችላል። 12የካህን ልጅ፣ ካህን ያልሆነ
ሌላ ሰው ካገባች፣ ከተቀደሰው *መሥዋዕት*
መብላት አትችልም። 13ይሁን እንጂ የካ
ህኑ ልጅ ባሏ ቢሞት ወይም ብትፋታ፣ ልጆ
ችም ባይኖሩዋትና እንደ ልጅነት ጊዜዋ
በአባቷ ቤት ለመኖር ብትመለስ፣ ከአባቷ
ድርሻ መብላት ትችላለች፤ ያልተፈቀደ
ለት ሰው ግን ከተቀደሰው *መሥዋዕት* መብ
ላት አይችልም።
14“ ‘ማንኛውም ሰው ባለማወቅ የተቀደ
ሰውን *መሥዋዕት* ቢበላ፣ የ*መሥዋዕቱ*ን
አንድ አምስተኛ ጨምሮ ለካህኑ ይተካ።
15እስራኤላውያን *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) የሚ
ያቀርቡትን የተቀደሰ *መሥዋዕት* ካህናቱ
አያርክሱት፤ 16ይህንኑ የተቀደሰ *መሥዋዕት*
እንዲበሉና ቅጣት የሚያስከትል በደል
እንዲፈጽሙ አያድርጉ፤ የምቀድሳቸው እኔ
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ።

### ለእግዚአብሔር መቅረብ የማይገባው *መሥዋዕት*

17*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤
18“ለአሮን፣ ለልጆቹና ለእስራኤላውያን በሙሉ
እንዲህ ብለህ ተናገር፤ ‘ከእናንተ ማንኛ
ውም እስራኤላዊ ወይም በእስራኤል የሚኖር
መጻተኛ ስእለት ለመፈጸም ወይም የበጎ
ፈቃድ ስጦታ ለማበርከት *ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) የሚቃጠል *መሥዋዕት* የሚያቀርብ
ቢሆን፣ 19*መሥዋዕታችሁ* ተቀባይነት እንዲ
ኖረው ከላም ወገን ወይም ከበጎች ወይም
ከፍየሎች እንከን የሌለበትን ተባዕት ያቅ
ርብ። 20እንከን ያለበትን ማንኛውንም ነገር
አታቅርቡ፤ *መሥዋዕታችሁ* ተቀባይነት አይ
ኖረውምና። 21ማንኛውም ሰው ስእለት ለመ
ፈጸም ወይም የበጎ ፈቃድ ስጦታ ለማበ
ርከት ከላም ወይም ከበግ ወይም ከፍየል
*መንጋ ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) የኅብረት *መሥዋ
ዕት*[ሠ] ሲያቀርብ፣ ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ
ፍጹም የሆነውንና ነውር የሌለበትን ያቅ
ርብ። 22ዕውር ወይም ሰባራ ወይም ጒን
ድሽ ወይም ማንኛውንም ዐይነት እከክ
ወይም ቋቍቻ ወይም የሚመግል ቍስል
ያለበትን እንስሳ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) አታ
ቅርቡ፤ ከነዚህ መካከል የትኛውንም በመ
ሠዊያው ላይ በእሳት የሚቃጠል *መሥ
ዋዕት* አድርጋችሁ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ)
አታቅርቡ። 23አካሉ ከመጠን በላይ የረዘ
መን ወይም ያጠረን በሬ[ዐ] ወይም በግ
የበጎ ፈቃድ ስጦታ አድርጋችሁ ማቅረብ
ትችላላችሁ፤ ይሁን እንጂ ስእለት ለመፈጸም
ተቀባይነት አይኖረውም፤ 24አባለዘሩ የተ
ቀጠቀጠ ወይም የተኰላሸ፣ የተሰነጠቀ
ወይም የተቈረጠ ማንኛውንም እንስሳ
*ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) አታቅርቡ፤ እነዚህ
ንም በምድራችሁ አትሠው። 25እንደነዚህ
ያሉትን እንስሳት ከባዕዳን በመቀበል
ስለ*ምላካችሁ* (ኤሎሂም) ምግብ አድርጋችሁ አታ
ቅርቡ፤ ነውር ስላለባቸው ፍጹም አይደ
ሉምና ተቀባይነት አይኖራቸውም።’ ”
26*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 27“ጥጃ ወይም የበግ ግልገል ወይም
የፍየል ግልገል በሚወለድበት ጊዜ ሰባት
ቀን ከእናቱ ጋር ይቈይ፤ ከስምንተኛው
ቀን ጀምሮ ግን ተቀባይነት ያለው *ለእግ
ዚአብሔር* (ያህዌ) በእሳት የሚቀርብ *መሥዋዕት*
ይሆናል። 28ላምን ከጥጃዋ፣ በግንም ከግልገሏ
ጋር በአንድ ቀን አትረዱ።
29“*ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) የምስጋና *መሥ
ዋዕት* በምታቀርቡበት ጊዜ፣ *መሥዋዕታችሁ*
ተቀባይነት እንዲኖረው አድርጋችሁ አቅር
ቡት። 30*መሥዋዕቱ* በዚያኑ ዕለት ይበላ፤
ለሚቀጥለውም ቀን አታሳድሩ፤ እኔ *እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ነኝ።
31“ትእዛዛቴን ጠብቁ፤ አድርጓቸውም፤
እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ። 32ቅዱሱን ስሜን
አታርክሱ፤ እኔ ቅዱስ መሆኔ በእስራኤላ
ውያን ዘንድ ይታወቅ፤ የምቀድሳችሁ[ዘ][ዠ]

[ኸ]9 ወይም ቅዱስ አድርጌ የምለያቸው፤ እንዲሁም ቍ 16 ይመ።
[ሠ]21 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል።
[ዐ]23 የዕብራይስጡ ቃል ተባዕትና እንስትን ሊያጠቃልል ይችላል።
[ዘ]32 ወይም *የቀደስኋችሁ*
[ዠ]32 ወይም *ቅዱስ አድርጌ የምለያችሁ*

22፥5 ዘሌ11፥24-28፡43፤15፥7
22፥6 ዘሌ11፥24፤14፥8፤ሐጌ2፥13
22፥7 ዘኍ18፥11
22፥8 ዘፀ22፥31፤ ዘሌ11፥39፡40፡44፤
22፥9 ቍ16፤ ዘፀ28፥38፡43፤ ዘሌ8፥35፤20፥8፤
22፥10 ቍ13፤ ዘፀ12፥45፤29፥33
22፥11 ዘፍ17፥13፤ ዘፀ12፥44
22፥14 ዘሌ4፥2፤5፥15
22፥15 ዘሌ19፥8፤ ዘኍ18፥32
22፥16 ቍ9፤ ዘፀ28፥38፤ ዘሌ20፥8፤ ዘኍ18፥11
22፥18 ቍ21፤ ዘፍ28፥20፤ዘሌ1፥2፤7፥16፤ዘኍ15፥8፡16፤19፥10፤ኢሱ8፥33፤መዝ22፥25፤76፥11፤116፥18፤
22፥19 ዘሌ1፥2፡3፤21፥18-21፤ ዘኍ28፥11፤ ዘዳ15፥21፤
22፥20 ዘፀ28፥38፤ ዘሌ1፥3፤ዘዳ15፥21፤17፥1፤ሕዝ43፥23፤45፥18፤46፥6፤ ሚል1፥8፤ዕብ9፥14፤ 1ጴጥ1፥19፤
22፥21 ዘፀ12፥5፤32፥6፤ዘሌ1፥2፤3፥6፤7፥16፤አሞ4፥5፤ ሚል1፥14
22፥24 ዘሌ21፥20
22፥25 ዘሌ21፥6፤1፥3፤ 3፥1፤ዘኍ19፥2
22፥27 ዘፀ22፥30፤28፥38፤ዘሌ1፥3፤
22፥28 ዘዳ22፥6፡7
22፥29 ዘሌ7፥12
22፥30 ዘሌ7፥15፤11፥44
22፥31 ዘፀ22፥31፤ ዘዳ4፥2፡40፤ መዝ105፥45፤
22፥32 ዘሌ10፥3፤18፥21፤20፥8

እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ:: [33]ሰምላካችሁ
(ኤሎሂም) እሆን ዘንድ ከግብፅ ምድር ያወጣ
ኋችሁ እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ::

# 23

*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ [2]“ለእስራኤላውያን እንዲህ
ብለህ ተናገር፤ ‘የተቀደሱ ጉባኤዎች ብላችሁ
የምትዋጇቸው የተመረጡ *የእግዚአብሔር*
(ያህዌ) በዓላት እነዚህ ናቸው፤

## ሰንበት

[3]“ ‘*ሥራ* የምትሠሩበት ስድስት ቀን
አላችሁ፤ ሰባተኛው ቀን ግን የዕረፍት ሰን
በት፣ የተቀደሰ ጉባኤ ዕለት ነው:: *የእግ
ዚአብሔር* (ያህዌ) ሰንበት ስለ ሆነ፣ በምት
ኖሩበት ስፍራ ሁሉ ምንም ዐይነት *ሥራ*
አት*ሥ*ሩበት::

## የፋሲካና የቂጣ በዓል

23፥4-8 ተጓ ምብ - ዘፀ 12፥14-20፤ ዘኍ 28፥16-25፤ ዘዳ 16፥1-8

[4]“ ‘የተመረጡ *የእግዚአብሔር* (ያህዌ) በዓ
ላት ብላችሁ በተወሰኑላቸው ጊዜያት የምታ
ውጇቸው የተቀደሱ ጉባኤዎች እነዚህ
ናቸው፤ [5]*የመጀመሪያው* ወር በገባ በዐ*ሥራ*
*አራተኛው* ቀን ምሽት *የእግዚአብሔር* (ያህዌ)
ፋሲካ በዓል ይጀመራል:: [6]በዚያው ወር
በዐ*ሥራ* አምስተኛው ቀን *የእግዚአብሔር*
(ያህዌ) የቂጣ በዓል ይጀመራል፤ ሰባት ቀንም
ያለ እርሾ የተጋገረ ቂጣ ትበላላችሁ:: [7]በመጀ
*መሪያው* ቀን የተቀደሰ ጉባኤ አድርጉ፤
የዕለት ተግባራችሁንም አታከናውኑ:: [8]ሰባት
ቀን በእሳት የሚቃጠል *መሥዋዕት* *ለእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) አቅርቡ፤ በሰባተኛው ቀን የተ
ቀደሰ ጉባኤ አድርጉ፤ በዚያ ዕለት የተለመደ
ተግባራችሁን አታከናውኑ::’ ”

## የበኵራት ስጦታ በዓል

[9]*እግዚአብሔር* (ያህዌ)ሙሴን እንዲህ አለው፤
[10]“ለእስራኤላውያን እንዲህ ብለህ ተናገር፤
‘እኔ ወደምሰጣችሁ ምድር ገብታችሁ መከር
በምትሰበስቡበት ጊዜ ከሰበሰባችሁት እህል
*የመጀመሪያውን* ነዶ ለካህኑ አቅርቡ፤
[11]ነዶው ተቀባይነት እንዲያገኝላችሁም *በእግ
ዚአብሔር* (ያህዌ) *ፊት* ይወዝውዘው፤ ካህኑ
ነዶውን የሚወዘውዘው በሰንበት ቀን ማግ
ስት ነው:: [12]ነዶውን በምትወዘውዙበት
ቀን እንከን የሌለበትን የአንድ ዓመት
ተባዕት የበግ ጠቦት የሚቃጠል *መሥዋዕት*
እንዲሆን *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) አቅርቡ፤
[13]ከዚህም ጋር *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) በእሳት
የሚቀርብ፣ ሽታውም ደስ የሚያሰኝ እን
ዲሆን ሁለት ዐሥረኛ የኢፍ[የ] መስፈሪያ በዘይት
የተለወሰ የላመ ዱቄት ለእህል ቍርባን፣
አንድ አራተኛ የኢን[ዩ] መስፈሪያ የወይን ጠጅ

22፥33 ዘፍ17፥7፤ ዘፀ6፥6፤
23፥2 ቍ4:21: 27:37:44፤ ዘኍ29፥30፤ ሕዝ44፥24፤ ቈላ2፥16፤
23፥3 ቍ7:21: 35፤ዘፀ20፥9:10፤ ዘኍ28፥6፤ ዕብ4፥9: 10፤
23፥4 ናሆ1፥15
23፥5 ዘፀ12፥6:11
23፥6 ዘፀ12፥17:19
23፥7 ቍ3:8
23፥8 ዘሌ1፥9
23፥10 ዘፀ22፥29፤ 34፥22፤ዘሌ19፥9፤ ዘኍ15፥2:18፤ ሮሜ11፥16
23፥11 ዘፀ28፥38፤ 29፥24
23፥12 ዘፀ12፥5፤ ዘሌ12፥6፤
23፥13 ቍ17፤ ዘፍ35፥14፤ ዘሌ 2፥14-16፤ 6፥20፤ 10፥9፤24፥5፤ ዘኍ15፥6፤28፥9
23፥14 ዘፀ34፥26፤ ዘሌ3፥17፤ዘኍ10፥8፤ 15፥21፤ኢሱ5፥11፤ 1ሳሙ17፥17፤25፥18 2ሳሙ17፥28፤ ሩት2፥14፤ኤር2፥3
23፥16 ሐሥ2፥1፤ 20፥16
23፥17 ቍ13፤ ዘፀ34፥22
23፥18 ቍ13፤ ዘፀ29፥41፤30፥9፤ 37፥16፤ኤር19፥13፤ 44፥18
23፥20 ዘፀ29፥24
23፥21 ቍ3:2፤ ዘፀ32፥5፤
23፥22 ዘሌ19፥9: 10፤ዘዳ24፥19-21፤ ሩት2፥2:15
23፥24 ቍ27:36፤ ዘሌ25፥9፤ዘኍ10፥9: 10፤29፥1፤31፥6፤ 2ነገ11፥14፤ 2ዜና13፥12፤ዕዝ3፥1፤ መዝ98፥6

*ለመጠጥ* ቍርባን አቅርቡ:: [14]ስጦታውን
ለሰምላካችሁ (ኤሎሂም) እስከምታቀርቡበት እስ
ከዚያ ቀን ድረስ እንጀራም ቢሆን፣ ቈሎ
ወይም እሸት አትብሉ፤ ይህም በምትኖሩበት
ስፍራ ሁሉ ለሚመጡት ትውልዶች የዘ
ላለም *ሥ*ርዐት ነው::

## የመከር በዓል

23፥15-22 ተጓ ምብ - ዘኍ28:26-31፤ ዘዳ 16፥9-12

[15]“ ‘የሚወዘወዘውን የነዶ *መሥዋዕት*
ካቀረባችሁበት የሰንበት ማግስት አን*ሥ*ታ
ችሁ ሰባት ሙሉ ሳምንታት ቍጠሩ::
[16]እስከ ሰባተኛው ሰንበት ማግስት ድረስ
አምሳ ቀን ቍጠሩ፤ ከዚያም የአዲስ እህል
ቍርባን *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) አቅርቡ:: [17]በሁ
ለት ዐ*ሥ*ረኛ የኢፍ *መስፈሪያ* የላመ
ዱቄት፣ በእርሾ የተጋገረ ሁለት እንጀራ
ለሚወዘወዝ *መሥዋዕት*፣ የበኵራት ስጦታ
እንዲሆን ከየቤታችሁ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ)
አምጡ:: [18]ከእንጀራውም ጋር ሰባት ነውር
የሌለባቸው የአንድ ዓመት ተባዕት የበግ
ጠቦቶች፣ አንድ ወይፈንና ሁለት አውራ
በጎች አቅርቡ፤ እነዚህም ከእህል ቍርባና
ቸውና ከመጠጥ ቍርባናቸው ጋር *ለእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) የሚቃጠል *መሥዋዕት* ይሆናሉ፤
ይህም በእሳት የሚቀርብ ሽታውም *እግዚ
አብሔርን* (ያህዌ) ደስ የሚያሰኝ *መሥዋዕት*
ነው:: [19]እንዲሁም አንድ ተባዕት ፍየል
ለኀጢአት *መሥዋዕት*፣ ሁለት የአንድ *ዓመት*
ተባዕት ጠቦቶችም ለኅብረት *መሥዋዕት*[ጀ]
አቅርቡ:: [20]ካህኑም ሁለቱን የበግ ጠቦቶች
ከበኵራቱ እንጀራ ጋር የሚወዘወዝ *መሥ
ዋዕት* አድርጎ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) *ፊት*
ይወዘውዛቸዋል፤ እነዚህም *ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ቅዱስ *መሥዋዕት*፣ የካህኑም ድርሻ
ናቸው:: [21]በዚያኑ ዕለት የተቀደሰ ጉባኤ
ዐውጁ፤ የተለመደ ተግባራችሁንም አታከ
ናውኑ፤ ይህም በምትኖሩበት ስፍራ ሁሉ
ለሚመጡት ትውልዶች የዘላለም *ሥ*ርዐት
ነው::
[22]“ ‘የምድራችሁን መከር በምትሰበስ
ቡበት ጊዜ፣ የዕርሻችሁን ዳርና ዳር አት
ጨዱ፤ ቃርሚያውን አትልቀሙ፤ እነዚህንም
ለድኾችና ለእንግዶች ተዉላቸው፤ እኔ
*እግዚአብሔር* ሰምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ::’

## የመለከት በዓል

23፥23-25 ተጓ ምብ - ዘኍ 29፥1-6

[23]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ [24]“እስራኤላውያንን እንዲህ በላቸው፤
‘የሰባተኛው ወር የመጀመሪያ ቀን ዕረፍት

[የ]13 4.5 ሊትር ገደማ ይሆናል፤ እንዲሁም ቍ17 ይመ
[ዩ]13 1 ሊትር ገደማ ይሆናል
[ጀ]19 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል

ይሁንላችሁ፤ በዚሁ በመለከት ድምፅ የሚ
ከበር የተቀደሰ ጉባኤ ይኑራችሁ:: 25መሥ
ዋዕትን በእሳት *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) አቅርቡ
እንጂ የተለመደ ተግባራችሁን አታከናው
ኑበት::’ ”

## የስርየት ቀን

23፥26-32 ተጓ ምብ - ዘሌ 16፥2-34፤ ዘኍ 29፥7-11

26*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 27“የሰባተኛው ወር ዐሥረኛ ቀን
የስርየት ቀን ነው፤ የተቀደሰ ጉባኤ አድ
ርጉ፤ አንዳች ነገርም አትብሉ፤[ገ] መሥዋዕ
ትም በእሳት *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) አቅርቡ::
28*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) በአምላካችሁ (ኤሎሂም)
ፊት ለእናንተ ስርየት የሚደረግበት የስር
የት ቀን ስለ ሆነ፣ በዚያ ዕለት ምንም ሥራ
አትሥሩ:: 29በዚያ ዕለት ሰውነቱን የሚያ
ጕሳቍል ማንኛውም ሰው ከወገኖቹ መካ
ከል ተለይቶ ይጥፋ:: 30በዚያ ዕለት ማንኛ
ውንም ሥራ የሚሠራውን ሰው ሁሉ ከወ
ገኖቹ መካከል ለይቼ አጠፋዋለሁ:: 31ማን
ኛውንም ሥራ ከቶ አትሥሩበት፤ ይህ በም
ትኖሩበት ስፍራ ሁሉ ለልጅ ልጆቻችሁ
የዘላለም ሥርዐት ነው:: 32ይህ ለእናንተ
የዕረፍት ሰንበት ስለ ሆነ፣ ራሳችሁን ዝቅ
ዝቅ አድርጉ* በወሩም ከዘጠነኛው ቀን
ምሽት ጀምራችሁ እስከሚቀጥለው ቀን
ምሽት ድረስ ሰንበታችሁን አክብሩ::”

## የዳስ በዓል

23፥33-43 ተጓ ምብ - ዘኍ 29:12-39፤ ዘዳ 16፥13-17

33*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 34“እስራኤላውያንን እንዲህ በላቸው፤
‘ሰባተኛውም ወር በገባ በዐሥራ አምስተኛው
ቀን *የእግዚአብሔር* (ያህዌ) የዳስ በዓል ይጀም
ራል፤ እስከ ሰባት ቀንም ይቆያል:: 35የመ
ጀመሪያው ቀን የተቀደሰ ጉባኤ ነውና የተ
ለመደ ተግባራችሁን አታከናውኑበት:: 36ሰባት
ቀን መሥዋዕቱን በእሳት *ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) አቅርቡ፤ በስምንተኛው ቀን የተቀደሰ
ጉባኤ አድርጉ፤ መሥዋዕትን በእሳት *ለእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) አቅርቡ፤ የተለመደ ተግባራች
ሁንም አታከናውኑበት::
37“ ‘የሚቃጠል መሥዋዕትንና የእህል
ቍርባንን፣ መሥዋዕትንና የመጠጥ ቍርባ
ንን በተመደበላቸው ቀን *ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) በእሳት ለማቅረብ፣ የተቀደሱ ጉባኤ
ዎችን የምታውጁባቸው *የእግዚአብሔር*
(ያህዌ) በዓላት እነዚህ ናቸው:: 38እነዚህ መሥ
ዋዕቶች *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) ሰንበት ከም
ታቀርቡት፣ ከስጦታችሁ፣[ጠ] ከስእለታችሁና
ከበጎ ፈቃድ ስጦታችሁ በተጨማሪ የምታ
ቀርቧቸው ስጦታዎች ናቸው::
39“ ‘የምድራችሁን ፍሬ ከሰበሰባችሁ

23፥25 ቍ21፤ ዘሌ1፥9
23፥27 ቍ2:24፤ ዘፀ30፥10፤ ዘሌ16፥29፤
23፥28 ቍ31
23፥29 ዘፍ17፥14፤ ዘሌ7፥20፤ዘኍ5፥2
23፥30 ዘሌ20፥3
23፥31 ዘሌ3፥17
23፥32 ዘሌ16፥31፤ ነህ13፥19
23፥34 ዘፀ23፥16፤ 1ነገ8፥2፤ሐጌ2፥1፤ ዮሐ7፥2
23፥35 ቍ2:3
23፥36 ቍ24፤ ዘሌ1፥9፤1ነገ8፥2፤ 2ዜና7፥9፤ነህ8፥18፤ ዮሐ7፥37፤
23፥37 ቍ13
23፥38 ዘፀ20፥10፤ ዘሌ1፥2፤7፥16፤ 2ዜና2፥4፤ሕዝ45፥17
23፥39 ዘፀ23፥16፤ ኢሳ62፥9፤
23፥40 ዘዳ12፥7፤ 14፥26፤28፥47፤ ነህ8፥10:14-17፤ መዝ9፥2፤66፥6፤ 105፥43፤118፥27፤ 137፥2፤ኢሳ44፥4፤ ኢል2፥26
23፥42 ዘፀ23፥16
23፥43 መዝ78፥5
24፥3 ዘፀ12፥14
24፥4 ዘፀ25፥31
24፥5 ዘፀ25፥30፤ ዘሌ23፥13፤ዕብ9፥2፤
24፥6 ዘፀ25፥23-30፤ ዘኍ4፥7
24፥7 ዘሌ2፥1፤2፥2

በኋላ በሰባተኛው ወር ከዐሥራ አምስተኛው
ቀን ጀምራችሁ ሰባት ቀን *ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) በዓል አክብሩ፤ የመጀመሪያው ቀን
የዕረፍት ዕለት ነው፤ ስምንተኛውም ቀን
እንደዚሁ የዕረፍት ዕለት ይሆናል:: 40በመ
ጀመሪያው ቀን የመልካም ዛፍ ፍሬ፣ የዘንባባ
ዝንጣፊ፣ የለመለመ ዛፍ ቅርንጫፍ የአኻያ
ዛፍ ቅርንጫፍ ይዛችሁ ሰባት ቀን በአምላ
ካችሁ *በእግዚአብሔር* (ኤሎሂም ያህዌ) ፊት ደስ ይበ
ላችሁ:: 41በየዓመቱም *የእግዚአብሔር* (ያህዌ)
በዓል አድርጋችሁ ሰባት ቀን አክብሩ፤
ይህም ለልጅ ልጃችሁ የዘላለም ሥርዐት
ነው፤ በሰባተኛውም ወር አክብሩት:: 42ሰባት
ቀን ዳስ ውስጥ ተቀመጡ፤ በትውልዱ
እስራኤላዊ የሆነ ሁሉ ዳስ ውስጥ ይሰን
ብት፤ 43በዚህም እኔ እስራኤላውያንን ከግ
ብፅ ባወጣሁ ጊዜ፣ ዳስ ውስጥ እንዲቀ
መጡ ማድረጌን የልጅ ልጆቻችሁ ያው
ቃሉ፤ እኔ *እግዚአብሔር* አምላካችሁ (ያህዌ
ኤሎሂም) ነኝ::’ ”
44በዚህ ሁኔታም ሙሴ የተመረጡትን
*የእግዚአብሔር* (ያህዌ) በዓላት ለእስራኤላውያን
አስታወቀ::

## *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት የሚቀርብ ዘይትና ኅብስት

24፥1-3 ተጓ ምብ - ዘፀ27:20-21

24 *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2“መብራቶቹ ያለማቋረጥ
እንዲያበሩ ከወይራ ተጨምቆ የተጠለለ
ዘይት እንዲያመጡልህ እስራኤላውያንን እዘዛ
ቸው:: 3አሮንም በመገናኛው ድንኳን ውስጥ
ከምስክሩ መጋረጃ ውጭ *በእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ፊት ያሉትን መብራቶች ከምሽት
እስከ ንጋት ያለ ማቋረጥ ያሰናዳቸው፤
ይህም ለትውልዶቻችሁ ሥርዐት ነው::
4*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት በንጹሕ የወርቅ
መቅረዝ ላይ ያሉት መብራቶች ያለማቋረጥ
መሰናዳት አለባቸው::
5“የላመ ዱቄት ወስደህ ዐሥራ ሁለት
ኅብስት ጋግር፤ እያንዳንዱ ኅብስትም በሁ
ለት ዐሥረኛ የኢፍ[ጨ] መስፈሪያ ዱቄት
ይጋገር:: 6እነዚህንም ስድስት ስድስቱን
በሁለት ረድፍ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት
ባለው የንጹሕ ወርቅ ጠረጴዛ ላይ አኑራ
ቸው:: 7ከኅብስቱ ጋር የመታሰቢያ ድርሻ
ሆኖ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) በእሳት የሚቀ
ርብ መሥዋዕት እንዲሆን ንጹሕ ዕጣን

ገ27 ወይም ጹሙ፤ እንዲሁም ቍ 29:32 ይመ
*32 ወይም ጹሙ
ጠ38 ወይም *እነዚህ በዓላት ከእግዚአብሔር ሰንበታት በተጨ ማሪ የምታቀርቡአቸው ናቸው፤ ስጦታዎቹም*
ጨ5 4.5 ሊትር ገደማ ይሆናል

በእያንዳንዱ ረድፍ ላይ አኑር:: 8ኅብስቱ
የእስራኤልን ሕዝብ ይወክል ዘንድ ዘወ
ትር በየሰንበቱ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት
ይደርደር፤ ይህም የዘላለም ቃል ኪዳን
ነው:: 9ኅብስቱ የአሮንና የልጆቹ ድርሻ
ነው፤ በተቀደሰ ስፍራም ይበሉታል፤ *ለእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) በእሳት ከሚቀርበው *መሥ
ዋዕት* እጅግ የተቀደሰ ድርሻቸው ነውና::”

## እግዚአብሔርን መስደብ የሚያስከትለው ቅጣት

10እናቱ እስራኤላዊት፣ አባቱ ግብፃዊ
የሆነ አንድ ሰው በእስራኤላውያን መካ
ከል ወጣ፤ በሰፈርም ውስጥ ከአንድ እስራ
ኤላዊ ጋር ተጣሉ:: 11የእስራኤላዊቱ ልጅ
*የእግዚአብሔርን* (ያህዌ) ስም በማቃለል ሰደበ፤
ስለዚህም ወደ ሙሴ አመጡት፤ የሰውየው
እናት ስም ሰሎሚት ነበር፤ እርሷም ከዳን
ወገን የተወለደው የደብራይ ልጅ ነበረች::
12*የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፈቃድም ግልጽ እስኪ
ሆንላቸው ድረስ በግዞት አኖሩት::

13*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 14“ተሳዳቢውን ከሰፈር ወደ ውጭ
አውጣው፤ ሲሳደብ የሰሙት ሁሉ እጃቸውን
በራሱ ላይ ይጫኑበት፤ ማኅበሩም ሁሉ
በድንጋይ ይውገረው:: 15እስራኤላውያንን
እንዲህ በላቸው፤ ‘ማንም ሰው ኤሎሂኡን
(ኤሎሂም) ቢሳደብ ኀጢአት ሠርቶአልና ይጠ
የቅበታል:: 16*የእግዚአብሔርን* (ያህዌ) ስም የሚ
ሳደብ ማንኛውም ሰው ይገደል፤ ማኅበሩ
ሁሉ ይውገሩት፤ መጻተኛም ሆነ የአገር
ተወላጅ *የእግዚአብሔርን* (ያህዌ) ስም ከሰደበ
ይገደል::

17“ ‘ሰውን ደብድቦ የገደለ ይገደል::
18የሌላውን ሰው እንስሳ ደብድቦ የገደለ
ማንኛውም ሰው ያንኑ ዐይነት እንስሳ ይተ
ካለት:: 19ማንኛውም ሰው በባልንጀራው
ላይ ጕዳት ቢያደርስ የዚያው ዐይነት
ጕዳት ይፈጸምበት፤ 20ይኸውም በስብራት
ፈንታ ስብራት፣ በዐይን ፈንታ ዐይን፣
በጥርስ ፈንታ ጥርስ ማለት ነው:: በሌላው
ሰው ላይ ያደረሰው ጕዳት በእርሱም ላይ
ይድረስበት፤ 21እንስሳ የገደለ ማንኛውም
ሰው በገደለው ፈንታ ይተካ፤ ሰው የገደለ
ግን ይገደል:: 22ለመጻተኛው ሆነ ለአገር
ተወላጅ አንድ ዐይነት ሕግ ይኑራችሁ፤
እኔ *እግዚአብሔር* ኤሎሂካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ::’ ”

23ሙሴም ይህን ለሕዝቡ ነገራቸው፤
እነርሱም ተሳዳቢውን ከሰፈር ወደ ውጭ
ወስደው በድንጋይ ወገሩት፤ እስራኤላው
ያንም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዳዘ
ዘው አደረጉ::

24፥8 ዘፀ25፥30፤ ዘኍ4፥7፤1ዜና9፥32፤ 2ዜና2፥4፤ማቴ12፥5
24፥9 ዘሌ6፥16፡ 17፤ማቴ12፥4፤ ማር2፥26፤ሉቃ6፥4፤
24፥11 ዘፀ3፥15፤ 18፥22፤20፥7፤31፥2፤ ዘኍ1፥4፤7፥2፤10፥15 13፥2፤17፥2፤ 2ነገ6፥33፤ኢሱ7፥18፤ 1ነገ7፥14ኢዮ1፥11፤
24፥12 ዘፀ18፥16
24፥14 ቍ23፤ ዘሌ20፥2፤ዘዳ13፥9፤ 17፥5፡7፤ሐሥ7፥58
24፥15 ዘፀ22፥28፤ ዘሌ5፥1
24፥16 ዘፀ21፥12፤ 22፥28፤1ነገ21፥10፡ 13፤ማቴ26፥66፤ ማር14፥64፤ ዮሐ10፥33፤19፥7፤ ሐሥ7፥58
24፥17 ቍ21፤ ዘፍ9፥6፤ዘፀ21፥12፤ ዘዳ27፥24
24፥18 ቍ21
24፥20 ዘፀ21፥24፤ ማቴ5፥38
24፥21 ቍ17፡18
24፥22 ዘፀ12፥49፤ 22፥21፤ዘኍ9፥14፤ ሕዝ47፥22፤
24፥23 ቍ14

25፥1 ዘፀ19፥11
25፥3 ዘፀ23፥10
25፥4 ቍ5፡6፡20፤ ዘሌ26፥35፤ 2ዜና36፥21፤ ኢሳ36፥16፤37፥30
25፥5 ቍ4፡11፤ ዘፍ40፥10፤ዘኍ6፥3፤ 13፥20፤ዘዳ23፥24፤ 2ነገ19፥29፤ነህ13፥15 ኢሳ5፥2፤
25፥6 ቍ4
25፥7 ዘፀ23፥11
25፥9 ዘፀ30፥10፤ ዘሌ16፥29፤23፥24፤ ዘኍ10፥8፤ኢሱ6፥4፤ መሳ3፥27፤7፥16፤ 1ሳሙ13፥3፤ ኢሳ27፥13፤ ዘካ 9፥14፤
25፥10 ቍ11፡27፡ 28፡50፤ዘሌ27፥17፡21 ዘኍ36፥4፤ ኢሳ61፥1፤ኤር34፥8፡ 15፡17፤ሕዝ46፥17፤ ሉቃ4፥19፤
25፥11 ቍ5፡10
25፥13 ቍ10
25፥14 ዘሌ19፥13፤ 1ሳሙ12፥3፡4፤ 1ቆሮ6፥8
25፥15 ቍ27፤ ዘሌ27፥18፡23
25፥16 ቍ27፡ 51፡52

## የሰባተኛው ዓመት ዕረፍት

25 *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን በሲና
ተራራ ላይ እንዲህ አለው፤ 2“ለእ
ስራኤላውያን እንዲህ ብለህ ተናገር፤ ወደ
ምሰጣችሁ ምድር በምትገቡበት ጊዜ ምድሪቱ
ራስዋ *የእግዚአብሔርን* (ያህዌ) ሰንበት ታክ
ብር:: 3ስድስት ዓመት በዕርሻህ ላይ ዝራ፤
ስድስት ዓመት ወይንህን ግረዝ፤ ፍሬው
ንም ሰብስብ:: 4በሰባተኛው ዓመት ግን
ምድሪቱ የዕረፍት ሰንበት ታድርግ፤ ይህም
*የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ሰንበት ነው:: በዕርሻህ
ላይ አትዝራ፤ ወይንህንም አትግረዝ:: 5ሳይዘራ
የበቀለውን አትጨደው፤ ካልተገረዘው የወ
ይን ተክልህ ፍሬ አትሰብስብ:: ምድሪቱ
የአንድ ዓመት ዕረፍት ታድርግ:: 6ምድሪ
ቱም በሰንበት ጊዜዋ የምታስገኘው ማንኛ
ውም ፍሬ ለአንተ፣ ለወንድ ባሪያህ፣ ለሴት
ባሪያህ፣ ለቅጥር ሠራተኛህና ከአንተ ጋር
ለሚኖር መጻተኛ ምግብ ይሁን፤ 7እንዲ
ሁም ለቤት እንስሶችህና በምድርህ ለሚ
ኖሩ የዱር አራዊት ምድሪቱ የምታበቅ
ለው ሁሉ መኖ ይሁን::

## የኢዮቤልዩ ዓመት

25፡8-38 ማመ - ዘዳ 15፡1-11
25፡39-55 ማመ - ዘፀ 21፡2-11፤ ዘዳ 15፡12-18

8“ ‘ሰባት የሰንበት ዓመታት ማለትም
ሰባት ጊዜ ሰባት ዓመታትን ቍጠር፤ ሰባቱ
የሰንበት ዓመታትም አርባ ዘጠኝ ዓመታት
ይሆናሉ:: 9ከዚያም በኋላ በሰባተኛው ወር
በዐሥረኛው ቀን፣ መለከት ይነፋ፤ በማስ
ተስረያ ቀንም በምድራችሁ ሁሉ መለከት
ንፉ:: 10አምሳኛውን ዓመት ቀድሱ፤ በም
ድሪቱ ሁሉ ላሉ ነዋሪዎች በሙሉ ነጻነት
ዐውጁ፤ ይህም ኢዮቤልዩ ይሁንላችሁ፤ ከእ
ናንተ እያንዳንዱ ወደ ቤተ ሰቡ ርስት፣
ወደ ወገኑም ይመለስ:: 11የአምሳኛው ዓመት
ኢዮቤልዩ ይሁንላችሁ፤ አትዝሩ፤ ሳትዘሩት
የበቀለውን አትጨዱ፤ ካልተገረዘውም የወ
ይን ሐረግ ፍሬ አትሰብስቡ:: 12ኢዮቤልዩ
ስለሆነ ለእናንተ የተቀደሰ ይሁን፤ ሳትዘሩት
በሜዳ የበቀለውን ብሉ::

13“ ‘በዚህ በኢዮቤልዩ ዓመት እያንዳንዱ
ሰው ወደ ርስቱ ይመለስ::

14“ ‘ከወገንህ ከአንዱ መሬት ብትገዛ
ወይም ብትሸጥለት፣ አንዱ ሌላውን አያ
ታል:: 15ከኢዮቤልዩ በኋላ ያሉትን ዓመታት
ብዛት መሠረት በማድረግ ከወገንህ ትገዛ
ለህ፤ እርሱም የቀሩትን የመከር ዓመታት
ብዛት መሠረት በማድረግ ይሸጥልሃል:: 16የዓ
መቱ ቍጥር ከበዛ ዋጋውን ጨምር፤ የዓ
መቱ ቍጥር ካነሰም፣ ዋጋውን ቀንስ፤
ምክንያቱም የሚሸጥልህ የዓመቱን የምርት

መጠን ነውና። 17 አንዱ ሌላውን አያታል፤
 አምላክህን (ኤሎሂም) ፍራ፤ እኔ እግዚአብሔር አምላ
ካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ።
18 “ ‘ሥርዐቴን ጠብቁ፤ ሕጌን በጥንቃቄ
አድርጉ፤ በምድሪቱም በሰላም ትኖራላችሁ።
19 ምድሪቱ ፍሬዋን ትሰጣለች፤ እስክትጠ
ግቡ ትበላላችሁ፤ በዚያም በሰላም ትኖ
ራላችሁ። 20 እናንተም፣ “ካልዘራን ወይም
ሰብላችንን ካልሰበሰብን በሰባተኛው ዓመት
ምን እንበላለን?” በማለት ትጠይቁ ይሆ
ናል። 21 በስድስተኛው ዓመት በረከቴን እሰ
ድላችኋለሁ፤ ምድሪቱም ለሦስት ዓመት
የሚበቃ ፍሬ ትሰጣለች። 22 በስምንተኛው
ዓመት በምትዘሩበት ጊዜ፣ የምትበሉት
ቀድሞ ከሰበሰባችሁት ሰብል ይሆናል፤
የዘጠነኛውን ዓመት መከር እስክትሰበስቡ
ድረስ ከዚሁ እህል ትበላላችሁ።
23 “ ‘መሬት ለዘለቄታ አይሸጥ፤ ምክን
ያቱም ምድሪቱ የእኔ ናት፤ እናንተም መጻ
ተኞችና እንግዶች ናችሁ። 24 ርስት አድር
ጋችሁ በምትይዙት ምድር ሁሉ መሬት
የሚዋጅበት ሁኔታ እንዲኖር አድርጉ።
25 “ ‘ከወገንህ አንዱ ደኽይቶ ርስቱን
ቢሸጥ፣ የቅርብ ዘመዱ መጥቶ ወገኑ የሸ
ጠውን ይዋጅለት። 26 ነገር ግን ሰውየው ርስ
ቱን የሚዋጅለት ምንም ዘመድ ባይኖረ
ውና፣ እርሱ ራሱ መዋጀት የሚችልበትን
ሀብት ቢያገኝ፣ 27 ርስቱን ከሸጠበት ጊዜ
ጀምሮ ያለውን የሽያጭ ዘመን በመቍጠር
የዋጋውን ልዩነት ለገዛው ሰው ይመልስ፤
እርሱም ወደ ገዛ ርስቱ ይመለስ። 28 ነገር
ግን ዋጋውን መመለስ ካልቻለ፣ የሸጠው
ርስት እስከ ኢዮቤልዩ ዓመት ድረስ የገ
ዢው ንብረት ሆኖ ይቈያል፤ በኢዮቤልዩ
ዓመት ለባለቤቱ ይመለሳል፤ ሰውየውም ወደ
ርስቱ ይመለሳል።
29 “ ‘ማንኛውም ሰው ቅጥር በተሠራለት
ከተማ ውስጥ የሚገኝ መኖሪያ ቤቱን ቢሸጥ
ከሸጠበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አንድ ዓመት
ሊዋጀው ይችላል፤ የመዋጀት መብቱ እስከ
አንድ ዓመት ድረስ ነው። 30 አንዱ ዓመት
ከማለቁ በፊት መዋጀት ካልቻለ ግን፣
ቅጥር በተሠራለት ከተማ ውስጥ ያለው
ቤት የገዢውና የልጅ ልጆቹ ንብረት ሆኖ
ይቀራል፤ በኢዮቤልዩ አይመለስለትም።
31 ቅጥር በዙሪያው ባልተሠራለት መንደር
ውስጥ የሚገኙ ቤቶች ግን እንደ ዕርሻ
መሬት ተቈጥረው ሊዋጁ ይችላሉ፤ በኢዮ
ቤልዩም ይመለሳሉ።
32 “ ‘ነገር ግን ሌዋውያን የራሳቸው በሆ
ኑት ከተሞች ውስጥ የሚገኙትን ቤቶቻ
ቸውን ምን ጊዜም የመዋጀት መብት አላ
ቸው። 33 ሌዋውያን በከተማቸው ያለውን
ቤታቸውን ቢሸጡና መዋጀት ባይችሉ፣
በኢዮቤልዩ ይመለሳል፤ በሌዋውያን ከተ
ሞች የሚገኙ ቤቶች በእስራኤላውያን መካ
ከል የሌዋውያን ንብረት ናቸውና። 34 በከ
ተሞቻቸው ዙሪያ ያለው የግጦሽ መሬት
ግን አይሸጥ፤ ለዘላለም ቋሚ ንብረታቸው
ነውና።
35 “ ‘በመካከልህ ከወገንህ አንዱ ቢደ
ኸይ፣ ራሱንም መርዳት ባይችል፣ በመካከልህ
ይኖር ዘንድ መጻተኛውን ወይም እንግዳ
ውን እንደምትረዳ እርዳው። 36 ወገንህ በመ
ካከልህ ይኖር ዘንድ ምንም ዐይነት ወለድ[a]
አትቀበለው፤ አምላክህን (ኤሎሂም) ፍራው። 37 ገን
ዘብህን በዐራጣ አታበድረው፤ ምግብህንም
በትርፍ አትሸጥለት። 38 የከነዓንን ምድር
ልሰጥህና አምላክህ (ኤሎሂም) ልሆን፣ ከግብፅ
ያወጣሁህ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ (ያህዌ
ኤሎሂም) ነኝ።
39 “ ‘ከወገንህ አንዱ ከመካከልህ ቢደኸይ፣
ራሱንም ለአንተም ቢሸጥ፣ እንደ ባሪያ አድ
ርገህ አታሠራው። 40 በመካከልህ እንዳለ ቅጥር
ሠራተኛ ወይም እንደ እንግዳ አድርገህ
ቍጠረው፤ እስከ ኢዮቤልዩ ዓመትም ይሥ
ራልህ፤ 41 ከዚያም በኋላ እርሱና ልጆቹ በነጻ
ይለቀቁ፤ ወደ ቤተ ሰቡና ወደ አባቶቹ
ንብረት ይመለስ። 42 እስራኤላውያን ከግብፅ
ያወጣኋቸው አገልጋዮቼ ስለሆኑ እንደ ባሪያ
አይሸጡ። 43 በጭካኔ አትግዛቸው፤ ነገር ግን
አምላክህን (ኤሎሂም) ፍራ።
44 “ ‘የሚኖሩህ ወንዶችና ሴቶች ባሪያ
ዎችህ፣ በዙሪያህ ካሉት አሕዛብ መካከል
የገዛሃቸው ባሪያዎች ይሁኑ። 45 እንደዚሁም
በመካከላችሁ ከሚኖሩት መጻተኞችና ከተ
ወለዱት ወገናቸው ባሪያዎችን ግዙ፤ ንብረ
ታችሁም ይሁኑ። 46 እነርሱንም እንደ ንብረት
ለልጆቻችሁ አውርሷቸው፤ በሕይወታቸው
ዘመን ሁሉ ባሪያዎች ይሁኑአችሁ፤ እስራ
ኤላውያን ወገኖቻችሁን ግን በጭካኔ አትግ
ዟቸው።
47 “ ‘በመካከላችሁ የሚኖር መጻተኛ
ወይም እንግዳ ሀብታም ቢሆንና ከወገናችሁ
አንዱ ደኽይቶ በመካከላችሁ ለሚኖር መጻ
ተኛ ወይም ከመጻተኛው ወገን ለአንዱ
ራሱን ቢሸጥ፣ 48 ከተሸጠ በኋላ ሊዋጅ
ይችላል። ከዘመዶቹም አንዱ፦ 49 አጎቱ ወይም
የአጎቱ ልጅ ወይም ከወገኖቹ ማንኛውም
የሥጋ ዘመዱ ይዋጀው፤ ሀብት ካገኘም
ራሱን መዋጀት ይችላል። 50 እርሱም ራሱን
ከሸጠበት ዓመት አንሥቶ እስከ ኢዮቤ

25፥17 ዘሌ19፥13፡14፡32 ኢዮ31፥16፤ ምሳ22፥22፤ ኤር7፥5፡6፤21፥12፤22፥3፡15፤ ዘካ7፥9-10፤ 1ተሰ4፥6፤
25፥18 ቍ19፤ ዘፍ26፥5፤ ዘሌ26፥4፡5 ዘዳ12፥10፤33፥28፤ ኢዮ5፥22፤ መዝ4፥8፤ ኤር23፥6፤30፥10፤ 32፥37፤ 33፥16፤ ሕዝ28፥26፤34፥25፤ 38፥14
25፥19 ቍ18፤ ዘሌ26፥4፤ ዘዳ11፥14፤ 28፥12፤ ኢሳ55፥10፤
25፥20 ቍ4
25፥21 ዘፀ16፥5፤ ዘዳ28፥8፡12፤ መዝ133፥3፤134፥3፤147፥13፤ ሕዝ44፥30፤ ሐጌ2፥19፤ ሚል3፥10፤
25፥22 ዘሌ26፥10
25፥23 ዘፍ23፥4፤ ዘፀ19፥5፤ ዘኍ36፥7፤ 1ነገ21፥3፤ ሕዝ46፥18፤ ዕብ11፥13
25፥24 ቍ29፡48፤ ሩት4፥7፤ ኤር32፥8
25፥25 ቍ48፤ ዘሌ27፥13፡19፡31፤ ሩት2፥20፤4፥4፤ ኤር32፥7፤
25፥26 ቍ49
25፥27 ቍ10፡15
25፥28 ቍ10፤ ዘሌ27፥24፤
25፥32 ዘኍ35፥1-8፤ ኢሱ21፥2
25፥34 ዘኍ35፥2-5፤ ሕዝ48፥14
25፥35 ዘዳ15፥8፤ 24፥14፡15፤ መዝ37፥21፡26፤ ምሳ21፥26፤ ሉቃ6፥35
25፥36 ዘፀ22፥25፤ ዘሌ19፥32፤ ኤር15፥10፤
25፥37 ዘፀ22፥25
25፥38 ዘፍ10፥19፤ 17፥7
25፥39 1ነገ5፥13፤ 19፥22፤ ኤር34፥14
25፥40 ቍ53
25፥41 ቍ28፤ ኤር34፥8
25፥42 ቍ38
25፥43 ዘፍ42፥18፤ ዘፀ1፥13፤ ሕዝ34፥4፤ ቈላ4፥1፤
25፥47 ነህ5፥5፤ ኢዮ24፥9
25፥48 ቍ24፥25
25፥49 ቍ26
25፥50 ቍ10፤ ኢዮ7፥1፤14፥6፤ ኢሳ16፥14፤21፥16

[a] 36 ወይም *እጅግ ብዙ ወለድ*፤ እንዲሁም ቍ 37 ይመ

ልዩ ዓመት ድረስ ያለውን ጊዜ ከገዛው ሰው
ጋር በመሆን ይቍጠር፤ ነጻ የሚለቀቅበ
ትም ዋጋ በእነዚያ ዓመታት ለአንድ ቅጥር
ሠራተኛ በሚከፈለው መሠረት ይተመ
ናል። 51ብዙ ዓመት የሚቀረው ከሆነም፣
እርሱን ለመግዛት ከተከፈለው ዋጋ ላይ
በቀረው ዓመት መጠን ለሚዋጅበት መልስ
ይክፈል። 52እስከ ኢዮቤልዩ ድረስ የሚቀ
ረው ጥቂት ዓመት ከሆነም፣ በቀረው
ዓመት መጠን የሚዋጅበትን መልስ ይክጠ
ፈል። 53ከዓመት እስከ ዓመት እንደ ቅጥር
ሠራተኛ ይኑር፤ አሳዳሪውም በፊትህ በጭካኔ
አይግ ዛው።
54“ ‘ከእነዚህ መንገዶች በአንዱ እንኳ
መዋጀት ባይችል፣ እርሱና ልጆቹ በኢዮ
ቤልዩ ዓመት በነጻ ይለቀቁ፤ 55እስራኤላ
ውያን ለእኔ አገልጋዮቼ ናቸውና። እነርሱ
ከግብፅ ምድር ያወጣኋቸው አገልጋዮቼ
ናቸው፤ እኔ *እግዚአብሔር* አምላካችሁ (ያህዌ
ኤሎሂም) ነኝ።

## በመታዘዝ የሚገኝ በረከት

26 “ ‘ትሰግዱላቸው ዘንድ ጣዖታትን
አታብጁ፤ ምስል ወይም የማም
ለኪያ ዐምድ አታቁሙ፤ በምድራችሁም
ላይ የተቀረጸ ድንጋይ አታኑሩ፤ እኔ *እግዚ
አብሔር* አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ።
2“ ‘ሰንበታቴን ጠብቁ፤ መቅደሴን አክ
ብሩ፤ እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ።
3“ ‘በሥርዐቴ ብትሄዱ፤ ትእዛዜንም በጥን
ቃቄ ብትጠብቁ፣ 4ዝናብን በወቅቱ እሰጣች
ኋለሁ፤ ምድሪቱ እህልዋን፣ የሜዳ ዛፎችም
ፍሬያቸውን ይሰጣሉ። 5የምትወቁት እህል፣
የወይን ዘለላ እስከምትቈርጡበት ጊዜ፣
የምትቈርጡትም የወይን ዘለላ፣ እህል እስ
ከምትዘሩበት ጊዜ ያደርሷችኋል፤ ምግባ
ችሁን እስክትጠግቡ ትበላላችሁ፤ በምድራ
ችሁም ላይ በጸጥታ ትኖራላችሁ።
6“ ‘በምድሪቱ ላይ ሰላምን እሰጣለሁ፤
ትተኛላችሁ፤ ማንም አያስፈራችሁም። ክፉ
አራዊትን ከምድሪቱ አስወግዳለሁ፤ ሰይፍም
በምድራችሁ ላይ አያልፍም። 7ጠላቶቻ
ችሁን ታሳድዳላችሁ፤ እነርሱም በፊታችሁ
በሰይፍ ይወድቃሉ። 8ከእናንተ አምስቱ
መቶውን፣ መቶውም ዐሥሩን ሺህ ያሳድ
ዳሉ፤ ጠላቶቻችሁም በፊታችሁ በሰይፍ
ይወድቃሉ።
9“ ‘ፊቴን ወደ እናንተ እመልሳለሁ፤
እንድታፈሩና እንድትበዙም አደርጋችኋለሁ፤
ቃል ኪዳኔንም ከእናንተ ጋር አጸናለሁ።
10የዓምናውን እህል እየበላችሁ ከጐተራው
ሳያልቅ ለዘንድሮው እህል ደግሞ ቦታ

25፥52 ቍ16
25፥53 ቈላ4፥1
25፥55 ዘሌ11፥44፡45
26፥1 ዘፀ20፥4፤ 23፥24፤ዘኍ33፥52፤ መዝ97፥7፤ኢሳ48፥5፤ ኤር44፥19፤ዕን2፥18፤
26፥2 ዘፀ20፥8፤ ዘሌ19፥30
26፥3 ዘፍ26፥5፤ ዘፀ24፥8፤ዘዳ6፥17፤ 7፥12፤11፥13፡22፤ 28፥1፡9
26፥4 ዘፀ23፥26፤ ዘሌ25፥19፤ዘዳ11፥14 ፤28፥12፤ኢዮ5፥10፤ 14፥9፤መዝ65፥9፤ 67፥6፤68፥9፤104፥13 ፤147፥8፤ኤር5፥24፤ ሆሴ6፥3፤ኢል2፥23፤ ዘካ10፥1፤
26፥5 ዘሌ25፥18፤ ዘዳ6፥11፤11፥15፤ ሕዝ36፥29-30፤ ኢል2፥19፡26፤
26፥6 ቍ22፤ ዘፍ37፥20፤ ኢዮ11፥18፡19፤ መዝ3፥5፤4፥8፤ 29፥11፤37፥11፤ 85፥8፤147፥14፤ ምሳ3፥24፤ኢሳ17፥2፤ 26፥3፤54፥13፤60፥18 ኤር30፥10፤ሐጌ2፥9፤ ሚክ 4፥4፤ሰፎ3፥13፤
26፥7 መዝ18፥37፤ 44፥5
26፥8 ዘዳ28፥7፤ 32፥30፤ኢሱ23፥10፤ መሳ15፥15፤ 1ዜና12፥14፤ ኢሳ30፥17፤
26፥9 ዘፍ1፥22፤ 17፥6፡7፤ነህ9፥23
26፥10 ዘሌ25፥22
26፥11 ቍ15፡43፡ 44፤ዘፀ25፥8፤ ዘዳ31፥6፤ 1ሳሙ12፥22፤ 1ነገ6፥13፤2ነገ17፥15 መዝ74፥7፤76፥2፤ ሕዝ37፥27
26፥12 ዘፍ3፥8፤ 17፥7፤ዘፀ6፥7፤ ኤር7፥23፤11፥4፤ 24፥7፤30፥22፤31፥1፤ ዘካ13፥9፤2ቆሮ6፥16
26፥13 ዘፀ6፥6፤ 13፥3፤ዘሌ11፥44፤ ኢሳ10፥27፤ኤር2፥20፤ 27፥2፤28፥10፤30፥8፤ ሕዝ30፥18፤34፥27፤ ሆሴ11፥4
26፥14 ዘዳ28፥15- 68፤ሚል2፥2
26፥15 ቍ11፤ ዘፍ17፥7
26፥16 ቍ 39፤ ዘዳ28፥22፡35፤ መዝ78፥33፤ መሳ6፥3-6፤ 1ሳሙ2፥33፤ኢዮ31፥8 መዝ107፥17፤

ታስለቅቃላችሁ። 11ማደሪያዬን[ጸ] በመካከ
ላችሁ አደርጋለሁ፤ ነፍሴም አትጸየፋችሁም።
12በመካከላችሁ እመላለሳለሁ፤ አምላካችሁ
(ኤሎሂም) እሆናለሁ፤ እናንተም ሕዝቤ ትሆና
ላችሁ። 13ለግብፃውያን ባሪያዎች እንዳትሆኑ
ከግብፅ ምድር ያወጣኋችሁ እኔ *እግዚአ
ብሔር* አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ፤ የባርነት
ቀንበራችሁን ሰብሬ ቀና ብላችሁ እንድ
ትሄዱ አድርጌአችኋለሁ።

## አለመታዘዝ የሚያስከትለው ቅጣት

14“ ‘ነገር ግን ባትሰሙኝ፣ እነዚህን ትዕ
ዛዛት ባትጠብቁ፣ 15ሥርዐቴን ብትንቁ፣
ሕጌን ብታቃልሉ፣ ትእዛዛቴንም ሁሉ ባለ
መፈጸም ቃል ኪዳኔን ብታፈርሱ፣ 16እኔም
ይህን አደርግባችኋለሁ፤ ድንገተኛ ድንጋጤ፣
የሚቀሥፍ፣ ዐይናችሁን የሚያጠፋና ሰውነ
ታችሁን የሚያመነምን ትኩሳት አመጣባች
ኋለሁ፤ እህል የምትዘሩት በከንቱ ነው፤
ጠላቶቻችሁ ይበሉታልና። 17በጠላቶቻችሁ
ድል እንድትሆኑ ፊቴን በእናንተ ላይ አከ
ብድባችኋለሁ፤ የሚጠሏችሁ ይገዟችኋል፤
ማንም ሳያሳድዳችሁም ትሸሻላችሁ።
18“ ‘ከዚህ ሁሉ በኋላ ባትታዘዙኝ፣ ስለ
ኀጢአታችሁ ሰባት ዕጥፍ እቀጣችኋለሁ፤
19የትዕቢታችሁን ኀይል እሰብራለሁ፤ ሰማ
ያችሁን እንደ ብረት፣ ምድራችሁንም እንደ
ናስ አደርጋለሁ። 20ኀይላችሁ በከንቱ ያል
ቃል፤ ምድራችሁ እህሏን፣ የምድሪቱ ዛፎ
ችም ፍሬዎቻቸውን አይሰጡምና።
21“ ‘በእኔ ላይ ማመፅ ብትቀጥሉና ባት
ታዘዙኝ እንደ ኀጢአታችሁ መጠን ሰባት
ዕጥፍ መቅሠፍት እጨምርባችኋለሁ። 22የዱር
አራዊትን እሰድባችኋለሁ፤ ልጆቻችሁን ይነጥ
ቋችኋል፤ ከብቶቻችሁን ያጠፉባችኋል፤
ቍጥራችሁ ይመነምናል፤ መንገዶቻችሁም
ሰው አልባ ይሆናሉ።
23“ ‘በዚህ ሁሉ ግን ወደ እኔ ባትመለሱ፣
በእኔም ላይ ማመፃችሁን ብትቀጥሉ 24እኔም
ጠላት እሆንባችኋለሁ፤ ስለ ኀጢአታች
ሁም ሰባት ዕጥፍ አስጨንቃችኋለሁ።

ሕዝ4፥17፤24፥23፤ 33፥10፤ 26፥17 ቍ36፡37፤ዘሌ17፥10፤ ዘዳ28፥7፡25፡48፤ኢሱ7፥4፡12፤ መሳ2፥15፤1ነገ8፥33፤2ዜና6፥24፤ መዝ53፥5፤ 106፥41፤ምሳ28፥1፤ ኢሳ30፥17፤ ኤር19፥7፤21፥7፤ ሕዝ15፥7፤ 26፥18 ቍ14፡21፤ መዝ99፥8፤ኤር21፥14፤አሞ3፥14
26፥19 ዘዳ28፥23፤ኢዮ38፥38፤ መዝ10፥4፤73፥6፤ ኢሳ16፥6፤25፥11፤28፥1-3፤ኤር13፥9፤48፥29፤ሕዝ24፥21፤ አሞ6፥8፤ሶፎ3፥11፤ 26፥20 ዘዳ11፥17፤ 28፥24፡38፤ መዝ127፥1፤ ኢሳ17፥11፤49፥4፤ኤር12፥13፤ሚክ6፥15፤ሐጌ1፥6፤
26፥21 ቍ18፥41፤ዘፍ4፥15 26፥22 ዘፍ37፥20፤ዘዳ28፥62፤ ኤር42፥2፤5፥6፤14፥16፤15፥3፤16፥4፤ሕዝ14፥15
26፥23 ኤር2፥30፤ 5፥3፤7፥28፤17፥23፤32፥33፤ሶፎ3፥2
26፥24 2ሳሙ22፥27

[ጸ]11 ወይም *የመገናኛ ድንኳኔን*

25ቃል ኪዳኔን ስላፈረሳችሁ፣ በላያችሁ
ሰይፍ በማምጣት እበቀላችኋለሁ፤ በከተሞ
ቻችሁ ውስጥ በምትሰበሰቡበት ጊዜ ቸነፈር
እሰድባችኋለሁ፤ ለጠላትም እጅ አልፋችሁ
ትሰጣላችሁ፡፡ 26የእንጀራችሁ እህል እንዲ
ቋረጥ በማደርግበት ጊዜ፣ ዐሥር ሴቶች በአ
ንድ ምጣድ ላይ እንጀራ ይጋግራሉ፤ እን
ጀራውንም በሚዛን መዝነው እናንተም
ትበላላችሁ፤ ግን አትጠግቡም፡፡
27" 'በዚህ ሁሉ ግን ባትታዘዙኝ፣ በእኔም
ላይ ማመፃችሁን ብትቀጥሉ፣ 28እኔም
በቍጣዬ እመጣባችኋለሁ፤ ስለ ኀጢአታ
ችሁም እኔው ራሴ ሰባት ዕጥፍ እቀጣች
ኋለሁ፡፡ 29የወንዶች ልጆቻችሁን ሥጋና
የሴቶች ልጆቻችሁን ሥጋ ትበላላችሁ፡፡
30የኰረብታ መስገጃዎቻችሁን እደመስሳለሁ፤
የዕጣን መሠዊያዎቻችሁን አፈርሳለሁ፤ በድኖ
ቻችሁን በድን በሆኑት ጣዖቶቻችሁ ላይ
እጥላለሁ፤ ነፍሴም ትጸየፋችኋለች፡፡ 31ከተ
ሞቻችሁን አፈራርሳለሁ፤ መቅደሶቻችሁንም
ወና አደርጋለሁ፤ ጣፋጭ ሽታ ያለውን
መሥዋዕታችሁንም አልቀበልም፡፡ 32በዚያ
የሚኖሩ ጠላቶቻችሁ እስኪደነቁ ድረስ፣
ምድሪቱን ባድማ አደርጋታለሁ፡፡ 33በአሕ
ዛብ መካከል እበትናችኋለሁ፤ ሰይፌን መዝ
ዤም አሳድዳችኋለሁ፡፡ ምድራችሁ ባድማ፣
ከተሞቻችሁም ፍርስራሽ ይሆናሉ፡፡ 34ምድሪቱ
ባድማ በሆነችበት ጊዜ ሁሉና እናንተም
በጠላቶቻችሁ ምድር በምትኖሩበት ወቅት
ምድሪቱ በሰንበት ዓመቷ ትደሰታለች፤
ምድሪቱም በሰንበቷ ታርፋለች፤ ትደሰታ
ለችም፡፡ 35ምድሪቱ እናንተ በነበራችሁባት
ጊዜ በሰንበት ያላገኘችውን ዕረፍት፣ ባድማ
በምትሆንበት ጊዜ ሁሉ ታገኛለች፡፡
36" 'ከእናንተ በሕይወት የተረፉትን፣
በጠላቶቻቸው ምድር ሳሉ ድንጋጤ እሰድባ
ቸዋለሁ፤ ነፋስ የሚያንቀሳቅሰው የቅጠል
ድምፅ ያስበረግጋቸዋል፤ የሚያሳድዳቸውም
ሳይኖር ከሰይፍ እንደሚሸሹ ይሮጣሉ፤
ይወድቃሉም፡፡ 37የሚያሳድዳቸው ሳይኖር
ከሰይፍ እንደሚሸሹ እርስ በርሳቸው
ይሰነካከላሉ፤ በጠላቶቻችሁም ፊት መቆም
አትችሉም፡፡ 38በአሕዛብ መካከል ታልቃላችሁ፤
የጠላቶቻችሁም ምድር ትውጣችኋለች፡፡
39ከእናንተ የተረፉት በጠላቶቻቸው ምድር
በራሳቸው ኀጢአትና በአባቶቻቸው ኀጢአት
ምክንያት መንምነው ያልቃሉ፡፡
40" 'ነገር ግን ለእኔ ያልታመኑበትንና
በእኔም ላይ ያመፁበትን የራሳቸውን ኀጢ
አትና የአባቶቻቸውን ኀጢአት ቢናዘዙ፣
41ይኸውም፣ እኔ ጠላት እንድሆንባቸውና
ወደ ጠላቶቻቸው ምድር እንድሰዳቸው ያደ
ረገኝን ኀጢአት ቢናዘዙ፣ ያልተገረዘው
ልባቸው ቢዋረድና ስለ ኀጢአታቸው የሚ
ገባውን ቅጣት ቢቀበሉ፣ 42በዚያ ጊዜ
ከያዕቆብ ጋር የገባሁትን ኪዳኔን፣ ከይስሐ
ቅም ጋር የገባሁትን ኪዳኔን፣ ደግሞም ከአ
ብርሃም ጋር የገባሁትን ኪዳኔን አስባለሁ፤
ምድሪቱንም አስባታለሁ፡፡ 43ምድሪቱ እነርሱ
ለቀዋት ስለሄዱ ባዶ ትቀራለች፤ እነርሱ
በሌሉበት ጊዜም ባድማ ሆና በሰንበትዋ
ትደሰታለች፤ ሕጌን በማቃለላቸውና ሥርዐ
ቴን በመናቃቸው፣ የኀጢአታቸውን ቅጣት
ይቀበላሉ፡፡ 44በዚህ ሁሉ ግን ከእነርሱ ጋር
የገባሁትን ኪዳኔን በማፍረስ፣ በጠላቶቻቸው
ምድር ሳሉ ፈጽሜ እስካጠፋቸው ድረስ አልተ
ዋቸውም፤ አልጸየፋቸውምም፤ እኔ እግዚ
አብሔር አምላካቸው (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ፡፡ 45ስለ
እነርሱም ስል፣ አምላካቸው (ኤሎሂም) እሆን ዘንድ
አሕዛብ እያዩ ከግብፅ ምድር ካወጣኋቸው
አባቶቻቸው ጋር የገባሁትን ኪዳን አስባለሁ፤
እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ፡፡' "
46እግዚአብሔር (ያህዌ) በራሱና በእስራ
ኤላውያን መካከል በሲና ተራራ ላይ በሙሴ
በኩል ያቆማቸው ሥርዐቶች፣ ሕጎችና ደንቦች
እነዚህ ናቸው፡፡

## ስለ ስጦታ የወጣ ሕግ

27 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2"ለእስራኤላውያን እንዲህ
ብለህ ተናገር፤ 'ማንኛውም ሰው ተመጣጣኙን
ዋጋ በመክፈል ለእግዚአብሔር (ያህዌ) ሰውን
ለመስጠት የተለየ ስእለት ቢሳል፣ 3ዕድሜው
ከሃያ እስከ ሥልሳ ዓመት ለሆነ ወንድ፣
በቤተ መቅደሱ ሰቅል[θ] ሚዛን መሠረት፣
ግምቱ አምሳ ጥሬ ሰቅል[ፌ] ብር ይሁን፡፡
4ለሴት ከሆነ ግምቱ ሠላሳ ሰቅል[T] ይሁን፡፡

26፥25 ዘፀ5፥3፤ 9፥3፤ዘኍ16፥46፤ 1ነገ8፥37፤ኤር5፥17፤ 15፥3፤47፥6፤50፥28፤ 51፥6፡11፤ሕዝ11፥8፤ 14፥17፤21፥4፤33፥2፤ ዕን3፥5፤
26፥26 1ነገ8፥37፤ 18፥2፤2ነገ4፥38፤ 6፥25፤8፥1፤25፥3፤ መዝ105፥16፤ ኢሳ3፥1፤9፥20፤ ኤር37፥21፤52፥6፤ ሕዝ4፥16፡17፤5፥16፤ 14፥13፤ሆሴ4፥10፤ ሚክ6፥14
26፥27 ቊ14
26፥28 ቊ18 ዘዳ32፥19፤መሳ2፥14 መዝ78፥59፤ 106፥40፤ዘዳ7፥10፤ ኢዮ34፥11፤ኢሳ 59፥18፤65፥6-7፤ 66፥6፤ኤር17፥10፤ 25፥29፤ኢል3፥4
26፥29 2ነገ6፥29፤ ኤር19፥9፤ሰቆ4፥10፤ ሕዝ5፥10፤ዘዳ28፥53
26፥30 ዘዳ12፥2፤ 1ሳሙ9፥12፤10፥5፤ 1ነገ3፥2፡4፤12፥31፤ 13፥2፡32፤2ነገ17፥29 23፥20፤2ዜና34፥3፤ መዝ78፥58፤106፥40 ኢሳ17፥8፤21፥9፤ 27፥9፤ኤር50፥2፤ ሕዝ6፥3፡6፡13፤ 16፥16፤አሞ6፥8፤7፥9
26፥31 2ነገ22፥19፤ ነህ1፥3፤መዝ74፥3-7፤ ኢሳ1፥7፤3፥8፡26፤ 6፥11፤24፥12፤61፥4፤ 63፥18፤64፥11፤ ኤር4፥7፤9፥11፤ 25፥11፤34፥22፤ 44፥2፡6፡22፤ሰቆ2፥7፤ ሕዝ24፥21፤36፥33፤ አሞ5፥21፡22፤ 7፥9፤8፥10፤ሚክ2፥4፤ 3፥12፤ሰፎ2፥5፤3፥6
26፥32 1ነገ9፥8፤ 2ዜና29፥8፤ኢሳ5፥6፤ 52፥14፤ኤር9፥11፤ 12፥11፤18፥16፤ 19፥8፤25፥11፤26፥9፤ 33፥10፤34፥22፤ 44፥22፤48፥39፤ ሕዝ5፥14፤26፥16፤ 27፥35፤28፥19
26፥33 ቊ31፤ ዘዳ4፥27፤28፥64፤ 1ሳሙ15፥22፤ ነህ1፥8፤ኢዮ36፥11፤ መዝ44፥11፤106፥27 ኤር4፥11፤7፥34፤ 9፥16፤13፥24፤31፥10 40፥3፡15፤42፥16፤ 50፥17፤ኢሳ49፥19፤ ሕዝ5፥10፤12፥15፤ 17፥21፤20፥23፤ 22፥15፤34፥6፤ ኢል3፥2፤ዘካ7፥14፤ አሞ9፥4
26፥34 ቊ43፤ 2ዜና36፥21፤ኢሳ1፥7፤ ኤር7፥34፤ 25፥11፤44፥6፤ሕዝ33፥29
26፥35 ዘሌ25፥4 26፥36 ቊ17፤ 2ነገ25፥5፤ኢዮ13፥25፤ መዝ58፥7፤ሰቆ1፥3፡ 6፤4፥19፤ሕዝ21፥7 26፥37 ኢሱ7፥12፤ ኤር6፥21፤13፥16፤ 46፥16፤ሕዝ3፥20፤ ናሆ3፥3
26፥38 ዘዳ4፥26፤ኢዮ4፥9፤36፥12፤ መዝ1፥6፤ኢሳ1፥28፤ ኤር16፥4፤44፥27 26፥39 ቊ16፤ዘፀ20፥5፤ኢሳ14፥21፤ ኢሳ24፥16 26፥40 ዘሌ5፥5፤መዝ32፥5፤38፥18፤ነህ9፥2፤ መዝ106፥6፤ኤር3፥12-15፤14፥20፤ሆሴ5፥15፤ ሉቃ15፥18፤ 1ዮሐ1፥9 26 41 ቊ21፤ዘዳ10፥16፤30፥6፤2ዜና7፥14፤ 12፥6፤ኢሳ6፥7፤33፥24፤40፥2፤53፥5፡6፡11፤ ኤር4፥4፤9፥25፡26፤ ሕዝ20፥43፤44፥7፡9፤ሐሥ7፥51 26፥42 ዘፍ28፥15፤35፥11-12፤ 26፥5፤ዘፀ2፥24፤ዘኍ11፥20፤14፥31፤ 1ሳሙ8፥7 26፥43 ቊ11፤ መዝ9፥25፤106፥24ኢሳ6፥11፤ 32፥14፤62፥4፤ኤር2፥15፤44፥2፤ ሰቆ1፥1፤ሕዝ20፥13፤ሕዝ36፥4 26፥44 ቊ11፡33፤ዘዳ4፥31፤ መሳ2፥1፤2ነገ17፥20፤25፥11፤ 2ዜና6፥36፤36፥20፤ኤር4፥27፤ 5፥10፤30፥11፤31፥37፤33፥26፤51፥5፤ሮሜ11፥2 26፥45 ዘፀ6፥8፤ ዘሌ25፥38፤ዘዳ4፥31 26፥46 ዘፀ19፥11፤ ዘሌ7፥38፤27፥34
27፥2 ዘፍ28፥20 27፥3 ዘፀ30፥13

[θ]3 0.6 ኪሎ ግራም ገደማ ይሆናል፤ እንዲሁም ቊ16 ይመ
[ፌ]3 11.5 ግራም ገደማ ይሆናል፤ እንዲሁም ቊ 25 ይመ
[T]4 0.3 ኪሎ ግራም ገደማ ይሆናል

[5]ዕድሜው ከአምስት እስከ ሃያ ዓመት ለሆነ
ሰው፣ ወንድ ከሆነ ግምቱ ሃያ ሰቅል፣[ሀ]
ሴት ከሆነች ግምቷ ዐሥር ሰቅል[ለ] ይሁን፡፡
[6]ዕድሜው ከአንድ ወር እስከ አምስት ዓመት
ለሆነ ሰው፣ ወንድ ከሆነ ግምቱ አምስት
ሰቅል[ሐ] ጥሬ ብር፣ ለሴት ከሆነ ሦስት
ሰቅል[መ] ጥሬ ብር ይሁን፡፡ [7]ሥልሳ ዓመት
ወይም ከዚያ በላይ ለሆነ ሰው፣ ወንድ
ከሆነ ግምቱ ዐሥራ አምስት ሰቅል፣ ሴት
ከሆነች ዐሥር ሰቅል ይሁን፡፡ [8]ስእለት
የተሳለው ድኻ ከሆነና ግምቱን መክፈል
ካልቻለ ግን፣ ለስጦታ ያሰበውን ሰው ወደ
ካህኑ ያምጣ፤ ካህኑም የተሳለው ሰው
ባለው ዐቅም መሠረት መክፈል የሚገባውን
ይተምንለታል፡፡

[9]" 'ሰውየው የተሳለው *ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) *መሥዋዕት* ሆኖ መቅረብ የሚችል
እንስሳ ከሆነ፣ እንዲህ ያለው *ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) የተሰጠ እንስሳ የተቀደሰ ይሆናል፡፡
[10]ሰውየው መልካም የሆነውን እንስሳ መልካም
ባልሆነው፣ መልካም ያልሆነውንም መልካም
በሆነው አይለውጥ ወይም አይተካ፤ አን
ዱን እንስሳ በሌላው ከተካም ሁለቱ የተቀ
ደሱ ይሆናሉ፡፡ [11]እንስሳው በሥርዐቱ
መሠረት የረከሰ፣ *ለእግዚአብሔርም* (ያህዌ)
*መሥዋዕት* ሆኖ መቅረብ የማይገባው ከሆነ፣
ሰውየው እንስሳውን ወደ ካህኑ ያቅርብ፤
[12]መልካም ቢሆን ወይም ባይሆን፣ ካህኑ
ዋጋውን ይወስን፤ የካህኑም ውሳኔ የጸና
ይሆናል፡፡ [13]ባለቤቱ እንስሳውን መዋጀት
ከፈለገ ግን፣ በተተመነው ዋጋ ላይ አንድ
አምስተኛ መጨመር አለበት፡፡

[14]" 'አንድ ሰው ቤቱን *ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ይሆን ዘንድ ቢቀድስ፣ መልካም ቢሆን
ወይም ባይሆን ካህኑ ዋጋውን ይተምን፤
ካህኑም የተመነው ዋጋ የጸና ይሆናል፡፡
[15]ቤቱን የቀደሰው ሰው መልሶ ሊዋጀው
ከፈለገ ግን፣ የዋጋውን አንድ አምስተኛ
በዋጋው ላይ መጨመር አለበት፤ ቤቱም
ዳግመኛ የራሱ ይሆናል፡፡

[16]" 'አንድ ሰው ከወረሰው ርስት ላይ
*ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) የዕርሻ መሬት ቢቀ
ድስ፣ ዋጋው የሚተመነው ለመሬቱ በሚያ
ስፈልገው ዘር መጠን ይሆናል፤ ይኸውም
ለአንድ ሆሜር[ሠ] መስፈሪያ የገብስ ዘር አምሳ
ሰቅል ጥሬ ብር ነው፡፡ [17]ሰውየው ዕርሻውን
የቀደሰው በኢዮቤልዩ ዓመት ከሆነ፣ የተወ
ሰነው ዋጋ አይለወጥም፡፡ [18]ዕርሻውን የሚቀ
ድሰው ከኢዮቤልዩ በኋላ ከሆነ ግን፣ ካህኑ
ዋጋውን የሚተምነው እስከሚመጣው የኢ
ዮቤልዩ ዓመት ድረስ ባሉት ዓመታት
ቍጥር ልክ ነው፤ የተተመነውም ዋጋ
ይቀነሳል፡፡ [19]ዕርሻውን የቀደሰው ሰው መልሶ

27፥5 ዘፍ37፥28
27፥6 ዘኍ3፥47፤ 18፥16
27፥8 ቍ12፥14፤ ዘሌ5፥11
27፥9 ቍ21፥26፡ 28፤ዘፍ28፥20፤ ዘፀ40፥9፤ዘሌ1፥2፤ ዘኍ6፥20፥18፥17፤ ዘዳ15፥19
27፥10 ቍ33
27፥11 ቍ27፤ ዘፀ13፥13፤ ዘኍ18፥15
27፥13 ዘሌ5፥16፤ 25፥25
27፥15 ቍ13፡20
27፥18 ዘሌ25፥10፡ 15
27፥19 ዘሌ25፥25
27፥21 ቍ9፥28፤ ዘሌ25፥10፤ዘኍ18፥14፤ሕዝ44፥29
27፥23፤ ዘሌ25፥15
27፥24 ዘሌ25፥28
27፥25 ዘፀ30፥13፤ ዘኍ3፥47፤ ሕዝ45፥12
27፥26 ዘፀ13፥12
27፥27 ቍ11
27፥28 ዘኍ18፥14፤ ኢሱ6፥17-19
27፥29 ዘዳ7፥26
27፥30ዘኍ18፥26፤ ዘዳ7፥6፤12፥6፥17፤ 14፥22፥28፤ 2ዜና31፥6፤ዕዝ9፥2፤ ነህ10፥37፤ 12፥44፤ 13፥5፤ኢሳ6፥13፤ ሚል3፥8፤
27፥31 ዘሌ5፥16፤ 25፥25

መዋጀት ከፈለገ፣ በዋጋው ላይ አንድ
አምስተኛ መጨመር አለበት፤ ከዚያ በኋላ
ዕርሻው እንደገና የራሱ ይሆናል፡፡ [20]ዕር
ሻውን ባይዋጅ ወይም ለሌላ ሰው አሳልፎ
ቢሸጥ፣ ከዚያ በኋላ ሊዋጀው አይችልም፡፡
[21]እርሻው በኢዮቤልዩ በሚለቀቅበት ጊዜ
*ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) እንደተሰጠ ዕርሻ ተቈ
ጥሮ ቅዱስና የካህናቱ[ረ] ንብረት ይሆናል፡፡

[22]" 'አንድ ሰው የወረሰው ርስት ያልሆ
ነውን፣ በገንዘቡ የገዛውን የዕርሻ መሬት
*ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) ቢቀድስ፣ [23]ካህኑ
የእርሻውን መሬት ዋጋ እስከ ኢዮቤልዩ
ዓመት ድረስ ባለው ጊዜ መጠን ይተም
ናል፤ ሰውየው የተተመነውን ዋጋ *ለእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) የተቀደሰ አድርጎ በዚያኑ
ዕለት ይክፈል፡፡ [24]በኢዮቤልዩ ዓመትም
የዕርሻው መሬት የቀድሞው ባለ ርስት
ለነበረው፣ ለሸጠውም ሰው ይመለሳል፡፡ [25]እያ
ንዳንዱ ዋጋ የሚተመነው በቤተ መቅደሱ
ሰቅል ልክ ሆኖ አንዱ ሰቅል ሃያ ጌራ ነው፡፡

[26]" 'የእንስሳት በኵር ቀድሞውኑ *የእግ
ዚአብሔር* (ያህዌ) ስለ ሆነ፣ ማንም ሰው የእ
ንስሳትን በኵር *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ)
*መቀደስ* አይችልም፤ በሬም[ሰ] ሆነ በግ *የእ
ግዚአብሔር* (ያህዌ) ነውና፡፡ [27]እንስሳው ርኩስ
ከሆነ ግን፣ ባለቤቱ በተተመነው ዋጋ ላይ
አንድ አምስተኛ ጨምሮ ሊዋጀው ይችላል፤
የማይዋጀው ከሆነ ግን በተተመነው ዋጋ
ይሸጥ፡፡

[28]" 'ነገር ግን *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) ተለይቶ
የተሰጠ[ሸ] ማንኛውም ነገር:- ሰውም ሆነ እን
ስሳ ወይም በውርስ የተገኘ መሬት አይሸ
ጥም፤ አይዋጅምም፡፡ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ)
የተሰጠ ማንኛውም ነገር እጅግ የተቀደሰ
ነውና፡፡

[29]" 'እንዲጠፋ የተወሰነ ማንኛውም ሰው
አይዋጅም፤[ቀ] መገደል አለበት፡፡

[30]" 'ከዕርሻ ምርትም ሆነ ከዛፍ ፍሬ፣
ማንኛውም ከምድሪቱ የሚገኝ ዐሥራት
*የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ነው፤ *ለእግዚአብሔርም*
(ያህዌ) የተቀደሰ ነው፡፡ [31]አንድ ሰው ከዐሥ
ራቱ የትኛውንም መዋጀት ቢፈልግ፣ በዋ

[ሀ]5 0.2 ኪሎ ግራም ገደማ ይሆናል
[ለ]5 110 ግራም ገደማ ይሆናል፤ እንዲሁም ቍ 7 ይመ
[ሐ]6 55 ግራም ገደማ ይሆናል
[መ]6 35 ግራም ገደማ ይሆናል
[ሠ]16 220 ሊትር ገደማ ይሆናል
[ረ]21 ወይም *የካህኑ*
[ሰ]26 የዕብራይስጡ ቃል ተባዕትና እንስትን ሊያጠቃልል ይችላል
[ሸ]28 የዕብራይስጡ አገላለጽ አንድን ነገር ወይም ሰውን እንደማይመለስ ሆኖ ለእግዚአብሔር መስጠትን ያመለክታል፡፡
[ቀ]29 የዕብራይስጡ አገላለጽ አንድን ነገር ወይም ሰውን ሙሉ በሙሉ በማስወገድ እንደማይመለስ ሆኖ ለእግዚአብሔር መስጠትን ያመለክታል

ጋው ላይ አንድ አምስተኛ መጨመር
አለበት። [32]ከቀንድ ከብቶች፣ ከበጎችና
ከፍየሎች መንጋ የሚወጣው ዐሥራት
ከእረኛ በትር በታች ከሚያልፉት ዐሥረኛው
እንስሳ ይሆናል፤ ይህም *ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) የተቀደሰ ነው። [33]ሰውየው መልካም

27፥32 መዝ89፥32፤ ኤር33፥13፤ ሕዝ20፥37
27፥33 ቍ10፤ ዘኍ18፥21
27፥34 ዘፀ19፥11፤ ዘሌ7፥38፤ ሐሥ7፥38

የሆነውን መልካም ካልሆነው አይለይ
ወይም አይተካ፤ አንዱን በሌላው ቢተካ
ግን ሁለቱም እንስሳት የተቀደሱ ይሆናሉ፤
ሊዋጁም አይችሉም።
[34]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) በሲና ተራራ ላይ
በሙሴ አማካይነት ለእስራኤል ሕዝብ የሰጣ
ቸው ትእዛዛት እነዚህ ናቸው።